የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረው ሚና

(በቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት፣ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ሲሳይ ነጋሽ

ሐምሌ 2015ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረው ሚና

(በቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት፣ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት


በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ማስተማር ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ሲሳይ ነጋሽ

አማካ፡- ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ር)



ሐምሌ 2015ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረው ሚና

በ

ሲሳይ ነጋሽ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ | ቀን |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ደረጃ ያደረሰኝ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይጋባው፡፡ በመቀጠል ከትልመ-ጥናቱ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ፅሁፍ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በአካልም ሆነ በስልክ ስህተቶቼን እያረሙ፣ እያበረታቱና ሙህራዊ አስተያየት እየሰጡ ጥናቴ ለዚህ ደረጃ እንዲበቃ ላገዙኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ዳዊት ፍሬህይወት ምስጋናዬ ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረስልኝ፡፡

ለጥናቴ መሳካት አስፈላጊውን መረጃ ያለመሰልቼት በመስጠት የተባበራችሁኝ የቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያለ እናንተ ድጋፍ ይህ ጥናት ውጤታማ አይሆንም ነበርና ላደረጋችሁልኝ ቅን ትብብር ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ሳዘጋጅ የእስታቲክሱን ሙያዊና የሀሳብ እገዛ ላደረጉልኝ መ/ር አለማየሁ ደስታው እንዲሁም ለዚህ ጥናት መሳካት የቁሳቁስና የሞራል ድጋፍ ለሰጡኝ የቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ርዕሰ መምህር ዳምጠው ነጋሽን ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ ከምንም በላይ ከጎኔ በመሆን ለጣናቴ መሳካት ትልቅ ድርሻ ያላትን ውድ ባለቤቴ ወይንሸት ታደሰን እጅግ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ጥናት መሳካት ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና የቤተ መጻህፍት ባለሙያዎች እንዲሁም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ምስጋናዬ ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረሳችሁ፡፡

# አህፅሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት አብይ አላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ጥናቱ የተከተለው ከፊል ሙከራዊ የምርምር ዘዴን ነው። ጥናቱ የተካሄደው በሞጆ ከተማ በሚገኘው ቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን የተመረጠውም በአመቺ የንሞና አመራረጥ ዘዴ ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎችም በ2015ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ 68 የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ በቀላል እጣ ናሞና ዘዴ ተመርጠው አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል። መረጃው የተሰበሰበውም በቅድመ ትምህርት ፈተናና ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም በድህረ ትምህርት ፈተና ነው። ጥናቱ ወደተግባር ሲገባ መጀመሪያ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቅድመ ፈተና ተሰጥቷል። በውጤቱ መሰረትም በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በተገኘው አማካይ ውጤት ሁለቱ ቡድኖች ከልምምዱ በፊት የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው የስታትቲክ ስሌቱ ($p>0.05$) አረጋግጧል። የቅድመ ፈተና ውጤቱን በማስከተል የሙከራ ቡድኑ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማስተማር ዘዴ አቀራራብ ስልት እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መንገድ ክሂሎቹን ነጥሎ በማቅረብ እንዲማሩ ተደርጓል። ትምህርቱ ለተከታታይ ለስምንት ሳምንታት (ሁለት ወራት) ከተሰጠ በኂላ ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል። ውጤቱንም በገለጭ ስታቲስቲክስና በባእድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኗል። በዚህም መሰረት የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (26.8824) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (19.5294) በስታትስቲክ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ሆኖ በመገኘቱ የጎላ ልዩነት መመዝገቡ ተረጋግጧል። በዚህም መሰረት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎቹን የማነንበብና የመጻፍ ክሂሎች ያሳድጋል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትኩረት በመስጠት በቅንጅት ቢያስተምሩ፤ የመርሐ ትምህርትና የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆችአዲስ መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጻህፍት በሚያዘጋጁበት ወቅት እነዚህን የቋንቋ ክሂሎች በቅንጅት የሚቀርቡበት መንገድ ቢኖርና ለልምምዱም በቂ ክፍለጊዜ ቢመደብለት እንዲሁም ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በተለይ አራቱን የቋንቋ ክሒሎች አቀናጅቶ ከማስተማር አኳያ በስፋት ጥናት ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል የሚሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።*

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ 3
አህፅሮተ ጥናት ........ 4
ማውጫ ........ i
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ iii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3 የጥናቱ መላምት ........ 3
1.4 የጥናቱ አላማ ........ 3
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7 የጥናቱ ውሱንነት ........ 4
1.8 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ብያኔ ........ 5
ምዕራፍ ሁለት ........ 6
ክለሳ ድርሳናት ........ 6
2.1 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት ........ 6
2.2 ክሂሎች እንዴት ይቀናጃሉ? ........ 7
2.3 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች ........ 8
2.4 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ ........ 9
2.5 የማንበብ ክሂል ምንነት ........ 10
2.6 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት ........ 12
2.7 የመፃፍ ክሂል ምንነት ........ 13
2.8 የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ........ 13
2.9 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስርና መደጋገፍ ........ 14
2.10 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማቅረብ አስፈላጊነት ........ 16
2.11 የማንበብና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ማስተማሪያ ዘዴዎች ........ 17
2.12 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማቅረብ ዘዴ ውስጥ የመምህሩ ሚና ........ 20
2.13 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 22

ምዕራፍ ሶስት ..... 25
የአጠናን ዘዴ..... 25
3.1 የጥናቱ ዘዴ ..... 25
3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ..... 25
3.2.1 የምርምር ቦታና የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ..... 25
3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ..... 25
3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ..... 26
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች..... 27
3.2.1 ፈተና..... 27
3.2.1.1 ቅድመ ትምህርት ፈተና ..... 27
3.2.1.2 ድህረ ትምህርት ፈተና ..... 28
3.2.2 ቃለ መጠይቅ ..... 30
3.3 የትምህርት እቅድ ..... 30
3.4የመማሪያ ምንባቦችና መልመጃዎች አዘገጃጀት..... 31
3.5 የትምህርቱ አሰጣጥና የትግበራው ሂደት ..... 31
3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ..... 34
ምዕራፍ አራት ..... 35
የመረጃ ትንተናና የግኝት ማብራሪያ..... 35
4.1 የውጤት ትንተና..... 35
4.1.1 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና ..... 35
4.1.2 የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና..... 36
4.1.3 የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና ..... 37
4.1.4 የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና..... 38
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..... 39
ምዕራፍ አምስት፣ ማጠቃለያ እና አስተያየት ..... 41
5.1 የጥናቱ ማጠቃለያ ..... 41
5.2 የጥናቱ መደምደሚያ ..... 42
5.3 አስተያየት ..... 43
ዋቢ ፅሁፎች ..... 45
አባሪዎች..... 48

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**ገፅ**


ሰንጠረዥ 3.1፦ ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች መረጃ .................................... 26

ሰንጠረዥ 3.2፦ የተማሪዎቹን ፈተና ያረሙ መምህራን መረጃ ......................................... 29

ሰንጠረዥ 4.1፦ የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት
ቡድናዊ ገላጭ ስታትስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት .................................... 35

ሰንጠረዥ 4.2፦ የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት
ቡድናዊ ገላጭ ስታትስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት.................................... 36

ሰንጠረዥ 4.3፦ የቅድመ ትምህር ፈተና አጠቃላይ ውጤት ቡድናዊ ገላጭ
ስታቲስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................ 37

ሰንጠረዥ 4.4፦ የድህረ ትምህር ፈተና አጠቃላይ ውጤት ቡድናዊ ገላጭ
ስታቲስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ......................................................... 38

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማዳበር የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ማዳበርና ሰዋስዋዊ ህግጋትን በማሳወቅ ተማሪዎች በቋንቋው ጥሩ ተናጋሪ፣ አድማጭ፣ አንባቢ እና ጸሀፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ትምህርቱ ተፈጥሯዊ መንገድ እንዲከተልና ተደጋጋፊነት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ ተማሪዎች የተማሩትን ቋንቋ በእውነተኛው አለም ላይ ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙበትና ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ስለሚያግዛቸው ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

ቋንቋን ለማስተማር ሲታቀድ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ ይህም እንደ ትምህርቱ ዓላማና ግብ እንዲሁም በዘመኑ እንደነበረው የቋንቋ ፍልስፍና መሰረት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ምሁራን ሲነደፉ ይታያሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያግዘው ተግባቦታዊ አቀራረብ የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገው ሁኔታ ግብ እንዲመታ ያግዛሉ ተብለው ከተጠቀሱት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ ነው (Littlewood፣1981:93):: ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ እንዲያጎለብቱ ለማድረግ በጥንቃቄ የታቀደ የቋንቋ ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በአግባቡ ማስተማር የሚያስችል የአቀራረብ ስልት መርጦ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡት ይዘቶች ከሚኖራቸው ዋና ዋና አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ብቃት ማጎልበት ነው፡፡ በመሆኑም ክሂሎች እንደ አይነታቸው በተገቢ መንገድ ተቀናጅተው ለተማሪዎቹ ተስማሚ በሆነ መንገድ መቅረብ እንዳለባቸው (Cunningsworth 1995:74) አስረድተዋል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረጹ ዓላማዎች አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት ሲሆን ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መምጣቱን (Byrne 1981:107) ገልጸዋል፡፡ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተው ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል:: የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ማለት በቋንቋ ክሂሎች አቀራረብ ወቅት አንዱ ክሂል ሲነሳ ሌላው ክሂል ተከትሎ የሚነሳ በመሆኑ ተያያዥነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች በማቀናጀት ማስተማርን የሚመለከት ነው (Byrne1981:108 እና Mcdonugh and Shaw 1992:201)::

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማቀናጀት ወይም አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ በማድረግ እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች መካከል "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ይህ አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ ተማሪዎች በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ በማንበብ እና በመጻፍ ክሂሎች ቅንጅት ላይ ጥናት ማድረግ እና አቀራረቡ እንዲሻሻል ማድረግ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡፡

ሞገስ (1999) ባደረጉት ጥናት እንደገለጹት "በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት ማንበብና መጻፍ በትምህርት ተኮር (Subject Centered) ስርዓተ ትምህርት አቀራረብ እንደተለያዩ አላባውያን ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ በዚህም በማንበብና በመጻፍ ትስስር ላይ ጥናት ማካሄድ የተለመደ አልነበረም፡፡" በተጨማሪም "በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ አመታት ላይ ግን በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ዝምድና ለማጥናት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምርምሮቹ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ከቀረቡና በልምምድ ከተተገበሩ ለክሂሎቹ መጎልበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡" እንዲሁም በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች Harp, etal (1996) እና Ruddel (1997) እንደገለጹት በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር መኖሩንና በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ የተመራማሪዎቹ ሃሳብ እንደሚያመለክተው የዚህ ጥናት አቅራቢም ከልምዱ እንደተገነዘበው ለክሂሎቹ አለማደግ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች ቅንጅት አለመኖር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረው ጠቀሜታ ትንተና" በሚል ርዕስ ሙከራዊ ጥናቱን እንዲያካሂድ ያነሳሱት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው አጥኚው በመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በአማርኛ መምህርነት እንዲሁም በትምህርት ክፍል ተጠሪነት ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ሲያገለግል ከቋንቋ መምህራን ጋር የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ በሚያደርግበት ጊዜ የማንበብና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ላይ ክፍተት ማየቱ ነው፡፡

በሌላ በኩል በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሂል ዙሪያ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ሞገስ (1999) ፣ አለማየሁ (2011) ፣ እሸቴ (2003) ይጠቀሳሉ፡፡ በጥናታቸውም የሁለቱ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ችግር እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ ከችግሮች መካከል ለአብነት ያህል አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ ሆኖ አለመቅረቡ፣ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱት መልመጃዎች የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ አለመሆናቸው፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች አቀራረብ በመማሪያ መጽሀፉ አዘገጃጀትና በክፍል ውስጥ አተገባበሩ በተናጠል እንጅ በቅንጅት አለመሆኑን በጥናታቸው ውጤት ገልጸዋል፡፡ ይህንንም አጥኚው ክሂሎቹ ታቅደው በቅንጅት የሚቀርቡበት ሁኔታ አለመኖሩን ይረዳል፡፡ በመሆኑም "ክሂሎችን በተናጠል ወይስ በቅንጅት ማስተማር ነው ለክሂሎቹ መጎልበት አስተዋጽኦ ያለው?" የሚለውን ጥያቄ በሙከራዊ ጥናት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መላምት

የጥናቱን ዓለማ ለማሳካት ያስችል ዘንድ አማራጭ መላምት (H1) እና አልቦ መላምት (H0) በመነሻነት አገልግለዋል፡፡ እነሱም፡-

1. H1፡- የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ጉልህ ሚና አለው፡፡
2. H0፡- የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ጉልህ አይደለም የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ መመርመር ሲሆን ይህን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

1. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎቹን የማንበብና የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ክሂሎችን ነጥሎ ከማስተማር ዘዴ የተለየ አስተዋጽኦ መኖር አለመኖሩን መመርመር፡፡
2. የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ከተማሩበት መንገድ የትኛው ውጤታማ መሆኑን መመርመር፡፡
3. የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በምን ያህል ደረጃ ትስስርና ዝምድና አላቸው የሚለውን መፈተሽ የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-** የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በቅንጅት መቅረባቸው ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝበው ተግባራዊ እንዲደርጉ ይረዳቸዋል፡፡
2. **ለመማሪያና መርሀ ትምህርት መጽሀፍ አዘጋጆች፡-** የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ያላቸውን ትስስርና ዝምድና በመገንዘብ ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማር በሚያስችል መልኩ እንዲያዘጋጁ ግብዓት ይሰጣል፡፡
3. **ለጥናት አድራጊዎች፡-** በክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የመነሻ ሀሳብ እንዲሁም ማጣቀሻ በመሆን ያገለግላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በሞጆ ከተማ አስተዳደር ለጥናቱ በተመረጠው ቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ላይ ነው፡፡ ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን አያካትትም፡፡ ከቋንቋ ክሂሎች መካከልም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ጠቀሜታ በሙከራዊ ጥናት ማረጋገጥ ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ውጭ ሌሎች ከክሂሎቹ ጋር ተያያዥ የሆኑ ክንውኖችን አልተመለከተም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውሱንነት

በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካት ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን ስራው በበቂ ሁኔታ ሁሉንም ነገሮች

ሸፍኗል ማለት ስለማይቻል ጥናቱ ውሱን የሚሆንባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህም ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ ጥናቱ የተካሄደው ከስራ ጎን ለጎን በመሆኑ የጊዜ እና የገንዘብ አቅም ውሱንነት አጋጥሟል፡፡ በመሆኑም ከመደበኛ ስራው ጊዜ ውጭ ሰአት በማመቻቸት መረጃዎችን የመሰብሰብና የመተንተን ስራውን በመስራት ችግሩን ለመቅረፍ ተሞክሯል፡፡
- ✓ የጥናቱ ግኝቶች ለተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ጠቃሚ ግብዓቶች እንደሚሰጡ ቢታመንም ጥናቱ በጊዜ እጥረት፣ በፋይናንስ አቅምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጥናቱ በሞጆ ከተማ አስተዳደር በቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በሁለት ክፍሎች ብቻ በመካሄዱ የሌሎች ክፍሎችን የማንበብና የመጻፍ ክሂል ችሎታ አያንፀባርቅም፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ብያኔ

- ✓ የመጻፍ ክሂል (Writing skill):- "የመጻፍ ክሂል ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሲሆን የማመንጨት ክሂል በመባል ከመታወቁም በላይ የቋንቋ ተጠቃሚዎች ጥቅል ክሂሎች በአንድ ጊዜ እንዲኖራቸው ያደርጋል" Harmer (1993፡15)፡፡ በዚህ ጥናትም በዚሁ ትርጉሙ አገልግሏል፡፡
- ✓ የማንበብ ክሂል (Reading skill):- "የማንበብ ክሂል ፀሀፊው በጽሑፍ ያሰፈረውን መልዕክት በንባብ ወደ ትርጉም የመለወጥ ሂደት ነው" Nuttall (1982፣18) በዚህ ጥናትም በዚሁ ትርጉሙ አገልግሏል፡፡
- ✓ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅት (Reading-Writing Connections):- ሁለቱንም ክሂሎች ያለምንም ክፍተት በትስስራቸውና በዝምድናቸው ተመስርቶና አቀናጅቶ የማቅረብ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ዑደታዊ በሆነ መልኩ እያነበቡ የሚጽፉበት እየጻፉ ደግሞ የሚያነቡበት ሂደት ነው፡፡
- ✓ የሙከራ ቡድን (Expermental Groups) በሙከራ ጥናቱ ጊዜ በቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ ስልት የተማሩት የተማሪዎች ቡድን ነው፡፡
- ✓ የቁጥጥር ቡድን (Control Groups) በሙከራ ጥናቱ ጊዜ በተለምዶው የትምህርት አቀራረብ ስልት የተማሩት የተማሪዎች ቡድን ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ በቋንቋ ክሂሎች አቀራረብ ወቅት አንዱ ክሂል ሲነሳ ሌላው ተከትሎ የሚነሳ በመሆኑ ተያያዥነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች በማቀናጀት ማስተማርን የሚመለከት ነው፡፡ Byrne (1981:108) ከዚህ ምሁር ሀሳብ የምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመርና በማስተሳሰር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲመጡ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡

Rivers (1981:297) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ ሌሎች ክሂሎችንም አብረው የሚያጎለብቱበት ዘዴ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የጽህፈት ክሂልን ማስተማር ከተፈለገ የተማሪዎቹ የማዳመጥና የማንበብ ክሂል ችሎታ መዳበር ይኖርበታል፡፡ምክንያቱም ተማሪዎች ጥሩ የሆነ የመናገር፣ የማዳመጥና የማንበብ ችሎታ ካላቸው ጥሩ ጸሀፊ ስለሚሆኑ ሌሎች ክሂሎችንም አያይዞ (በቅንጅት) ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ብቃት ለማሳደግ የጻፉትን፣ ያዳመጡትንና ያነበቡትን ነገር በቡድንም ሆነ በተናጠል እንዲናገሩና የተለያዩ ተግባራትን እንዲፈጽሙ ቢደረግ የተሻለ የመማር ማስተማር ሁኔታ እንደሚፈጠርና አንዱ ክሂል ከሌላው ክሂል ጋር የተቆራኘ ቢሆንም ቋንቋውን ለትክክለኛ አላማ ለማዋል በትምህርት መደገፍ እንዳለበት ነው፡፡

የቋንቋ ክሂሎችን አቀራረብ ስናስብ በአንድ መማሪያ ክፍል አንድን የቋንቋ ክሂል ነጥሎ ማቅረቡ አስቸጋሪ ነው፡፡ የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታሰም የመጻፍ ክሂል አብሮ መምጣቱ አይቀርም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ትስስር የቋንቋ ባህሪ የሚፈጥረው ቢሆንም በቋንቋ ትምህርት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ Byrne (1981:108) እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚፈጠረውን ቅንጅት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታቅዶበት ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁና የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ሂደት ነው፡፡ የክሂሎች ቅንጅታዊ አተገባበር ከክፍለ ጊዜው የትምህርት ዕቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባውን ክሂል በዋናነት ትኩረት እንዲቸረው ለማድረግ

ያስችላል፡፡ አክለውም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በእርስ ተሳስረው አንዱ ሲነሳ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ክሂሎችን በማስከተል ተዋህደው የሚቀርቡበት የቋንቋ ክሂሎችን የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

Rivers (1981:297) በበኩላቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሚማሩበት ጊዜ ሌሎችንም ክሂሎች አብረው እንዲያዳብሩ ለምሳሌ ተማሪዎች በሳል ድርሰት እንዲጽፉ ከተፈለገ በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ መዳበር እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጣም ጥሩ የሆነ አንብቦ የመረዳት ክህሎት የመናገርና የማዳመጥ ብቃት ካላቸው ጥሩ ጽሁፍ እንደሚጽፉ የታመነ ነው፡፡ በመሆኑም ጽህፈትን ስናስተምር ሌሎችም አብረው እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከምሁሩ ሃሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ ወይም እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

## 2.2 ክሂሎች እንዴት ይቀናጃሉ?

ክሂሎች የሚለያዩባቸው የየራሳቸው ባህሪ ቢኖራቸውም ተደጋጋፊ እንደሆኑ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ከንባብ ክሂሎች ጋር በማጣመር የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን መጠቀም ተመራጭ ነው፡፡ የትምህርት ይዘቶች ለማስተማሪያነት ስነ ዘዴ ማፍለቂያዎች እንደሆኑ Corder (1973:5) ይገልጻሉ፡፡

የቋንቋ ክሂሎች እንዴት ይቀናጁ የሚለውን ሀሳብ አምስት ሞዴሎች ብሎ አስፍሯቸዋል፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ይዘት ተኮር መመሪያ፡- ከስሙ እንደምንረዳው ይዘትን መሰረት ባደረገ መልኩ ክሂሎችን ማዋሀጃ ሞዴል ነው፡፡ ምሳሌ፡- ቋንቋውን ለአንድ ታላሚ ተግባር ማዋል (ለምህንድስና፣ ለግብርና፣ ለህክምና ወዘተ.)

ለ. ጭብጥ ተኮር መመሪያ፡-ይዘት ተኮር ለጭብጥ ተኮር ጠንካራ ትርጉም ሲሆን ጭብጥ ተኮር ደግሞ ለይዘት ተኮር ደካማ ትርጉም ነው፡፡ ይህ ማለት ይዘት ተኮር ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በታላሚው ቋንቋ ትምህርቱን ማስተማር ላይ ነው፡፡ ለጭብጥ ተኮርም ሆነ ለይዘት ተኮር ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ መመሪያዎች

ድንገቴያዊነት፣ ትርጉማዊ መማር፣ ተፈጥሯዊ ተነሳሽነት፣ ተግባቦታዊ ብቃት ናቸው።

ሐ. ከልምምድ የመነጨ መማር፡- በዚህ የመማር ልምድ መምህሩ ተማሪዎች እንዲማሩ የሚያደርግበት መንገድና ስህተታቸውንም ቢሆን በየጊዜው ቋንቋውን በመጠቀም ሂደት ተማሪዎች ለሚኖራቸው ልምዶች መማራቸው ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። የልምምድ መማር የራሱ የሆኑ ብልሀቶች አሉት። እነሱም፡- ፕሮጀክቶችን ማሰራት፣ የኮምፒውተር ተግባራት፣ የጥናትና ምርምር ስራ፣ የማህበራዊ መስተጋብር ሌምምዶች፣ የመስክ ጉዞ፣ የሚና ጨዋታ ተነሳሽነት ከዚህ በተጨማሪ መምህር መር ብልሀቶች ሲኖሩ እነሱም፡- ቁሳቁሶችን ተጠቅሞ ማስተማር (ሞዴሎችን አይቶ መናገር የሚያስችሉ ትእይንቶች)፣ ጨዋታዎች፣ ዘፈኖች፣ መገናኛ ብዙሀኖችን መጠቀም (ቴሌቪዥን፣ ራዱዮ)

መ. ቅደም ተከተላዊ መላምት፡- ቅደም ተከተላዊ መላምት ማለት ድርጊቶችን በቅደም ተከተል እያደራጁ በመግለጽ የቋንቋ ክሂሎችን የሚማሩበት ሂደት ነው።

ሠ. ተግባር ተኮር ማስተማር፡- ይህ ዘዴ ተማሪዎች ቋንቋውን ከክፍል ውጭ የሚጠቀሙበትን ተግባር መሰረት ያደረገ የማስተማሪያ ብልሀት ነው።

## 2.3 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች

በመማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልጻሉ። ከዚህ በመቀጠል ጥቂቶችን ለማየት ተሞክሯል።

Celece-Muricia (1991:313) እና Oxford (2001:3) የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት ቀራጮች፣መጽሀፍ አዘጋጆችና መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ገልጸው በተለይም ይዘትን መሰረት ያደረገ፣ተግባር ተኮር የሆነ ወይም ሁሉንም ዘዴዎች ያዋሀደ ዘዴን ተጠቅመው ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ እንደሚችሉ አስረድተዋል።ከዚህ በመቀጠል ስለ ይዘት ተኮር እና ስለ ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ እንመለከታለን።

ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ በዋናነት ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ ነው።በዚህም አማካኝነት ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት እየተማሩ የቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብራሉ።

Celce-muricia (1991፡316) ይዘት ተኮር ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ቅርጽ ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩን መሰረት በማድረግ እንዲረዱት የሚያደርግ አቀራረብ ነው ሲሉ Atkins etal (1996፡223) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች ክሂሎችን አዋህደው እንዲጠቀሙና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ከማድረግም በተጨማሪ የሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ይዘቶች በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማስቻልም ነው ይላሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ይዘት ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ ዋና ዓላማ ቋንቋን በይዘት ማስተማር በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር ባሻገር የተለያዩ ይዘቶችን በጥልቀት እንዲያውቁ የሚያደርግ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራርብ የሚያተኩረው ደግሞ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ተግባር ላይ እየተሳተፉ ቋንቋውን ለመማር የሚያስችላቸው ዘዴ ነው፡፡ይህን ዘዴ በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡ተግባር ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆኑ የቋንቋ ተግባራት የሚሳተፉበትና ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚያዳብሩበትን ተግባራትን የሚያከናውኑበት ዘዴ መሆኑን (Oxford፡2001) ላይ ተገልጿል፡፡

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተግባር ተኮር ዘዴ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በተለያዩ ተግባራትና ክንውኖች እየተሳተፉ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙባቸው የሚያደርግ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ ይህን ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምን እየተገነዘቡ ተግባቦትን የሚያዳብሩበትና መረዳታቸውን የሚያጎለብቱበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ ቀጥሎ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ያለውን ጠቀሜታ እናያለን፡፡

## 2.4 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ

Oxford (2001:2) የቋንቋ ክሂሎች ተናጠላዊ አቀራረብ በጥንታዊው የቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ከመገደብ ባለፈ በሌሎችም ትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርግ እንደነበር በመግለጽ ለዚህም እንደምክንያት የገለጹት ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት የሚቀርጹ ባለሙያዎች የቋንቋ ትምህርቱን በቋንቋ ቅርጽ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ የተነጣጠሉ የቋንቋ ክሂሎችን ማቅረባቸው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የተማሩ ተማሪዎች ሊኖራቸው የሚችለው የቋንቋ እውቀት ደግሞ ስለቋንቋው ከማወቅ ባለፈ በታላሚው ቋንቋ

የመጠቀም ችሎታቸውን እንዳያጎለብቱና ተግባቦታዊ ብቃታቸው በተገቢው መጠን እናዳይጨምር ትልቅ እንቅፋት ሆኗል በማለት ያብራራሉ፡፡ እንዲሁም Mcdonough and Shaw (1992:217) በበኩላቸው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አቀናጅቶ ማቅረብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ዋና ዋና ዋናዎቹ የተማሪውን ፍላጎት ማነሳሳት፣ የተማሪውን ግንዛቤ ማሳደግና የመማር ማስተማርን ሂደትን ማፋጠን መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን ነጣጥሎ ከማቅረብ ይልቅ አቀናጅቶ ማቅረቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎቹ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" የሚል ይጠቀሳል፡፡ ይህ አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ በመፃህፉ ውስጥ ተቀናጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ ተማሪዎች በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በላይ ከቀረቡት ቅኝቶች በመነሳት አጥኚው ክሂሎች በውህደት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ያምናል፡፡ ስለሆነም በመጀመሪያ ስለክሂሎቹ ምንነትና አስፈላጊነት መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ስለማንበብ ክሂል ምንነት፣ የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት፣ ስለመጻፍ ክሂል ምንነትና የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.5 የማንበብ ክሂል ምንነት

የማንበብ ክሂል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አድርጎ ከሚያተኩርባቸው ክሂሎች ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ክሂል ነው፡፡ የክሂሉን ምንነት በተመለከተ Nuttall (1982፣18) "ማንበብ ማለት ፀሀፊው በጽሑፍ ያሰፈረውን መልዕክት በንባብ ወደ ትርጉም የመለወጥ ሂደት ነው" ሲሉ Victoria (2012፣3) ደግሞ "ማንበብ ማለት ውስብስብ በሆነው አለም ውስጥ ለዛሬና ለነገ ስኬት መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ሰዎች የቀረበውን ምንባብ ከተመለከቱ በኋላ ምን እንደተከሰተና በምንባቡ ውስጥ የቀረቡ ምልክቶችን መልዕክት መረዳት ነው" ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በኀሰው (2003፣5) በበኩላቸው "ማንበብ በደራሲውና በአንባቢው

መካከል በርቀት የሚደረግ ውይይት ነው፡፡ ይህም ማለት ጸሐፊው ሀሳቡንና መረጃውን በወረቀት ላይ ያሰፍራል፡፡ አንባቢው ደግሞ በጽሑፍ የሰፈረውን መረጃና ሀሳብ ይቀበላል” ብለዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ትንታኔዎች የምንረዳውም ማንበብ በምንኖርበት አለም ውስጥ በጽሑፍ እና በምልክት የሚገለጹ መልዕክቶችን ለመረዳት የምንጠቀምበት የክሂል ዘርፍ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ መንገድ ጌታቸው (2007፣176) “ማንበብ ከኬሚስትሪ፣ ከፊዚክስ፣ ከልቦለድ፣ ከሳይንስ፣ ከሂሳብ፣ ከታሪክ፣ ከጆግራፊ፣ ከግጥምና ፍልስፍና መጻህፍት ዕውቀትን በመሸመት ከዘመኑ ፍጥነት ጋር አብሮ ለመጓዝ የሚያስችል ክሂል ነው” ብለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ገለፃዎች የምንረዳው የማንበብ ክሂል ምንነት አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እንደሌለውና የትኩረት አቅጣጫቸውም የማንበብ ክሂል ማለት በጽሑፍ የሰፈረውን መልዕክት በዓይን እንቅስቃሴና በአዕምሮ የነቃ ተሳትፎ አማካኝነት በተገቢው መንገድ ተረድቶ ወደ ተግባር የመለወጥ ሂደት እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው ማንበብን ስናነሳ አብሮ የሚነሳው ጉዳይ በጽሁፍ ሰፍሮ የምናገኘውን ምንባብ መልዕክት በተገቢው መንገድ አንብቦ የመረዳትን ሂደት ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ Nunan (1991፣33) “አንብቦ መረዳት ማለት የተፃፉ የቋንቋ ምልክቶችን (ፊደላትን፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓ. ነገሮችን) በመተርጎም መረዳት ነው” ሲሉ Nuttall (1982፣2) “አንብቦ መረዳት ማለት ፊደላትን መለየት፣ መቁጠርና ድምፅን ማፍለቅ ሲሆን በዚህ ክንውን ውስጥ ተፈላጊውን ዕውቀት መጨበጥ መቻል ነው” ብለዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ትንታኔዎች የምንረዳው አንብቦ መረዳት ማለት ከፊደላት ጀምሮ እስከ ሰፋፊ ድርሰቶች ያሉትን አሀዶች እንደምንፈልገው የማንበብ ክሂል ዓላማ መሰረት በተገቢው መንገድ ከተለያየ አቅጣጫ እያገናዘቡ በስፋት አንብቦ መረዳት ያለብን መሆኑን እና አንብቦ መረዳትንም ለማዳበር ለተማሪዎች የተለያዩ ቅንጭጫቢዎችን በማቅረብ የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግና የክፍል ውስጥ ክንውኑን መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

## 2.6 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

አሁን ባለንበትም ሆነ በቀደምት ጊዜያት ንባብ ቋሚ ከሆነው መረጃ ማለትም ከጽሀፊት እውቀት የምንቀስምበት ብቸኛ ክሂል እንደሆነ ይታመናል፡፡ የንባብ ትምህርትን አስፈላጊነት አስመልክተው Williams (1990:19) ሲያስረዱ አንድን ጽሁፍ አንብቦ መልዕክቱን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣ በማንበብ እውቀትን ለመገብየት እንዲሁም ከተለያዩ የንባብ ባህሪያት ጋር ለማስተዋወቅና የንባብ ችሎታን ለማጎልበት የንባብ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ Mcdonough and Shaw (1993:102) ሲገልጹ ንባብ መረጃ ለማግኘት፣ አንድ ነገር መቼና የት እንደተከናወነ ለማወቅ እንዲሁም በጋዜጦች፣በመጽሄቶች የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለመረዳትና ለመዝናናት ወይም ለመደሰት አስፈላጊ ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው ንባብ ለትምህርት ብቻ ሳይሆን ለምናከናውናቸው ተግባራት መረጃ በመስጠት፣ ለመዝናናትና ታሪክን ለማወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ይህ ክሂል እንዲዳብር የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ Lindsay and Knight (2006:74) ሲያስረዱ የንባብን ክሂል ለማዳበር የምናዘጋጃቸው ጽሁፎች የሚከተሉትን ሶስት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡

እነሱም ፡-

- ርዕሰ ጉዳይ፡- የምንመርጠው ጽሁፍ የተማሪዎቻችንን ፍላጎት ያማከለ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ደረጃ፡- ጽሁፉ የተማሪዎችን የእውቀትና የክፍል ደረጃ ያማከለ ሊሆን ይገባል፡፡በውስጡ የሚካተቱ ቃላት፣ አረፍተ ነገሮች ወዘተ. ውስብስብነት ከተማሪዎች የእውቀት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት፡፡
- የጽሁፉ ርዝመት (መጠን)፡- የምንመርጠውን ጽሁፍ ስፋት ወይም መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ጽሁፍን ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ እና ካነበብን በኂላ ለሚሰሩ ተግባራት የምንሰጠው ጊዜ ከአለን አጠቃላይ ጊዜ ጋር ካልተጣጣመ ልናዳብረው የፈለግነውን የንባብ ክሂል ውጤታማ ልናደርገው አንችልም በማለት ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ እንደምንረዳው የንባብ ክሂልን ለማዳበር የማስተማሪያ ፅሁፎችን ትኩረት ሰጥቶ መምረጥና የተማሪዎችን የቀደመ ችሎታ ማወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ነው፡፡

## 2.7 የመፃፍ ክሂል ምንነት

በመስኩ ልምድ ያላቸው ብዙ ምሁራን ስለ ፅህፈት ትምህርት ካላቸው አተያይ በመነሳት መፃፍ (writing) የሚለውን በተለያየ መንገድ ይገልፁታል። እንደ Byrne (1981፡3) አገላለፅ፣ “መፃፍ ማለት የቋንቋውን የድምፅ ምልክቶች በወረቀት ላይ ማስፈር ነው ሊባል ይችል ይሆናል፤ ይሁን እንጅ አቀናጅቶ ከማስቀመጥ ባሻገር በአእምሮ ያለውን ሀሳብ በፅሁፍ መልክ አቀነባብሮ ለአንባቢ የመግለፅም ሂደት ጭምር ነው” ።

መፃፍ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት በተከታታይ መለማመድን የሚጠይቅ የክሂል አይነት መሆኑን Harmer (1993፡16) ፣ Ur (1996፡26) እና Richards (1990፡101) በተመሳሳይ ሁኔታ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ።

Byrne (1981:1) ፣ Norish (1990:6) “የመፃፍ ትምህርት ሂደታዊ እንጅ ቅፅበታዊ ባለመሆኑ ተማሪዎች ረጅም ጊዜን በመውሰድ ልምምድ ማድረግ ይገባቸዋል” ። በማለት የመፃፍ ክሂልን ማዳበር እንደሚችሉ እና የሚያደርጉትም ልምምድ ሂደታዊ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ መፃፍን አስመልክተው ከቀረቡት የምሁራን ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የመፃፍ ክሂል የታላሚውን ቋንቋ የድምፅ ወኪሎች በትክክል ለይቶ በማወቅ በአእምሮ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በወረቀት ላይ የመግለፅ ሂደት መሆኑን ነው። ትምህርቱ በመደበኛ አውድ ውስጥ የሚቀርብ በመሆኑም ክሂሉን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

## 2.8 የመጻፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

የፅህፈትን ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ሰጥተዋል። ለአብነት ያህልም የተወሰኑትን እንመልከት፣ “ሰው በፅህፈት በኩል ይማራል፣ ያስባል፣ እውቀትንም የግል ገንዘቡ ማድረግ ይችላል፤ በተጨማሪም ፅህፈት አዲስ ሀሳብን የማመንጫ ዘዴ በመሆኑ ሀሳብን በሚታይ እና ቋሚ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላለፍ፤ ምሁራን እውቀታቸውን ለማንፀባረቅ፤በማህበራዊ ህይወት ውስጥም ማስታወሻ ለመያዝ፣ደብዳቤ ለመፃፍ እና ሪፖርቶችን ለማቅረብ አስፈላጊ ነው” በማለት Troyka (1990:2) ገልፀዋል።

Raimes (1983:3) "ፅሁፈት ተማሪዎች የሰዋሰው አወቃቀርን እና አባባሎችን እንዲያውቁ ያበረታታል፤ተማሪዎች ሲፅፉ በቋንቋው ላይ የበለጠ እንዲበረታቱና ከተማሩት በላይ ስለ ቋንቋው እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፤ ሲፅፉ የማያውቁት ቋንቋ ቢሆንም እንኳን ጠለቅ ብሎ በመግባት ሀሳባቸውን በቋንቋ ለመግለፅ ጥረት በማድረግ ቀጣይነት ባለው መልኩ አይናቸውን፣ እጃቸውን እና አእምሮአቸውን አቀናጅተው የሚጠቀሙበት ልዩ መንገድ ይሆናቸዋል" በማለት ገልፀዋል፡፡

ፅሁፈት የእውቀት እና የታሪክ መመዝገቢያ በመሆኑ ሊማሩት የሚገባ ጠቃሚ ትምህርት ነው፡፡ Reid (1993:21) "እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፅሁፈትን ማስተማር ማለት መልመጃዎችን ማሰራትና የቃል ፅሁፈት ነበር፤በዘመናችን ግን ፅሁፈት ተግባቦታዊ እና አእምሮአዊ ክሂልን ማበልፀጊያ ሆኖ ተገኝቷል" በማለት ክሂሉን መማር ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያስገነዝባሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ፅሁፈት ተማሪዎች ያላቸውን ስሜት፣አስተሳሰብ እና እውቀት እንዲገልፁ የሚጠቅም መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በበቂ መልኩ የመፃፍ ክሂል እውቀት መኖር ስሜትን፣ አስተሳሰብን እና እውቀትን ለመግለፅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከዚህ በመቀጠል በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.9 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስርና መደጋገፍ

በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል ያለው ትስስር የጠበቀ በመሆኑ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ መጻፍ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሊያሳድግ ይችላል፤ ማንበብ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱን፣ የታሪክ አወቃቀሩንና የጽሁፉን መልዕክት በመገንዘብ ራሳቸው ለሚጽፉት ጽሁፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ይህም ሂደት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር የሚያመለክት መሆኑን Harp, etal (1996) ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም Ruddel (1997) ሲገልጹ ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ ፡፡ የሁለቱ በውህደት መቅረብ የትምህርቱንም ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ ክሂሎቹ የቀደመ እውቀትንና ነባር ልምድን የሚጠይቁ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው በመሆናቸው እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

May (1990) ማንበብ እንደ መፃፍና መናገር ሀሳብ ማደራጀትና መረዳትን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ ክሂሎች የሚጋሯቸው አእምሯዊ ሂደቶች አሉ፡፡ ማንበብ ሀሳብን ከተፃፈ ነገር ለመረዳት ጥረት የማድረግ ሂደት ነው፡፡ መጻፍ ደግሞ መልእክትን በጽሁፍ በማስፈር አንባቢው ሀሳቡን እንዲረዳው የማድረግ ሂደት ነው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች አንብበው የጽሁፉን ሀሳብ ለመተንተን፣ የተገነዘቡትን ለማንፀባረቅ በጥንድና በቡድን ለመረዳዳት ማንበብና መፃፍን በውህደት ሊማሩ ይገባል በማለት ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ማንበብ በሌሎች የተጻፉ ዓረፍተ ነገሮችን በመገልገል የሰዎችን አስተሳሰብ ወደ ጠቃሚ ልምድ፣ መርህና ዕውቀት ስለሚመራ እንደመፃፍ ሁሉ አፍላቂ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ማንበብና መፃፍ የጋራ የሆነ ባህርይ አላቸው ቢባል ምክንያታዊ ይሆናል፡፡ ድርሰት መፃፍ ወደተሻለ የማንበብ ሂደት ሊመራ ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ የሁለትዮሽ ግንኙነት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ግንኙነት በመባል ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም ፀሀፊውም ሆነ አንባቢው የሚጨነቁት ለአንድ ጽሁፍ (ሀሳብ) ትርጉም መስጠት ወይም መረዳት መቻል ላይ እንደሆነም አስገንዝቧል፡፡

ማንበብና መፃፍ ሁለቱም ማቀድን፣ ማቀናበርንና መከለስን የሚሻ የጋራ ባህሪይ ይኖራቸዋል፡፡ ጥሩ ፀሀፊዎች አንድን ጽሁፍ ለማዘጋጀት እቀድ እንደሚነድፉ ሁሉ ጥሩ አንባቢዎችም ማንበብ በሚፈልጉበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ዓላማ በመንደፍ እቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ ከሚያነቡት ጽሁፍ በመነሳትም የራሳቸውን ትርጉም ይገነባሉ፡፡ ስለሚቀጥለው ሀሳብ ወይም ሁነት ይተነብያሉ ባነበቡት ቁጥርም ይከልሳሉ፡፡ ስለሆለም ከእነዚህ ሶስት መሰረታዊ ተመሳስሎዎች በመነሳት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ትስስር አለ ቢባል ምክንያታዊ እንደሆነ (Ruddel, 1997) ገልፀዋል፡፡

May (1990) ተማሪዎቹ ውስብስብ ዐ/ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል፡፡ ይህም የሚያሳየው በክሂሎቹ መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩን ያመለክታል፡፡ አንባቢዎችና ፀሀፊዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመስታዎት ውስጥ እንደሚታይ የአንድ ቁስ አካል ምስልና ራሱን የቁስ አካሉን ያህል ትስስር አላቸው፡፡ አንባቢዎችና ፀሀፊዎች ለማንበብና ለመጻፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁለቱም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ ይኸውም ለማንበብ ወይም ለመጻፍ የራሳቸውን ዓላማ ይነድፋሉ፤ ፍላጎትም ይኖራቸዋል፤ የቀደመ እውቀታቸውን ይጠቀማሉ፤ አእምሯዊ ምስል ይፈጥራሉ፡፡ የፀሀፊዎች ፍላጎት ሀሳባቸውን ለሌሎች በማካፈል መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን ማዝናናት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም

የሁለቱ የመግባቢያ መንገዳቸው የተዘጋጀው በጽሁፍ ነው፡፡ የአንባቢዎች ፍላጎት ደግሞ መረጃ ለማግኘት፣ ሃሳብ ለመጋራት ወይም ለመዝናናት ጽሁፍ ማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ባለጉዳዮች ማለትም ፀሀፊውና አንባቢው በተዘጋጀው ጽሁፍ ይገናኛሉ በማለት አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተመራማሪዎች የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን ገልጸዋል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

## 2.10 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማቅረብ አስፈላጊነት

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ማቅረብና ጠቀሜታውን አስመልክቶ ምሁራን የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን ያቀርባሉ፡፡ Conley (1997) የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ማንበብና መፃፍ በእለት ተእለት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ትርጉም መገንባት የሚያስችሉ የቋንቋ ሂደቶች እንደሆኑም አስገንዝቧል፡፡ በመሆኑም አንዱ ክሂል ሌላውን ለማዳበር መሰረታዊ ጠቀሜታ ያለውና እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ በመሆናቸው ጭምር ነው፡፡

ማንበብና መፃፍ በየእለቱ የሚከወን ተግባቦታዊ ሂደት ነው፡፡ ምክንያቱም በማንበብና መጻፍ መካከል ያለው መስተጋብር የተመሰረተው በተግባቦት ላይ ስለሆነ ነው፡፡ የተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ችሎታ የሚዳብረው በየእለቱ በሚያደርጉት የማንበብና የመፃፍ ልምምድ እንደሆነ Beerdgew (2003) ገልፀዋል፡፡ በዋናነት ሁለቱ ክሂሎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በውህደት ከቀረቡ ክሂሎቹ ሊጎለብቱ ይችላሉ፡፡ የተማሪዎችን አስተሳሰብም ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በጥንድና በቡድን በሚሰሩ ክንዋኔዎች ላይ ሁሉም ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ከአንድ በላይ ክሂልን በሚጠይቅ መልመጃዎች ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ ቋንቋውን በብቃት እንዲገለገሉበት ማድረግ ይቻላል፡፡

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት መቅረብን በተመለከተ Block (1997) ተማሪዎች የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን እንዲተነትኑ፣ እንዲተረጉሙና እንዲገመገሙ ያግዛቸዋል፡፡ እንዲሁም የማንበብና የመፃፍ ፍላጎታቸውን በመጨመር በህይወት ዘመናቸው ከሰዎች ጋር ተግባቦትን

እንዲፈጥሩ፣ እንዲዝናኑ፣ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን በተገቢው መንገድ መማር እንዲችሉ፣ ባህለ ብዙነትን እንዲረዱና ወደፊት ሊከሰቱ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የመተንበይ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሊያግዛቸው እንደሚችል ገልፀዋል።

Kennedey (1994) ማንበብና መፃፍ ጎን ለጎን የሚሄዱ፣ የተያያዙና የሚደጋገፉ ከሆነ ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ማቅረብ ውጤታማ ነው ቢባል ተጠየቃዊ ይሆናል። ክሂሎቹ በቅንጅት ከቀረቡ ደግሞ ተማሪዎቹ የማንበብና የመፃፍ ሂደትን፣ ክህሎትንና ብልሀትን በመረዳት ስኬታማ አንባቢና ጸሀፊ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም አንዱን ክሂል በሌላው መማርን ይለምዳሉ። ከዚህ አንፃር ማንበብና መፃፍን በውህደት ማስተማር ጠቀሜታውን የጎላ ሊያደርገው ይችላል።

በአጠቃላይ በመፃፍ ሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያብራሩ መንገድ ይከፍትላቸዋል። ስለዚህ ይዘት ተኮር የማንበብ ሂደትም ጥራት ያለው ድርሰት ለመፃፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦን ያበረክታል። የማንበብና የመጻፍ እድገት የሚመጣው ሁለቱ ክሂሎች በቅንጅት ሲቀርቡ ነው። በመሆኑም አጥኚው በምሁራኑ ጽንሰ ሀሳባዊ ትወራ መሰረት ክሂሎቹ በውህደት መቅረባቸው የሚያስገኘው ጥቅም የላቀ እንደሆነ በመገመቱ በሙከራዊ ጥናት ለማድረግ አስቧል።

## 2.11 የማንበብና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ማስተማሪያ ዘዴዎች

የማንበብና የመጻፍ ክሂልን በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ። ለአብነት ያህል ጥቂቶችን ለማየት እንሞክራለን።

Block (1997) የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ። አክለውም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና ጽሁፍ ማቀናበርን ሊያጎለብቱ የሚችሉ በርካታ ብልሃቶች እንዳሉም ገልጸዋል። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ያለምንም ብዥታ አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ብልሃቶች ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ማጠቃለል፣ መተንበይና መገመት፣ ምሰላ፣ በጥልቀት ማሰብ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን በተናጠል እንመለከታለን።

**ጥያቄ መጠየቅ፡-** በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠየቅ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ Block (1997) ሲገልጹ ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት ጋር አጣምረው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል፡፡ ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ እውቀትን የማዳበር ክንውን ነው ሲሉ Airasian (1997) በበኩላቸው በቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ሀሳባቸውን በቃላት ጽፈው እንዲገልጹ፣በጥልቀት እንዲያነቡና ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Gary (1995) ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ ምን አውቃለሁ? ለማወቅ የምፈልገው ምንድነው? ያወቅኩት ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ግንዛቤያቸውን ያሳድግላቸዋል በማለት አስረድተዋል፡፡

Block (1997) ጥያቄ መጠየቅን በሚመለከት ያቀረበው ፅንሰ ሀሳብ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት ጋር አጣጥመው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል፡፡ ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ እውቀትን የማዳበር ክንውን ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች ሲያነቡና ሲጽፉ በርካታ ጥያቄዎችን በጠየቁ ቁጥር ትምህርቱን የመረዳት ችሎታቸው እየጎለበተ ሊሄድ እንደሚችል አጥኚው ያምናል፡፡

**ማብራራትና መተርጎም፡-** አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሃቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም ተጠቃሾች እንደሆኑ Block (1997) ያስረዳሉ፡፡ በእነዚህ ብልሃቶች አማካኝነት ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመጻፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ ጥረት የሚደረግባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያችሉበት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ Gary (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ በሚዘጋጁት የውይይት ክንዋኔዎች ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ የሚገፋፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ከእነዚህ ክንዋኔዎች በኋላ ተማሪዎቹ ስለጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፣ ትርጉም ይሰጣሉ፣ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይመረምራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ስላነበቡት ወይም ስለጻፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት ከቻሉ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ይዘት በቂ መረጃ

ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ ብልሃት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

**መተንበይና መገመት** (Inferring and predicting)፡- ይህን የማስተማሪያ ብልሃት በተመለከተ Block (1997) መገመት የሚባለው አንባቢው እያነበበ እያለ ቀጥሎ የሚመጣውን ሁነት ድርጊት ወይም ሀሳብ የሚጠቁምበት ልዩ የመገመቻ ስልት ነው፡፡ መተንበይ ግን ከጽሁፍ አንብቦ የሚገኘን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቁምበት ልዩ ስልት ነው:: እንዲሁም Barrs (2000) መተንበይን በሚመለከት የሰጡት ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ  አንድን ጽሁፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገጸባህሪያትን ማንነት፣ ድርጊት፣ ሴራ በመረዳት ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ጽሁፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመጻፍ የሚገልጹበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

**ማጠቃለል** (Summarizing)፡- ማጠቃለልን በሚመለከት Block and Mangeri (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ በአእምሯቸው የታሰባቸውን በጽሁፍ የሚያጠቃልሉ ከሆነ የማስታወስ ወይም እውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸው 16% ያህል እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ማጠቃለል ንባብን በዕለት ተዕለት ህይወት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሁፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችላቸውን ብልሃቶች መማር ይኖርባቸዋል፡፡

**ምሰላ** (Imaging): - አንባቢው በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ ባሉት ገጸ ባህሪያት፣ ድርጊትና ሁነቶች በአእምሮ ምስል የሚቀረጽበት ስልት ምሰላ ይባላል፡፡ ይህንንም ለአንባቢዎችና ለጸሀፊዎች ማስተማር አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ በንቃት እንዲያነቡ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡ይህም ብልሃት በህይወት ውስጥ ስሜታዊ ገጠመኞችን ከአመለካከትና ከተጠየቃዊ ገጠመኞች ጋር ለማቀናጀትም ይጠቅማል፡፡ በቋንቋው ሂደት ውስጥ በራሱ ሳይሆን የቋንቋው ሂደት በሚፈጥረው ገጠመኝ ውስጥ ጠልቆ ለመግባት ያስችላል፡፡ ምስል ከሳች ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማድረግ እያበቡ እያሉ በአእምሯቸው የመጣውን ምስል እንዲናገሩ በማድረግ እያነበቡ እያሉም ምስላቸው እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ በመጠየቅም ማለማመድ እንደሚቻል Block (1997) አስረድተዋል፡፡

**በጥልቀት ማሰብ፡-** የጥልቅ አስተሳሰብ ብልሀት አንብቦ ለመረዳትም ሆነ ጽሁፉን ለማቀናበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው Unrau (2004) ያስረዳሉ፡፡ እንደባለሙያው ማብራሪያ ጥልቅ አስተሳሰብ በተማሪዎች ውጤት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ አለው፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን የማንበብም ሆነ የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ አይነተኛ ብልሃት ነው በማለት አብራርተዋል፡፡ ይህንንም ብልሃት ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ትልቁ ስራ ተማሪዎችን ግለ ግምገማና ግለ ቁጥጥር ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በዋናነት ይህንን ሀሳብ ተረድቸዋለሁ ፡፡ ይህንን ሀሳብ ደግሞ አልተረዳሁትም፡፡ ስለዚህ ምን ማድረግ አለብኝ? ብለው እራሳቸውን መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ወይም ግለ ቁጥጥር የሚያደርጉት በማንበብ ላይ እያሉና ካነበቡ በኋላም ሊሆን ይችላል፡፡ የንባባቸው ቁም ነገር ግን ለማንበብ ብቻ ሳይሆን አንብቦ ለመረዳት መሆን ኖርበታል፡፡ በዚህም መሰረት ተማሪዎቹ እያንዳንዱን አንቀጽ በጥሞና በማንበብ ብዥታ የሚፈጥር ሃሳብ ካለ በጥልቀት በመመርመር አእምሮአዊ ብቃታቸውን በመጠቀም አብራርተው በመጻፍ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡

Smith (1983) ጽሁፍን በማቀናበሩ ረገድ ያቀረቡት ጽንሰ ሀሳብ ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ ጠንካራ ይዘት ያለው ጽሁፍ ለማቅረብ አእምሮአቸውን ማሰራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ተግባር በማከናወን ሂደት ተማሪዎቹ ራሳቸውን የሚጠይቋቸው በርካታ መሰረታዊ ጥያቄዎች መኖራቸውን አክለው አስረድተዋል፡፡

## 2.12 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማቅረብ ዘዴ ውስጥ የመምህሩ ሚና

የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው ይቀርቡ ዘንድ መምህራን ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የታቀደው አላማ ከግብ እንዲደርስ መምህራን የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ብልሀቶችን ተጠቅመው በማስተማር ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ እንዲገለገሉና የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ከእነሱ የሚጠበቀውን ሚናና ተግባር መወጣት አለባቸው፡፡

Gower and Walters (1983:154) እንደገለጹት የመማር ማስተማር ሁኔታውን ተቆጣጥረው በተማሪዎች ዘንድ መስተጋብር (interaction) እንዲኖር የማድረግ ሀላፊነት የመምህራን ተግባር ነው፡፡ መምህራን ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ከተወጡ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ መጠቀም እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ Burns (1999:3) መምህራን ተማሪዎችን ማበረታታትና ለመማር ማስተማር ምቹ የሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

እንዳለባቸው በመግለጽ ይህን ተግባራዊ ለማድረግም የክሂሎችን ትምህርት ተጨባጭነት ባላቸው ክንውኖች አቀናጅተው ማቅረብና ተናጠላዊ የክሂሎችን ትምህርት ማስወገድ አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Squire (1983) በበኩላቸው ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ብቃት ያለው የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂል ትምህርት እንዲያገኙ በጥንቃቄ የታቀደ ክንውንና ልምምድን እንደሚሹ ገልጸው መምህራንም በቋንቋ ክንውን ወቅት ክሂሎችን እርስ በርስ አቀናጅተው ለማቅረብ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ያስረዳሉ፡፡

Byrne (1981:114) መምህራን እንደየክፍሉ ሁኔታ የተለያዩ ዘዴዎችንና ብልሀቶችን ተጠቅመው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው ቢያቀርቡ የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያሟሉ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የመጻፍ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን እንዲያደራጁ በማድረግ የሚገፉፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ ክንዋኔውም ቀላልና የተወሰነ ማስታወሻ መያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ሊሆን ይችላል፡፡ በመጨረሻም መምህራኑ የተማሪዎችን ስራ ለመገምገም ዝርዝር መልሶች የሚያስፈልጋቸው ይዘት ተኮር ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ጥያቄዎችም ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ሁሉም ክንዋኔዎች ከንባብ ጋር የተቆራኙ የመጻፍ ተግባሮች በመጻፍ ለማንበብ ምላሽ መስጠት የሚያስችሉና ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gary 1995)፡፡

በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳናቱ የቀረቡት ጥናታዊ ግኝቶች አንብቦ የመረዳትና የመጻፍን ክሂሎች በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች የማይነጣጠሉ፣ የሚደጋገፉና ትስስር ያላቸው መሆኑንም አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ክሂሎቹን በቅንጅት ተከታታይ በሆነ መልኩ ማቅረብ ከተቻለ የተማሪዎችን በራስ የመተማመንን ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው፣ የተማሪዎችን ግንዛቤ እንደሚያሳድግላቸውና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያግዛቸውም ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ጥናቶች የሚያመለክቱት ክሂሎቹን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የራሱ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ

በውጭ ሀገር የተከናወኑ ጥናቶች በዚህ አውድ ቢተገበር ተመሳሳይ ውጤት ይመጣ ይሆን? የሚል ጥያቄ በአጥኚው አዕምሮ እንዲጭር አድርጎታል፡፡

## 2.13 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሩ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የታሰቡ ቀደምት ስራዎችን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ጥናታዊ ስራዎቹ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

እሸቴ (2003) "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና" በሚል ርዕስ በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ማረጋገጥ ሲሆን በወረታ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራዊ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ካላቸው ትስስርና ዝምድና አንጻር በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ በውህደት ቢቀርቡ ለክሂሎቹ መጎልበት የላቀ ሚና እንዳለው አሳይቷል፡፡

የእሸቴ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በርእስም ሆነ በአላማ ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ከተመራማሪው ጥናት በአጠናን ዘዴው፣ በፈተና አዘገጃጀትና አስተራረም ሂደቱ፣ በክፍል ደረጃ፣ በተጠኝዎች ብዛት፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል፡፡

ትዝታ (2003) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር አተገባበርና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የነበረውም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብና የተማሪዎችን አቀባበል መፈተሽ ነው፡፡ በተገኘው ውጤትም ክሂሎችን አቀናጅተው የሚያቀርቡ ጥቂት መምህራንና ክሂሎችን አቀናጅቶ የማያቀርቡ በርካታ መምህራን እንዳሉ የታወቀ ሲሆን የተማሪዎቹም የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀባበል ጥሩና መጥፎ መሆን እንደ

መምህራኑ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ጥሩና መጥፎ መሆን የተወሰነ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

በመሆኑም የተመራማሪዋ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብና የተማሪዎችን አቀባበል መፈተሽ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይህ ጥናት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራዊ ጥናት የሚያረጋግጥ በመሆኑ በጥናቱ ርዕስ፣ ዓላማ፣ በአጠናን ዘዴው፣ በፈተና አዘገጃጀትና አስተራረም ሂደቱ፣ በክፍል ደረጃ፣ በተጠኝዎች ብዛት፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል፡፡

አታኽልቲ (1998) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማም የቋንቋ ክሂሎችን እንዴት እንዳቀረቧቸው የሚቃኝ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም መምህራኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንደማያቀርቧቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የአታኽልቲ ጥናት የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ላይ ሲሆን ይህ ጥናት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራዊ ጥናት የሚያረጋግጥ በመሆኑ በርእስም ሆነ በዓላማ በእጅጉ ይለያል፡፡ በተጨማሪም በክፍል ደረጃ፣ በጥናቱ አካላዮች፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ይለያል፡፡

ጥላሁን (2003) ዓ.ም "የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብና አተገባበር" በሚል ርእስ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ አላማም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥ ክሂልን ከመናገር ክሂል ጋር ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚተገበር ቅንጅታዊ አቀራረብን ይጠቀማሉ? ከተጠቀሙስ ከቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ አንጻር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ሲሆን በጥናቱ የተደረሰበት ውጤትም መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማቀናጀት ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ፣ መምህራን ከተማሪዎች ችሎታ፣ ዳራና ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ይዘቶችን እንደማያቀርቡ፣ ከመማሪያ መጽሀፍ በተጨማሪ ለአላማው ተስማሚ የሆኑ አጋዥ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ በጥናቱ አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ጥናት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራዊ ጥናት የሚያረጋግጥ በመሆኑ ከጥላሁን ጥናት ጋር በርእስም ሆነ በዓላማ በእጅጉ ይለያል፡፡ በተጨማሪም በክፍል ደረጃ፣ በጥናቱ አካላዮች፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ይለያል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ቀደም ሲል በዝርዝር ከእያንዳንዱ ጥናት ጋር በጠቀስኩት መልኩ የአታክልቲ (1998)፣ የትዝታ (2003) እና ጥላሁን ከበደ (2003) ዓ.ም ጥናቶች በስያሜ፣ በጥናቱ ዓላማና በአጠናን ዘዴው፣ በፈተና አዘገጃጀትና አስተራረም ሂደቱ፣ በክፍል ደረጃ፣ በተጠኝዎች ብዛት፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት ያላቸው ሲሆን ከእሸቴ (2003) ጥናት ጋር በስያሜ የሚመሳሰል ሲሆን በጥናቱ ዓላማና በአጠናን ዘዴው፣ በፈተና አዘገጃጀትና አስተራረም ሂደቱ፣ በክፍል ደረጃ፣ በተጠኝዎች ብዛት፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም ጥናቱ የተከተለው ከፊል ሙከራዊ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ይህም የሁለት ቡድን የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና አጠናን ስልት (Two Groups Pretest-Posttest design) በስራ ላይ አውሏል፡፡ የዚህ ምርምር ንድፍ ፅንሰ-ሀሳብ ሁለት ተጠኝ ቡድኖች ማለትም የሙከራ ቡድን (Experimental Groups) እና የቁጥጥር ቡድን (Control Groups) ክሂሎቹን በተናጠል የተማሩና ክሂሎቹን በቅንጅት የተማሩ ሁለት ቡድኖች በሚወስዱት ተመሳሳይ ፈተና የሚያሳዩት የውጤት ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማሳየት መሆኑን Koule (1996) ይገልፃሉ፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የዚህ ንዑስ ክፍል አላማ የጥናቱ ናሙና እንዴት እንደሚመረጥረጥ ማስረዳት ነው፡፡
ስለሆነም የጥናቱ ቦታና ተሳታፊዎች በምን አይነት ዘዴ እንደተመረጡ ያብራራል፡፡

### 3.2.1 የምርምር ቦታና የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ሸዋ ዞን በሞጆ ከተማ አስተዳደር በሚገኘው ቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በሞጆ ከተማ አስተዳደር ስር ቀርሳ፣ ዋርካ፣ ኢ.ፊ ቦሩ እና ሰዮ የሚባሉ አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ከእነዚህ ትምህርትቤቶች መካከል ቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በአመቺ የናሙና ስልት ተመርጦ በጥናቱ ተካቷል፡፡ የዚህም ምክንያት አጥኚው ችግሩን ያስተዋለው በዚህ ትምህርት ቤት ላይ በመሆኑና በመሰል ትምህርትቤቶች ላይ ተመሳሳይ ችግር ይኖራል በሚል የሃሳብ መነሻነት ነው፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ለናሙናነት የተመረጠው ቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ9ኛ -12ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን ከ9ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ያሉት ደረጃዎችን በቀላል

እጣ ንሞና በመለየት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ተመርው የጥናቱ አካላይ ሆነዋል፡፡ እነዚህ የክፍል ደረጃዎች በእጣ የተመረጡበት ምክንያት የጥናቱን አስተማማኝነት ለመጠበቅ ሲባል ተማሪዎቹ ሀገር አቀፍ ፈተና ስለማይወስዱ ትምህርት ጨርሰናል የሚል አስተሳሰብ ስለማይኖርና እስከመጨረሻው የትምህርት መዝጊያ ጊዜ ስለሚኖሩ በቂ መረጃ ይሰጣሉ ከሚል እሳቤ ነው፡፡ 12ኛ ክፍል ያልተካተተበት ምክንያት ሀገራዊ ፈተና ተፈታኝ በመሆናቸው አመቱን ሙሉ የማይቆዩ ከመሆናቸውም በላይ ወደ ቀጣዩ የትምህርት እርከን መሸጋገሪያ ላይ በመገኘታቸው ለጥናቱ ትኩረት ላይሰጡት ይችላሉ በሚል ምክንያት ነው፡፡

## 3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የተማሪዎች ናሙና አመራረጥን በተመለከተ ከላይ በቀረበው ትምህርትቤት በ2015 ዓ.ም በ11ኛ ክፍል ለመማር የተመዘገቡትን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ 275 ተማሪዎች በ8 የመማሪያ ክፍሎች ተደልድለው ትምህርታቸውን እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ተማሪዎች መካከል 131 የሚሆኑት አፋን ኦሮሞ ተማሪዎች በመሆናቸው አማርኛ ትምህርት አይማሩም፡፡ አማርኛ የሚማሩት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 144 ናቸው፡፡ ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ማካተት ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እና ጊዜ ስለሚጠይቅ፣ ጥናቱ በሙከራ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና የጥናቱን አስተማማኝነትና ተገቢነት ለመጠበቅ የተማሪዎችን ቁጥር መወሰን ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም የ144 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ አይቻልም፡፡ በዚህም መሠረት ከ144 ተማሪዎች ውስጥ11ኛ A እና 11ኛ D ክፍል የሚማሩ 68 ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በመቀጠልም የ11ኛ A ክፍል ተማሪዎች በሙከራዊ ቡድን የ11ኛ D ክፍል ተማሪዎች በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ ተመድበው ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

ሰንጠረዥ 3.1፡- ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች መረጃ

| ተ.ቁ | የመማሪያ ክፍል | ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | 11ኛ A | 18 | 16 | 34 |
| 2 | 11ኛ D | 19 | 15 | 34 |
| | ድምር | 37 | 31 | 68 |

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አላማ እውን ለማድረግ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተናና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በመሆኑም አዘገጃጀታቸውና አቀራረባቸው በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 3.2.1 ፈተና

በጥናቱ ዓላማ መሰረት የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች አይነት፣ አዘገጃጀትና አተገባበሩ በቅደም ተከተል ቀርቧል፡፡

#### 3.2.1.1 ቅድመ ትምህርት ፈተና

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ ተማሪዎች ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የማንበብና የመጻፍ ችሎታቸውን ዳራና የግንዛቤ ደረጃቸው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ ለጥናቱ ጠቃሚ ነው፡፡ የቅድመ ፈተና ውጤቱ ሁለት ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

የመጀመሪያው በሁለቱ ቡድኖች መካከልና በቡድኖቹም ውስጥ ከመነሻው ላይ ጉልህ የሆነ ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ፋይዳው በቡድኖቹ መካከልና በቡድኖቹ በራሳቸው ውስጥም ቢሆን መነሻ ላይ የነበራቸውን ክህሎት ደረጃ ከቀረበው ሙከራዊ ጥናት (ከተሰጠው ትሪትመንት በኋላ ያለውን ለውጥ ለማየት ከድህረ ሙከራው ፈተና ጋር በንጽጽር ለማየት ነው)፡፡

በመሆኑም አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታቸውን የሚለካ ቅድመ ትምህርት ፈተና በአጥኝው ተዘጋጅቷል፡፡ የፈተናውን ጥራትና ተገቢነት ለማረጋገጥ በአማካሪው ታይቶና ተገምግሞ ማሻሻያ ተደርጎበት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ (የቅድመ ትምህርት ፈተናውን በአባሪ አንድ ይመልከቱ)፡፡

የቅድመ ትምህርት ፈተናው ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያ ክፍል ተዘበራርቀው የተቀመጡ አስር አረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተል በማስያዝ አንድ የተሟላ አንቀጽ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ሲሆን እያንዳንዱ አንድ ማርክ እንዲይዝ ተደርጎ አጠቃላይ አስር ማርክ ይዟል፡፡

ሁለተኛው የፈተና ክፍል ከፍቅር እስከመቃብር መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ቅንጫቢ ጽሑፍ ነው፡፡ ይህም ቅንጫቢ ተማሪዎቹ የምንባቡን መልክት መገንዘባቸውን መለካት ያስችል ዘንድ በምንባቡ ውስጥ ሊመለሱ የሚችሉ የሂደት ጥያቄዎችን በማካተት በሶስት ንዑሳን ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ምንባቡን

ከማንበባቸው በፊት የምንባቡን ርእስ በመመልከትና ከቀደመ ልምዳቸው በመነሳት እያብራሩ እንዲጽፉ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

በመሆኑም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ሁለት ማርክ በመስጠት አራት ማርክ ይዟል፡፡ ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ምንባቡን እያነበቡ ቀጣዩን ከታሪክ ሂደትና ከቀደመ እውቀት ተነስተው በመገመት የሚመልሷቸው ዘጠኝ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዱ ሶስት ነጥብ በመስጠት ሃያ ሰባት ማርክ ይዟል፡፡ ሶስተኛው ንዑስ ክፍል የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የምንባቡን ታሪክ መሰረት በማድረግ የሚመለሱ ሲሆን ለእያንዳንዱ ሁለት ማርክ በመስጠት አራት ማርክ ይዟል፡፡

ሶስተኛው የፈተና ክፍል በሰንረዥ የቀረበን የዶክተር ሀዲስ አለማየሁ የሕይወት ታሪክ በማቀናጀት እንደገና እንዲጽፉ የሚያዝ ሲሆን አምስት ማርክ ይዛል፡፡ በአጠቃላይ የቅድመ ትምህርት ፈተናው ሃምሳ ማርክ የያዘ ሲሆን የመረጃዎቹን አስተማማኝነት ለመጠበቅ ሲባል የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ተራርቀው በመቀመጥ ተፈትነዋል፡፡ ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ 1፡30 ሲሆን ተማሪዎቹ ፈተናውን ሰርተው እንደጨረሱ የፈተናው የመልስ ወረቀት በአጥኝው ተሰብስቧል፡፡ ከዚያም በተዘጋጁት የማረሚያ መልሶች መሰረት ፈተናው በሶስት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርሟል፡፡ ውጤት አሰጣጡ ሶስት የተለያዩ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት ተደምሮና ለሶስት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ነጥብ ዋና ውጤት ተደርጐ ተወስዷል፡፡ (የተማሪዎቹን የቅድመ ፈተና ውጤት በአባሪ ስድስት “ሐ” ይመልከቱ)

### 3.2.1.2 ድህረ ትምህርት ፈተና

ድህረ ትምህርት ፈተና (Post-test) ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ሁለት አቀራረቦች ማንበብና መጻፍን በመማራቸው ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ መበላለጥ ስለመታየት አለመታየቱ መረጃ ማስገኘት ነው፡፡

ከድህረ ትምህርት ፈተናው ተገቢውን መረጃ መሰብሰብ እንዲቻልና የፈተናውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ተመሳሳይ ይዘት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ፈተናዎቹ በጥያቄ ቁጥር ብዛት፣ በአቀራረብ፣ በይዘትና በአወቃቀራቸው ተመሳሳይ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ቡድኖቹ በተለያየ ሁኔታ በየግላቸው የተዘጋጀላቸውን ትምህርት በአጥኚው ከተማሩ በኋላ በትምህርት አቀራረብ ልዩነት ምክንያት የችሎታ ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በመሀኑም ለሙከራና

ለቁጥጥር ቡድኖቹ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታቸውን የሚለካ ድህረ ትምህርት ፈተና በአጥኚው ተዘጋጅቷል። ፈተናው በአማካሪው ታይቶና ተገምግሞ ማሻሻያ ተደርጎበት ተግባር ላይ ውሏል። (የድህረ-ትምህርት ፈተናውን በአባሪ ሁለት ይመልከቱ)።

የዘርፉ ባለሙያዎች ሙያዊ ግምገማና አስተያየት መሰረት በማድረግም የፈተናውን ተገቢነት (Validity) ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። የፈተናውን አስተማማኝነት (Reliability) ለማረጋገጥ የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆኗል። ውጤቱም በአግባቡ ተሰልቶ አስተማማኝነቱ 0.995 ሆኗል። ከዚያም በኋላ በጥናቱ ተሳታፊዎች ልክ ፈተናው ተባዝቶ ተዘጋጅቷል።

የፈተናውን ውጤት አስተማማኝነት ለመጠበቅ ሲባል በአንድ ወንበር ላይ አንድ ተማሪ እንዲቀመጥ ተደርጓል። በዚህ መልኩ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታቸውን፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን፣ የቃላትን ትርጉም ከአውዳቸው መረዳት መቻላቸውን፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀራቸውን፣ የአንድን ጽንሰ ሀሳብ ትርጉም መገንዘባቸውን፣ የጥያቄውን ምላሽ በተገቢው መንገድ መግለጻቸውን እንዲሁም በጥያቄው ውስጥ ያለውን መረጃ በውል መረዳታቸውን በሰጧቸው መልሶችና ገለጻዎች እየታዩ ታርመዋል።

የውጤት አሰጣጡን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለመጠበቅ ሲባል በትምህርትቤቱ ሶስት የአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን እንዲታረም ተደርጓል። የአስተራረም ሂደቱም ከፈተና ወረቀቱ ላይ የተማሪዎች ስም ሳይጻፍ መለያ ኮድ ተሰጥቷል። በዚህ መሰረት የእያንዳንዱ ተማሪ የፈተና ወረቀት በሶስት ኮፒ ተባዝቶ ለሶስቱም መምህራን እንዲደርስ ተደርጓል። ሶስቱ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት ተደምሮና ለሶስት ተካፍሎ የተማሪው አማካይ ነጥብ ተደርጎ ተመዝግቧል። (የተማሪዎቹን የድህረ ፈተና ውጤት በአባሪ ስድስት “መ” ይመልከቱ)

ሰንጠረዥ 3.2፡- የተማሪዎቹን ፈተና ያረሙ መምህራን መረጃ

| ተ.ቁ | የመምህራኑ መለያ | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የተመረቁበት የት/ት አይነት | | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | አብይ | ንዑስ | |
| 1 | መምህር አንድ | ሴ | ዲግሪ | አማርኛ | - | 12 አመት |
| 2 | መምህር ሁለት | ሴ | ዲግሪ | አማርኛ | - | 11 አመት |
| 3 | መምህር ሶስት | ወ | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 16 አመት |

### 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

ከፈተና በተጨማሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ የዋለው ቃለ መጠይቅ ነው። ቃለ-መጠይቆቹ በሙከራው ቡድን ውስጥ ለተካተቱ ስድስት ተማሪዎች የቀረቡ ሲሆን ቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ተብለው በሁለት ከፍለው ተዘጋጅተዋል። የቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቁ ዓላማም ተማሪዎቹ ከሙከራ ትምህርቱ በፊት የአንብቦ መረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን በሚመለከት ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን የድህረ ቃለ መጠይቁ ዓላማ ደግሞ በፈተና የተገኘውን መረጃ ለመደገፍ አገልግሎት ላይ ውሏል። ቃለ መጠይቆቹ በመስኩ የተካሄዱ የምርምር ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ በአጥኚው ተዘጋጅተው የአማካሪ መምህር ማስተካከያና አስተያየት ተጨምሮበት ተግባር ላይ ውሏል። (የተማሪዎቹን ቃለ-መጠይቅ በአባሪ አምስት ይመልከቱ)

## 3.3 የትምህርት እቅድ

ጥናቱን በተገቢው መንገድና ጊዜ መከናወን የሚቻለው የትምህርት እቅድ ሲዘጋጅ ነው። በመሆኑም የትምህርት ትግበራው ሂደት በስርትና ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኑ እለታዊ የትምህርት እቅድ ተዘጋጅቷል። እቅዱ በአማካሪው ከተገመገመና ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ ለሙከራ ቡድኑ አገልግሎት ላይ ውሏል። በሌላ በኩል የቁጥጥር ቡድኑ የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሚያዘጋጁበት የትምህርት እቅድ መሰረት እለታዊ የትምህርት እቅድ እየተዘጋጀ ተግባራዊ ተደርጓል።

ለሙከራ ቡድኑ የትምህርት አሰጣጠጥና ትግበራው አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያገለግሉ ብልሀቶችን በጥልቀት ማሰብ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማንፀባረቅና ዳራዊ እውቀትን መጠቀም፣ ማጠቃለል፣ ማሳጠር፣ መገመትና ምሰላን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል። በእለታዊ የትምህርት እቅዱ መሰረት (ከየካቲት 1 እስከ መጋቢት 30) ድረስ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ተማሪዎች የተዘጋጁትን መልመጃዎችና ክንዋኔዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን በየክፍለጊዜው እንዲያከናውኑ ተደርጓል።

## 3.4የመማሪያ ምንባቦችና መልመጃዎች አዘገጃጀት

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር አጥኚው ለጥናቱ ይመጥናሉ ያላቸውን የተለያዩ ልቦለዶችን፣ ግጥሞችን፣ ተረቶችንና ስነ-ቃሎችን በመምረጥ ተዘጋጅቷል፡፡ ማስተማሪያው የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ የቀደመ እውቀት፣ ዝንባሌያቸውን፣ ባህላዊ ዳራቸውን ወዘተ. ግምት ውስጥ በማስገባት ከተዘጋጀ በኋላ ተገቢነቱን በተመለከተ የአማካሪው አስተያትና ማሻሻያ ተደርጎበት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

ለሙከራ ትምህርቱ የተዘጋጀው መማሪያ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በማዋሃድ የሚያለማምዱ መልመጃዎችና ክዋኔዎች እንዲካተቱበት ተደርጓል፡፡ የተመረጡት የማስተማሪያ ርእሶችም ያልተንዛዙ፣ ተግባቦትን የሚያጠናክሩ፣ ወቅታዊ የሆኑ፣ ጥንታዊ ቢሆኑም በወቅቱ ተደማጭነት ያላቸው፣ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሱና ከዳራዊ እውቀታቸው ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ (ለሙከራ ቡድኑ ለማስተማሪያነት የቀረቡ የምንባብ ትምህርቶችን በአባሪ ሶስት ይመልከቱ)

## 3.5 የትምህርቱ አሰጣጥና የትግበራው ሂደት

ትምህርት አንድ፡- ከዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስ" መጽሀፍ ላይ የአበዳሪዋ ጫና በሚል ርዕስ አንድ ቅንጫቢ ቀርቧል፡፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል "የአበዳሪዋ ጫና" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል አንብበዋል፡፡ ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻም ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ፅፈዋል፡፡

ትምህርት ሁለት፡- ከከበደ ሚካኤል "የቅኔ ውበት" መጽሀፍ ላይ "የክፋት ተጋቦት" የሚል ግጥም ቀርቧል፡፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል፡፡ የታደላቸውን ግጥም ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል አንብበዋል፡፡ የግጥሙን አንብበው ያገኙትን ቁም ነገር በጽሁፍ ገልፀዋል፡፡ ከዚያም የግጥሙን ሃሳብ በአጭሩ በዝርው ጽፈዋል፡፡ የፃፉትን ሀሳብ ከቡድን

አጋራቸው ጋር በየተራ በማንበብ ከተወያዩበት በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡

ትምህርት ሶስት፡- ማንተጋፍቶት ስለሺ (2016) "ውቅያኖስ በድንኳ ፕላኔት፣ፕሉቶ" የሚል ጽሁፍ ቀርቧል፡፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል፡፡ "ውቅያኖስ በድንኳ ፕላኔት፣ፕሉቶ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል አንብበዋል፡፡ ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል፡፡ ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡ በመጨረሻም ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ በአጭሩ በጽሁፍ እንዲገልጹ ተደርጓል፡፡

ትምህርት አራት፡- "አስተዋፅኦ" በሚል ርዕስ ለቀረበላቸው ቅድመ ንባብ ጥያቄ ተገቢውን መልስ በፅሁፍ ሰጥተዋል፤ የቀረበላቸውን አስተዋፅኦ/ቢጋር በጥሞና አንብበዋል፡፡ በመቀጠልም በቢጋሩ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች ገጣጥመው የተሟላ ድርሰት ጽፈዋል፡፡ የፃፉትን ድርሰት ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየርና በመገማገም አስተያየታቸውን በጽሁፍ ተሰጣጥተዋል፡፡ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡

ትምህርት አምስት፡- "ምሳሌያዊ አነጋገር" በሚል ርዕስ ትምህርት ቀርቦላቸዋል፡፡ ለቀረቡላቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች በፅሁፍ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡ የሰጡት ፍቺ ትክክል መሆኑን ከጓደኞቻቸው ጋር በመቀያየር አስተያየታቸውን በጽሁፍ ተሰጣጥተዋል፡፡ የቀረቡላቸውን ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮች አሟልተዋል፡፡ በመቀጠል ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየርና በመገማገም አስተያየታቸውን በጽሁፍ ተሰጣጥተዋል፡፡ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡

ትምህርት ስድስት፡- የነገ ናፍቆት (ገፅ 80-83) "መኖር ሰው ገደለ" በሚል ርዕስ ቅንጫቢ ጽሁፍ ቀርቦላቸዋል፡፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል፡፡ "መኖር ሰው ገደለ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል አንብበዋል፡፡ ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል፡፡ ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ

ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡ በመጨረሻም ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ በአጭሩ በጽሁፍ እንዲገልጹ ተደርጓል፡፡

ትምህርት ሰባት፡- ዳንኤል ክብረት "ዋንጫውና ጠጁ" በሚል ርዕስ ቅንጫቢ ጽሁፍ ቀርቦላቸዋል፡፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል፡፡ "ዋንጫውና ጠጁ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል አንብበዋል፡፡ ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል፡፡ ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ፅፈዋል፡፡

ትምህርት ስምንት፡- ግሩም አበጀ "ንጉሱና ሞት" በሚል ርዕስ ከድረ ገፅ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ ቅንጫቢ ጽሁፍ ቀርቦላቸዋል፡፡ ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል፡፡ "ንጉሱና ሞት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል አንብበዋል፡፡ ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል፡፡ ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ጽፈዋል፡፡

በአጠቃላይ ከምንባቦቹ በመጀመሪያ፣ በመካከልና በመጨረሻ ላይ የተካተቱት ጥያቄዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት አዋህዶ ለማስተማር የሚረዱና ተማሪዎችን እንዲተነብዩ፣ እንዲያብራሩ፣ ምስል ከሳች ቃላትን ለይተው እንዲያወጡ፣ እንዲጠይቁና ማጠቃለል እንዲችሉ ታስቦ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ የተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ ለሁሉም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች እንዲዳረስ ሆኖ በየክፍለጊዜው እየታደለ ትምህርቱ ተሰጥቷል፡፡

ቁጥጥር ቡድኑ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መጽሀፍ፣ በተለመደው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ፣ ተማሪዎቹ ከደረሱበት ርዕስ በመቀጠል ክሂሎቹን በተናጥል በአጥኚው እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በመደበኛው የትምህርት መርሃ ግብር ትምህርቱን ለመስጠት አመቺ ባለመሆኑ ከተማሪዎቹ ጋር በመነጋገር የሙከራ ቡድኑ ማክሰኞ ማክሰኞ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ ሀሙስ

ሀሙስ ለስምንት ክፍለጊዜያት (ለሁለት ወር) ከመደበኛው የትህርት መርሃ ግብር በኋላ ከ9፡30 እስከ 11፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ በአጥኚው እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

## 3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በመጀመሪያ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች ልዩነቱን ለማወቅ በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለሙከራ ቡድኑ የተሰጠው የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች የተገኘውን ለውጥ ለማወቅ በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቷል፡፡ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ ከሙከራው ትምህርት በፊት ክሂሎቹን በመገልገል ረገድ የግንዛቤ ደረጃቸው ምን ያህል ልዩነት እንዳለው ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የሁለቱን ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቶና ተነፃፅሮ ተተንትኗል፡፡ በመጨረሻም በሁለቱ ቡድኖች መካከል የታየው የችሎታ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና በቡድኖቹ መካከል ያለውን ልዩነት መለካት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የድህረ ትምህርት ፈተናውን ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቶና ተነፃፅሮ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንተናና የግኝት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ ማሳየት መሆኑ በምዕራፍ አንድ ተገልጿል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ከቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች እንዲሁም ከተማሪዎች ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የውጤት ትንተና

### 4.1.1 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

**ሰንጠረዥ 4.1 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ቡድናዊ ገላጭ ስታትስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት**

| የቁጥር ቡድኑ | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት Std.D | መደበኛ የስህተት አማካይ | የቲ-ዋጋ (T) | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ሰንጠረዥ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 34 | 19.2353 | 7.08416 | 1.21492 | 0.036 | 66 | 0.935 | የለም |
| ድህረ ፈተና | 34 | 19.5294 | 7.57682 | 1.29941 | | | | |

**የጉልህነት ደረጃ (significant level) *P>0.05**

ከላይ በሰንጠረዝ 4.1 እንደሚታየው የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (19.2353) ከድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (19.5294) ተቀራራቢ ይመስላል፡፡ ከዚህም ሌላ የቅድመ ትምህርቱ መደበኛ ልይይት አማካይ ውጤት (7.08416) እና የድህረ ትምህርቱ መደበኛ ልይይት አማካይ ውጤት (7.57682) ብዙም የተራራቁ ባለመሆናቸው የሁለቱም ቡድኖች ውጤት ከየአማካዮቻቸው ያላቸው ርቀት ተቀራራቢ

መሆኑን ያመላክታል። ይሁን እንጅ የአማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ ያላቸው ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑን በእርግጠኝነት መናገር አያስደፍርም።

ይህንኑ በስታትስቲክስ ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (idependent sample t-test) ተፈትሾ፣ ለምናልባት ስህተት 5% (0.05) (significant level) በመተው የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ (t(0.034) በመሆኑ፤ በ66 የነፃነት ደረጃ (Dgree of freedom) በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.036) ያነሰ በመሆኑ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል። ቀጥለን የሙከራ ቡድኑን የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤትን እንመለከታለን።

### 4.1.2 የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

**ሰንጠረዥ 4.2 የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ቡድናዊ ገላጭ ስታትስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት**

| የሙከራ ቡድኑ | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት Std.D | መደበኛ የስህተት አማካይ | የቲ-ዋጋ (T) | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ሰንጠረዥ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | 34 | 19.2941 | 7.01310 | 1.20274 | 4.056 | 66 | 0.000 | አለው |
| ድህረ ፈተና | 34 | 26.8824 | 7.40092 | 1.26925 | | | | |

**የጉልህነት ደረጃ (significant level) *P < 0.05**

በሰንጠረዥ 4.2 የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካካይ ውጤት (19.2941) ከድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (26.8824) ብልጫ ያለው መሆኑን ከስሌቱ መረዳት ይቻላል። እንዲሁም የቅድመና ድህረ ትምህርት የመደበኛ ልይይቶች ውጤቶቻቸው ሲታይ የቅድመ ትምህርት ፈተናው (7.01310) ሲሆን የድህረ ትምህርቱ ደግሞ (7.40092) ሆኗል። ሆኖም የአማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው ጉልህ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል። ልዩነታቸውን በስታስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው

በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (idependent sample t-test) ተፈትሾ፣ ለምናልባት ስህተት 5% (0.05) በመተው የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ (t(4.056) በመሆኑ፤ በ66 የነፃነት ደረጃ (Dgree of freedom) በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.000) ብልጫ ያለው በመሆኑ በሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት እንዳለ አመላክቷል፡፡ ቀጥለን የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖቹን የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት እንመለከታለን፡፡

## 4.1.3 የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ ትምህርቱን ምንም ሳይማሩ በወሰዱት ፈተናና በተለያየ የአቀራረብ ስልት ለስምንት ሳምንታት (ሁለት ወራት) ከተማሩ በኋላ በወሰዱት ፈተና መካከል ያሳዩትን የችሎታ መለያየት ወይም መመሳሰል በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መለየት ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ቅድመ ፈተናው የተገኘው ውጤት ተተንትኖ ጥቅም ላይ የዋለው በሁለቱ ቡድኖች የተካተቱት ተማሪዎች ተቀራራቢ የቋንቋ ችሎታ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከቅድመ ፈተናው የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.3 የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ቡድናዊ ገላጭ ስታትስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት**

| ቡድኖቹ | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት Std.D | መደበኛ የስህተት አማካይ | የቲ-ዋጋ (T) | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ሰንጠረዥ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 34 | 19.2941 | 7.01310 | 1.20274 | 0.034 | 66 | 0.973 | የለም |
| የቁጥጥር | 34 | 19.2353 | 7.08416 | 1.21492 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (significant level) *P>0.05

ከላይ በሰንጠረዝ 4.3 እንደሚታየው የቅድመ ትምህርት ፈተናው የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት (19.2941) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (19.2353) ተቀራራቢ ይመስላል፡፡ ከዚህም ሌላ የሙከራ ቡድኑ መደበኛ ልይይት አማካይ ውጤት (7.01310) እና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርት ፈተናው (7.08416) ብዙም የተራራቁ ባለመሆናቸው የሁለቱም ቡድኖች ውጤት ከየአማካዮቻቸው ያላቸው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይሁን

እንጅ የአማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የመጠቀም ችሎታ በእርግጠኝነት መናገር አያስደፍርም፡፡

ይህንኑ በስታትስቲክስ ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (idependent sample t-test) ተፈትሾ፣ ለምናልባት ስህተት 5% (0.05) (significant level) በመተው የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ (t(0.034) በመሆኑ፤ በ66 የነፃነት ደረጃ (Dgree of freedom) በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.973) ያነሰ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ በተካተተቱ ተጠኝዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል በችሎታ ረገድ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ቀጥለን የድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤትን እንመለከታለን፡፡

## 4.1.4 የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በቡድኖቹ መካከል የሰፋ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ በመተግበር፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን ደግሞ በመደበኛው ክሂሎችን ለየብቻ ነጣጥሎ በማስተማር ለተከታታይ ስምንት ሳምንታት (ለሁለት ወር) ከተማሩ በኋላ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ለክሂሎቹ መጎልበት ያለውን አስተዋፅኦና በተማሪዎች ላይ ያመጣውን ለውጥ ለማረጋገጥ ለሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ተመሳሳይ ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በምዕራፍ ሶስት በመረጃ አተናተን ዘዴው ለመግለፅ እንደተሞከረው የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ያመጡትን ውጤት በመመዝገብ የድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት ተተንትኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.4 የድህረ ትምህር ፈተና አጠቃላይ ውጤት ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ በባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት**

| ቡድኖቹ | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት Std.D | መደበኛ የስህተት አማካይ | የቲ-ዋጋ (T) | የነፃነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ሰንጠረዥ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 34 | 26.8824 | 7.40092 | 1.26925 | 4.048 | 66 | 0.000 | አለው |
| የቁጥጥር | 34 | 19.5294 | 7.57682 | 1.29941 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (significant level) *P < 0.05

በሰንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካካይ ውጤት (26.8824) ከቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (19.5294) ብልጫ ያለው

መሆኑን ከስሌቱ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የሁለቱ ቡድኖች የመደበኛ ልይይቶች ውጤቶቻቸውም ሲታይ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተናው (7.40092) ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ (7.57682) ሆኗል፡፡ ሆኖም የአማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የመጠቀም ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ ልዩነታቸውን በስታስቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ስለሆነ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (idependent sample t-test) ተፈትሾ፣ ለምናልባት ስህተት 5% (0.05) በመተው የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ (t(4.048) በመሆኑ፤ በ66 የነፃነት ደረጃ (Dgree of freedom) በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.000) ብልጫ ያለው በመሆኑ በድህረ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ ፈተናው ስታስቲክስ ውጤት የጎላ ልዩነት እንዳለ አመላክቷል፡፡

በዚህም መሰረት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማስተማር ዘዴ አንብቦ የመረዳት ክሂልን የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የመጠቀም ችሎታ እንዳላቸው ያመላክታል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ከጥናቱ ባህሪ ጋር በሚሔዱ የመተኘተኛ ስልቶችም ተተንትነዋል፡፡ በመረጃዎቹ ትንታኔ መሰረት የጥናቱ ውጤት ተብራርቶ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ በጥናቱ ውጤት ትንተና በመጀመሪያ የተፈተሸው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንጽጽር ነው፡፡ በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በተገኘው አማካይ ውጤት ሁለቱ ቡድኖች ከልምምዱ በፊት የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው የስታትቲክ ስሌቱ ($p>0.05$) አረጋግጧል፡፡

በዚህ መነሻነት ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ መንገዶች ማለትም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት እና በመደበኛው የትምህርት ዘዴ ለየብቻ ከተለማመዱ በኋላ ተመሳሳይ ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የሰጠው ግኝት በሰንጠረዥ 4.4 እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (26.8824) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (19.5294) በስታትስቲክ ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ሆኖ በመገኘቱ የጎላ ልዩነት መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት ጠቀሜታ አለው ወደሚለው መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡

ለውጡ የመጣው ክሂሎቹን በቅንጅት ሲማሩ የቀረበላቸውን መማሪያ እያነበቡ በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ-ንባብ በተዘጋጁት ተግባራት ላይ በግልና በቡድን ተወያይተው ካዳበሩት ሀሳብ የመጣ ይመስላል፡፡ ተማሪዎች በዚህ አቀራረብ ስልት በግልና በቡድን ሲለማመዱ በአግባቡ ስለምንባቡ ይዘት ያላቸውን ግንዛቤ እየተነበዩ እንደጻፉ፤ እያነበቡ ከቀደመ ዕውታቸው ጋር እያገናዘቡ እንደጻፉ፤ እንዲሁም ካነበቡት ነገር ተነስተው ዋና ሀሳብና ማጠቃለያ በጽሁፍ መስጠት እንደቻሉና ስላነበቡት ጉዳይ በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑንም የሚጠቁም ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የተሳተፉት የሁለት ክፍል 68 ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ እንደሆነ አጥኝው በክፍል ውስጥ ጠይቆ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተመሳሳይ መሆኑ ለጥናቱ ውጤት አስተዋፅኦ ያደረገም ይመስላል፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ለጥናቱ ጥያቄ አወንታዊ ምላሽ አስገኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፣ ማጠቃለያ እና አስተያየት

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የጥናቱን ማጠቃለያና አስተያየት መግለፅ ነው፡፡ ስለሆነም የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ማጠቃለያና አስተያየቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 5.1 የጥናቱ ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ መመርመር ነበር፡፡ ይህንን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ ሌሎች ዝርዝር አላማዎች ተነድፈውለታል፡፡ እነሱም፡-የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎቹን የማንበብና የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ክሂሎችን ነጥሎ ከማስተማር ዘዴ የተለየ አስተዋጽኦ መኖር አለመኖሩን መመርመር፤ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ከተማሩበት መንገድ የትኛው ውጤታማ መሆኑን መመርመር፤ እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በምን ያህል ደረጃ ትስስርና ዝምድና አላቸው የሚለውን መፈተሽ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት እንዲቻል በመጀመሪያ ተጠኝዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት 68 ተማሪዎችን በናሙናነት በመምረጥ በሁለት ምድቦች በመክፈል የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የያዘ የቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፡፡ በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤትም በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኂላ የሙከራዊ ቡድኑ በማንበብና መጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ ለሁለት ወር ተምረዋል፡፡ ትምህርቱ ከተሰጠ በኂላ ሁለቱም ቡድኖች ድህረ-ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡

በዚህ መሰረት በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተና እንዲሁም በቅድመ ትምህርት ቃለ-መጠይቅና ድህረ ትምህርት ቃለ-መጠይቅ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ከጥናቱ ባህሪ ጋር በሚሔዱ የመተንተኛ ስልቶችም ተተንትነዋል፡፡ የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል፡፡

በጥናቱ ውጤት ትንተና በመጀመሪያ የተፈተሸው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንጽጽር ነው፡፡ በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት

ፈተና በተገኘው አማካይ ውጤት ሁለቱ ቡድኖች ከልምምዱ በፊት የጎላ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው የስታትቲክ ስሌቱ (p>0.05) አረጋግጧል፡፡

በዚህ መነሻነት ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ መንገዶች ማለትም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት እና በመደበኛው የትምህርት ዘዴ ለየብቻ ከተለማመዱ በኋላ ተመሳሳይ ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ወስደው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (26.8824) ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (19.5294) በስታትስቲክ ጉልህ ልዩነት (p<0.05) ሆኖ በመገኘቱ የጎላ ልዩነት መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ከተማሪዎች የተሰበሰቡት የቃለ-መጠይቅ መረጃዎች ክሂሎቹን በቅንጅት መማራቸው ተመራጭ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ ከድህረ ፈተና ትንተናው የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ይጠቃለላል፡፡

- ❖ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ክሂሎቹን ነጥሎ ከማስተማር ዘዴ የተሻለ አስተዋፅኦ አለው፡፡
- ❖ የሙከራ ቡድኑ የተማሩበት የማስተማሪያ ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑ ከተማሩበት ዘዴ የተሻለና ውጤታማ ነው፡፡
- ❖ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ትስስርና ዝምድና አላቸው፡፡

## 5.2 የጥናቱ መደምደሚያ

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት አጥኝው ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል፡፡

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ሞጆ ከተማ አስተዳድር በሚገኘው ቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በአስራ አንደኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች በወሳኝ ንሞና የተመረጡ ስልሳ ስምንት ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለመመርመር የተካሄደ ነበር፡፡ በመሆኑም ትምህርቱ ለተከታታይ ስምንት ሳምንታት (ሁለት ወር) ተሰጥተዋል፡፡ ትምህርቱ የቀረበው ለሁለቱም ቡድኖች በተለያዩ መንገዶች ነው፡፡ የሙከራ ቡድኖቹ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት አቀራረብ ስልትን በመተግበር ሲማሩ፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ ክሂሎቹን በተለመደው መንገድ ተምረዋል፡፡

ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት በሁለቱ ቡድን ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የአንብቦ መረዳት እና የመጻፍ ክሂል ችሎታቸው ዳራና የግንዛቤ ደረጃቸውን በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማረጋገጥ አንድ አይነት ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል። ከቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኘው ውጤት በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ እና በባእድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኗል። ትንተናው እንዳመለከተውም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት የለም።

የሙከራ ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ለሁለቱም ቡድን ተማሪዎች አንድ አይነት ድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር አቀራረብ ስልትን በመተግበር በሙከራ ቡድን ተማሪዎች ችሎታ ላይ ያመጣው ለውጥ ተገምግሟል። ከድህረ ፈተናው የተገኘው ውጤትም በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክ እና በባእድ የናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል። በውጤቱም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ የማንበብና የመጻፍ ክሂልን ማዳበራቸው ተረጋግጧል። የቡድን እና ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ውጤት እንዳመላከተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታቲስቲካዊ የውጤት ልዩነት (statistically significant difference) አለ። በመሆኑም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ስልትን መተግበር የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ  ክሂል ያዳብራል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

## 5.3 አስተያየት

ከላይ በማጠቃለያው እንደተገለፀው የጥናቱ ውጤት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ስልትን መተግበር የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ  ክሂል የሚያዳብር መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። በመሆኑም አጥኚው የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አስተያቶች አቅርቧል።

### 1. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በቅንጅት ማቅረቡ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ ይህ ጥናት አመላክቷል። በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትኩረት በመስጠት በቅንጅት ቢያስተምሩ መልካም ነው። ክሂሎቹን ሲያስተምሩም ተማሪዎቻቸውን በግል፣ በጥንድና በቡድን በመከፋፈል እርስ በርስ መረጃ እዲለዋወጡ፣ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ተገቢውን ዝግጅትና ክትትል ቢያደርጉ መልካም ነው።

## 2. ለመርሐ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች፡-

ክሂሎችን ነጣጥሎ ማስተማሩ የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂሎች ከማጎልበት አንጻር ክፍተት እንዳለበት የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። በመሆኑም በተዘጋጀው መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂል የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ የመገምገም ስራ ቢሰሩ፤ አዲስ መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጻህፍት በሚያዘጋጁበት ወቅት የቋንቋ ክሂሎች በቅንጅት የሚቀርቡበት መንገድ ቢኖርና ለልምምዱም በቂ ክፍለጊዜ ቢመደብለት መልካም ነው።

## 3. ለጥናት አቅራቢዎች፡-

ይህ ጥናት ሙከራዊ የምርምር ዘዴን በመከተል የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ በመመርመር የተከናወነ ነው። የጥናቱ ውጤትም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማስተማር ስልትን መተግበር የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ  ክሂል የሚያዳብር መሆኑን አመልክቷል። ይሁን እንጂ ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በተለይ አራቱን የቋንቋ ክሒሎች አቀናጅቶ ከማስተማር አኳያ በስፋት ጥናት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል የሚሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

## ዋቢ ፅሁፎች

ሞገስ አመራ፡፡ (1999)፡፡ “የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና” ፡፡ ለ አርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ትዝታ ደሳለኝ፡፡ (2003)፡፡ “የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር አተገባበር እና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ”፡፡ ለ አርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

አለማየሁ ደስታው፡፡ (2011) ፡፡ “ በመፃፍ ክሂል ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ንፅፅራዊ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 በሚገኙ የመንግስትና የግል ት/ቤቶች በ7ኛ ክፍል ተተኳሪነት”፡፡ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ፣ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ(ያልታተመ)፡፡

አታኽልቲ መኮንን፡፡ (1998)፡፡ “የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ሥነዘዴ አተገባበር ፍተሻ”፡፡ ለ አርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

እሸቴ መብራት ፡፡ (2003) ፡፡ “የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት” ፡፡ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ጌታቸው በለጠ፡፡ (2007) ፡፡*አማርኛ ቋንቋ ከ9ኛ-10ኛ ክፍል (Galaxye Reference Series*)፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጥላሁን ከበደ ፡፡ (2003) ፡፡ “የ9ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባባር ፍተሻ”፡፡ ለ አርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

Airasian, W. Peter (1997). *Class room Assessment*. Newyork: The Mc G raw-Hill Company.

Atkin S, J. etal. (1996). *Skills development methodology part two* Addis Ababa: Addis Ababa University press.

Barrs, Myra. (2000). The Reader in the Writer.Reading (United Kingdom Reading Association), July, 54-60. Beerdgew (2003). “*Reading-writing connection in the class-room*” (hht://www.Edu/ library CAGS-project /LTHOMSON/ web%20 page/r-w% 20 class-room htm.)

Beerdgew (2003). Readering-writing connection in the class-room. (http://www.edu/ library /CAGS-project/LTHOSON/web%20 class-room htm.)

Block, C and Mangieri, J. (1995). *Reason to Read Thinking Strategies for Lifee Through Literature,* Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addison.

Block, CathyColling. (1997). *Teaching the Language arts. Expanding thinking Student Centred instruction*. Boston: Allyn and Bacon.

Burns et al. (1999). *Teaching Reading*; *Today's Elementary schools*(7thed). New York; Houghton mifflin Company.

Byrne, D. (1981). *Integration Skill in Johnson and Marrow*. HongKong: Long man Group Ltd.

Celce, M. (1991). *Teaching English as Second Language (ed)*. Boston: Heinle and Heinle publishers.

Conley, Mark W. (1997). *Reading and Writing: teaching for the connection*. (2nd ed.) Less har court Brache and company.

Corder.p.(1973). *Introducing applied linguistics*. Penguine.

Cunnings worth, A. (1995). *Evaluating and selecting EFL Teaching Materials*.London: Heinemann Educational Books.

Gary, cobine. (1995). Writing as a response to reading. (Http://www.Vatide. com./pnp/ERIC/ write- read.htm.)

Gower, R.and Walters.S.(1983). Teaching Practice Hand Book: A reference Book for EFL Teachers in training. Oxford Heinemann.

Harmer, J. (1993). *The practice of English language teaching*. London: Longman Press.

Harp, Bill and Brewry, John. (1996). *Reading and writing Teaching for Company the connection.* (2nd ed.) S.A: Har court brace and campany.

Kennedey, Barbara C. (1994). *"The role of topic and the reading-writing connection."*

Koule, L. (1996). Methodology of Educational Research (2nd ed.) uiks publishing House pvt.Ltd.

Lindsay and knight. (2006). *Learning and teaching English: A course for teachers*. Oxford: oxford university press.

Littile wood, W. (1981*). Communicative language teaching*. Cambridge: Cambridg Unverstiy press.

May, Frank B. (1990). *Reading as communication*. New york: Macmillan Publishing company.

McDonough, J. and Shaw, C. (1992). Integrated Skills. ELT a teachers guide. Oxford: Black Well.

McDonough, J. and Shaw, C. (1993). Materials and methods.in ELT Oxford∶ Black well.

Nourish, J. (1990). *Language learning and their errors*. Modern English publication.

Nunan, D. (1991). *Language Teaching Methodology*. Cambridge; Cambridge Univeresity Press, Prentice Hall.

Nuttall, Christine. (1982). *Teaching Reading skills a Foreign Language*. London: Heinemann Educational Books. (New edition available 1998).

Oxford, R. (2001). Integrated Skills in the ELS/EFL Class room. ERTV. Maio: eric@Cas.org.

Raimes, A. (1983). Techniques in teaching writing. Oxford: Oxford university press.

Reid, J. (1993). Teaching ESL. writing. New Jersey: prentice hall peagents.

Richards, j. (1990). *The language teaching matrix*. Cambridge: Cambridge University press.

Richards, j. (1990). *The language teaching matrix*. Cambrige: Cambridge University press.

Rivers.W.(1981). Teaching Foreign Language Skill(2nded). Chicago press.

Ruddel, Martha Rapp (1997). Teaching content Reading and Writing. (2$^{nd}$ .ed.). U.A.S: Allyn and Bacon.

Ruddel, Martha Rapp (1997). Teaching content Reading and writing. (2$^{nd}$ ed.). U.S.A: Allyn and Bacon.

Smith, F. (1983) Reading Like a Writer. Language Arts.60 (5) ,558-567.

Squire, J. (1983). Integration focus and the teaching of writing. in freed man et.al. Learning to write. New york∶longMan Group Ltd

Troyka, L. (1990). Handbook for writers Englewood Cliffs: New Jersey prentice- hall Inc.

Unrau. Norman (2004). Content Area Reading and Writing Fostering Literacy. Middle and Highschool Culture USA: Merill prentice Hail.

Ur, P. (1996). Course in language teaching, Practice and theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Victoria Grundvig. (2012). Can Picture Books in the English Class Room Lead to Increased Reading Comprehension? MA Thesis California University; Unpolished.

Williams, (ed.) *(1990). Reading in the Classroom.* London: Macmillan Publishers Ltd.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በሙከራና በጥብቅ ቡድኑ ለተካተቱ የቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና፡፡**

**መለያ ቁጥር** …………… ክፍልና ሴክሽን ………………………

**አጠቃላይ መመሪያ፡-** የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ ሲባል ለሚደረግ ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡ ቡድኖቹ ክሂሎቹን በውህደት ሳይማሩ የግንዛቤ ችሎታቸውና ደረጃቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ይህ ፈተና ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም መሰረት ይህ ፈተና ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ የእያንዳንዱን ክፍል መመሪያ በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በጽሁፍ መስጠት ይጠበቅባችኋል፡፡ ጥያቄዎቹን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 1:30 ሲሆን አጠቃላይ ፈተናው ከ50% የሚታረም ይሆናል፡፡

**ክፍል አንድ፡-** ቀጥሎ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍ ተነገሮች እንደያዙት ሀሳብ ቅደም ተከተል በማስተካከል አንድ የተሟላ አንቀጽ አድርጋችሁ ጻፉ፡፡ ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በተገቢው ቦታ ተስተካክሎ መፃፍ አንድ ነጥብ በመስጠት 10 ማርክ ይይዛል፡፡

1. በክረምት ለእረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ቃል ገብቼላት ነበር፡፡
2. በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ፣ አክስቴ ብቻዋን እንደምትኖር የነገረችኝ ትዝ አለኝና ምናልባት የሚሰማኝ ያጣሁት ደህና ባትሆን ይሆናል ብዬ ሀሳብ ገባኝ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማሰላሰል ቀጠልኩ፡፡
3. በልጅነቴ የምወዳት አክስቴን ለመጠየቅ ወደ ፍቼ ከተማ የሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር መቼም አይረሳኝም፡፡

4. ለግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኋላ፣ ባረጀውና ቁመቱ በጣም ከፍ ባለው የፍልጥ አጥር ላይ ተንጠልጥዬ አክስቴን ለመጥራት ወሰንኩ፡፡
5. የአክስቴን አይን ለማየት ብቸኩልም ወደ ቤቷ አጥር ግቢ ከመድረሴ በፊት ጥቅጥቅ ባለው የባህርዛፍ ጫካ ውስጥ ጥቂት መጓዝ ነበረብኝ፡፡
6. እኔም ከታች አግጥጦ ከሚጠብቀኝ ጉቶ ላይ አረፍኩ፡፡ ከዚያ በኋላማ ሁለት የጎድን አጥንቶቼ ተሰብረው አክስቴ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ከመንቃቴ በስተቀር በመካከል የሆነውን ነገር ሁሉ አላስታውስም፡፡
7. ድካሜን ሁሉ ረስቼ ጫካውን በሩጫ በማለፍ እውጪው በር እንደደረስኩ በሩን ቶሎ ቶሎ አንኳኳሁ፡፡ ነገር ግን "ማን ነህ"? የሚለኝ አጣሁ፡፡
8. እንደምንም ብዬ በመውጣት አጥሩ ጫፍ እንደደረስኩ የጨበጥኩት የበሰበሰ ፍልጥ ተሰበረ፡፡
9. የሐምሌን ጭጋግና ዝናብ ችዬ በልጅ እግሬ እየገሰገስኩ ከምኖርባት የገጠር መንደር ከአዲስጌ ግማሽ ቀን ተጉዤ ስድስት ሰዓት ገደማ ፍቼ ከተማ ደረስኩ፡፡
10. እንደገናም በሩን ደበደብኩት፤ ምንም መልስ የለም፡፡

## አንቀፁን አስተካክላችሁ እዚህ ቦታ ላይ ፃፉ

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ክፍል ሁለት፡- 2.1 ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት ለመልሳችሁ ምክንያት በመስጠጥ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ 4 ማርክ ይይዛሉ) ፡፡

1. አንድ ሰው ብቻውን ጫካ ውስጥ ቢያድር ምን ችግር ሊያጋጥመው ይችላል? መልሳችሁን አብራርታችሁ ጻፉ፡፡-----------------------------------------------------------------
2. ሰዎች ያልጠበቋቸው ችግሮች በሚያጋጥሟቸው ጊዜ ምን አይነት ስሜት ይፈጠርባቸዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን? -------------------------------------------

2.2 በምንባቡ መካከል የሚቀርቡትን የሂደት ጥያቄዎች የምንባቡን ቀጣይ ታሪክ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት የምትመልሱት ነው፡፡ ጥያቄዎቹን

ሳትሰሩ የምንባቡን ቀጣይ ክፍል ማንበብ ክልክል ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት ሶስት ነጥብ የሚይዝ ሲሆን አጠቃላይ 27 ማርክ ይይዛል።

## ምንባብ

(1) "አምላኬ እባክህ ጠብቀኝ የምህረት መላክተኛህን ላክልኝ!" አሉና መልካ እየሱስ ለመድገም "ለዝክረ ስምከ" ሲሉ በፊታቸው ሃያ ሜትር ያክል ራቅ ብላ የነበረች ትንሽ ቁጥቋጦ ከብዳ ታዩቻቸው። ወዲያው መልካ እየሱሳቸውን አቋርጠው ዓይኖቻቸውን አሻሹና እንደገና ቢገልጡ ያ እቁጥቋጦው ውስጥ ከብዶ የታያቸው ነገር የሚንቀሳቀስ መሰላቸው። እንደገና አስተውለው ሲመለከቱ አንድ ወይም ሁለት ርምጃ ወደፊት እየተራመደ ቀረብ ሲል ካናት እስከ ጅራቱ ጥርት ብሎ ታያቸው።

| |
|---|
| **ጥያቄ 1. እናንተ ብትሆኑ ምን አይነት ስሜት ይሰማችኋል? ምንስ ታደርጋላችሁ? ምክንያታችሁን ግለፁ። ---------------------------------------------------------------------------** |

(2) እግዚአብሄር መላከ ምህረቱን እንዲልክላቸው ቢለምኑት፣ ያልጠየቁትን መላከ መቅሰፍቱን ላከላቸው። "ነብር!" አሉ አባ ዓለም ለምኔ ቀስ ብለው። ከዚያ በሁዋላ አንደበታቸው ታሰረ። ልባቸው እንደተቃጠለ ሻማ ቀልጦ በውስጣቸው የፈሰሰ መሰላቸው። ሙሉ አካላቸው ቆርጦ ለፀሀይ እንደሰጡት ለጋ ተክል ዛለ፤ አእምሮዋቸው ድንዝዝ አለ፤ ዓይኖቻቸው እንቅልፍ እንደከበዳቸው ሲስለመለሙ አንዱ ነብር ሁለት እዩሆነ ይታያቸው ጀመር። ለመጮህ እየሞከሩ የሚበቃ ትንፋሽ አጡ።

| |
|---|
| **ጥያቄ 2. በአባ ዓለም ለምኔ ላይ የደረሰው ዓይነት ችግር ቢጋጥማችሁ ምን ዓይነት የመፍትሄ እርምጃ ትወስዱ ነበር? ---------------------------------------------------------------** <br> **-------------------------------------------------------------------------------------------** |

(3) ነብሩ እንዲህ ቀስ እያለ ተጉዞ አባ ዓለም ለምኔ አሉበት ለመድረስ ትንሽ ሲቀረው ቆም ብሎ እያጉረመረመ እሳቸውን ትንሽ ተመለከተና ከዚያ ዓይኖቹን ወደወንዝዋ አተኮሮ ይመለከት ጀመር። መነኩሴውም የመጀመሪያው የፍርሃት ሰመመን እንደማለፍ ብሎላቸው አእምሮዋቸውን መግዛት ሲጀምሩ ዓይኖቻቸውን ሲፈሩ ሲቸሩ ገለጥ አደረጉ። ነብሩ ሽንጡን ለሳቸው ሰጥቶ ፊቱን ወደ ወንዝዋ አዙሮ እየተመለከተ ጅራቱን በቀስታ ከወዲያ ወዲህ ሲያወዛውዝ አዩ። ቀስ ብለው ነብሩ ወደሚመለከትበት ዓይኖቻቸውን

ቢልኩ ከወንዝዋ ወዲህ ማዶ የሳር ክምር በራሱ ላይ የተሸከመ የሚመስል ነገር ቆሞ አዩ፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 3. ከወንዝዋ ወዲህ ማዶ ቆሞ ያዩት ነገር ምን ይመስላችኋል? ለግምታችሁ ምክንያታችሁ ምንድን ነው? ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(4) ምንም እንኳ ያንበሳን ስም እንጂ መልኩን አይተው ባያውቁም እንዲሁ በግምት አዲስ መጪው እሱ መሆኑን አወቁ፡፡ ሁለቱ ኀበዞች ሃያ ሜትር ያክል በሚሆን ርቀት ቆመው ትንሽ ከተፋጠጡ በኋላ አንበሳ ቀስ እያለ አንድ ወይም ሁለት እርምጃ ወደፊት ሲራመድ ነብር ያኑ ያክል ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመረ፡፡ እንዲህ እያሉ አባ ዓለም ለምኔ ካሉበት ዛፍ ስር ተጠጉ፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 4. እንደ አባ ዓለም ለምኔ በሁለት ሀይለኛ አራዊት ብትከበቡ ምን አይነት እርምጃ ትወስዳላችሁ? ለምን? ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

| |
|---|
| **ጥያቄ 5. ከአንበሳና ከነብር ማን ያሸንፋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ምክንታችሁ ምንድን ነው? ---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(5) አባ ዓለም ለምኔ እንደተቃጠለ ሻማ ቀልጦ የፈሰሰ ልባቸው ሀይሉን እንዴት እንዳጠራቀመ፤ እኒያ ከተዘረጉበት ለማጠፍ አስቸግረው የነበሩ እግሮቻቸው እንዴት ተነስተው እንደቆሙ ሳይታወቃቸው እንደ ብርቱ እንደጤናማ ሮጠው እዛፉ ላይ ለመውጣት ቢሞክሩ ግንዱ ወፍሮ መታቀፍ ስላልቻሉና ያበጡ እግሮቻቸው መቆንጠጥ ስላቃታቸው ተንሸራተው ወደቁ፡፡ እንደገና ለመውት ሲሞክሩ ተመልሰው ሲወድቁ ዛፉ ከላጠውና ጋሬጣ ከወጋው እግራቸው እዚያ ዋርካ ስር የፈሰሰው ደም ሲታይ በደም ስራቸው አንድ ጠብታ ደም የቀረ አይመስልም ነበር፡፡ በመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው ማልቀስ ጀመሩ፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 6. የአንበሳውና የነብሩ ፍጥጫ ለአባ ዓለም ለምኔ መፍትሄ ያመጣል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ምክንያታችሁን ግለፁ፡፡-----------------------------------------------------------** <br> **------------------------------------------------------------------------------------------------------------** <br> **--------------------------------------------------------------------------** |

| |
|---|
| **ጥያቄ 7. አባ ዓለም ለምኔ ተስፋ ቆርጠው ማልቀስ ጀምረዋል፡፡ እናንተ ብትሆኑ ከአደጋው ለማምለጥ ምን ታደርጉ ነበር? ------------------------------------------------------** <br> **------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(6) አንዲት ከትልቁ ዋርካ አጠገብ ለብቻዋ በቅላ እላይ ከትልቁ ዋርካ ቅርንጫፎች ጋር የጠገናኘች ቀጭን ዛፍ አዩ፡፡ ወዲያው እሮጡ ሄዱና እስዋን አቅፈው በልባቸው እየተሳቡ ወጥተው ከዋርካው ቅርንጫፎ መካከል ተጣብቀው ተቀመጡ፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 8. አባ ዓለም ለምኔ ከዋርካው ላይ በመውጣታቸው ከአንበሳው መበላት ማምለጥ ቢችሉ ከነብሩ መበላት ማምለጥ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን?-------------------** |

| |
|---|
| **ጥያቄ 9. በታሪኩ መሰረት ስለ አባ ዓለም ለምኔ የኑሮ ሁኔታ ምን ተገነዘባችሁ?** <br> **------------------------------------------------------------------------------------------------------------** <br> **--------------------------------------------------------------------------------** |

(7) አንበሳው ዋርካው ስር የፈሰሰው ደምና ጠረናቸው ሲሸተው እዚያ ግድም መሆናቸውን እያወቀ ፈልጎ ስላጣቸው በብርቱ ጉምጅትና ቁጣ እያገሳ መሬቱን ሲልጥ፣ ድንጊውን ሲፈነቅል ፣ ቁጥቋጦውን ሲጥስ፣ ልባቸው ራደ፡፡ እንዳላመለጡት ሲረዱ ተስፋ በመቁረጥ ስቅስቅ ብለው ማልቀስ ጀመሩ፡፡

(ሀዲስ ዓለማየሁ፣ 1960)

## 2.3 ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ (የድህረ ንባብ ጥያቄዎች 4 ማርክ ይይዛሉ) ፡፡

1. በታሪኩ መሰረት ስለ አባ ዓለም ለምኔ የኑሮ ሁኔታ ምን ተገነዘባችሁ? -------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------

2. የፅሁፉን አብይ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለፅ በአጭሩ ፃፉ፡፡--------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------

**ክፍል ሶስት፡-** ከታች የቀረበውን ሰንጠረዥ መሰረት በማድረግ የዶክተር ሀዲስ አለማየሁን የሕይወት ታሪክ በማቀናጀት እንደገና ጻፉ፡፡ (5 ማርክ ይይዛል) ፡፡

| | |
|---|---|
| የባለታሪኩ ስም | ክቡር ዶክተርሀዲስ አለማየሁ |
| የአባት ስም | ቄስ አለማየሁ ሰለሞን |
| የእናት ስም | ወይዘሮ ደስታ አለሙ |
| የትውልድ ቦታ | ደብረ ማርቆስ አውራጃ ጎዛምን ወረዳ |
| የትውልድ ዘመን | ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ. ም |
| የተሰማሩበት የስራ መስክ | ደራሲ፣ አምባሳደር (1935-1966 በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥለሀገራቸው አገልግለዋል |
| የፃፏቸው መፃህፉት በጥቂቱ | ፍቅር እሰከ- መቃብር፣ተረት ተርት የመሰረት፣ወንጀለኛው ዳኛ ወዘተ. |
| ለሌሎች አርዓያ የሆኑበት ተግባር | ለኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት ለሀገራቸው በአርበኝነት አገልግለዋል፡፡ |
| ከዚህ ዓለም የተለዩበት ቀን | ህዳር 26 1996 ዓ. ም |

የሕይወት ታሪክ መፃፊያ ቦታ

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ ሁለት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**በሙከራና በጥብቅ ቡድኑ ለተካተቱ የቀርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የድህረ ትምህርት ፈተና።**

**መለያ ቁጥር** …………….  ክፍልና ሴክሽን ……………………….

**አጠቃላይ መመሪያ፡-** የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ ሲባል ለተደረገ ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው። ሁለቱም ክፍሎች በተለያየ መንገድ ለሁለት ወር የተማሩት ትምህርት ምን ያህል ለውጥ እንዳስገኘና ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመገምገም እንዲቻል የድህረ ትምህርት ፈተናው ተዘጋጅቷል። በዚህም መሰረት ይህ ፈተና ሶስት ክፍሎች አሉት። የእያንዳንዱን ክፍል መመሪያ በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በጽሁፍ መስጠት ይጠበቅባችኋል። ጥያቄዎቹን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 1፡30 ሲሆን አጠቃላይ ፈተናው ከ50% የሚታረም ይሆናል።

ክፍል አንድ፡- ቀጥሎ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍ ተነገሮች እንደያዙት ሀሳብ ቅደም ተከተል በማስተካከል አንድ የተሟላ ተረት አድርጋችሁ ጻፉ። ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በተገቢው ቦታ ተስተካክሎ መፃፍ አንድ ነጥብ በመስጠት 10 ማርክ ይይዛል።

1. ድሃ ወንድሙን ግን የአንድ ምጦተኛ ምስኪን ያህል እንኳን በችሮታ ራርቶለት አያውቅም ነበር።
2. ከጓደኞቹ አንዳቸውም እንኳን አንድ መላ ሳይሰጡት ጥለውት በየቤታቸው ገብተው ይንሾካሾኩ ጀመር።
3. አንድ ድሃ እና አንድ ሀብታም ወንድማማቾች ነበሩ።
4. በዚህ ጊዜ ወንድሙ ሳይፈራና ሳይደነግጥ አንተ ብቻ እንኳን ደህና ሆንክ አለና ትጥቁን ጠበቅ ጠበቅ ያድርግ ጀመር።
5. ሀብታሙ የሚበላውና የሚጠጣው ደስታ የሚያደርገው ሁሉ ከባዕዶች ጋር ነበር።

6. ከዚያም ሀብታም ወንድሙ ሰው በእጁ እንዳልጠፋበት በመንገር የሆነውን ነገር ሁሉ በዝርዝር በማስረዳት ወንድሙን ይቅርታ ጠየቀው፡፡
7. ከዚያም አንድ ሙክት አርዶ ስጋውን በጨርቅ አልብሶ ከአንድ ሳንቃ ላይ ዘርሮ የሞተ ሰው አስመስሎ አሰቀመጠና፤እነዚያን ጓደኞቹን እየጠራ ምክር እንዲሰጡት ጠየቃቸው፡፡
8. በመጨረሻም ከንብረቱ ገሚሱን ሰጥቶት አብረው በደስታ መኖር ጀመሩ፡፡
9. አንድ ቀን ግን አንድ ብልሃት መጣለት፡፡
10. በጓደኞቹ ካዘነ በኋላ ያን ሊስጠጋው የማይፈቅደውን ወንድሙን ጠራና ዛሬ ከትልቅ መከራ ላይ ወድቄያለሁ፤ ስለዚህ ምን ማድረግ ይሻለኛል ሲል አማከረው፡፡

## አንቀፁን አስተካክላችሁ እዚህ ቦታ ላይ ፃፉ

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**ክፍል ሁለት፡- 2.1 ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት ለመልሳችሁ ምክንያት በመስጠጥ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ 4 ማርክ ይይዛሉ) ፡፡**

1. ርዕሱን በመመልከት ስለምን ሊያወራ እንደሚችል ግምታችሁን ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡-----------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

2. ሰው በአካባቢው ነዋሪ የሚከበረው ምን ሲያደርግ ይመስላችኋል? የሚጠላውስ? ------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

2.2 በምንባቡ መካከል የሚቀርቡትን የሂደት ጥያቄዎች የምንባቡን ቀጣይ ታሪክ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት የምትመልሱት ነው፡፡ ጥያቄዎቹን ሳትሰሩ የምንባቡን ቀጣይ ክፍል ማንበብ ክልክል ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት ሶስት ነጥብ የሚይዝ ሲሆን አጠቃላይ 27 ማርክ ይይዛል፡፡

## "ወንድማማቾቹ"

(1) ጊዜው ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ሃያ ዓመት በኋላ ነው፤ቦታው "ጃኑዳ" የሚባል ውብ ከተማ፡፡ የከተማው ት/ቤት ርዕሰ መምህር ስም ዘነበ ሲሆን በልዩ የሚባል ወንድም ነበረው፡፡ ወንድማማቾቹ በልጅነት እድሜያቸው እርስ በርሳቸው በጣም የሚተሳሰቡና የሚሰሩትን ስራ ሁሉ በአንድነት የሚያከናውኑ ነበሩ፡፡ ወታደር ለመሆን በአንድነት ተመዘገቡ፤ ወደጦርነት በአንድነት ዘመቱ፤ በአንድ የጦር ክፍል ውስጥ በአንድነት አገልግለው በአንድ ጊዜ የአስር አለቅነት ማዕረግ አገኙ፡፡ ከጦርነት ሲመለሱም የከተማዋ ነዋሪ "ቁም ነገረኛ ወጣቶች" እያለ ያሞካሻቸው ነበር፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 1. በቀጣዩ የታሪኩ ክፍል ምን የሚቀርብ ይመስላችኋል? ------------------------------ ----------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(2) ከዚህ በኋላ አባታቸው ሞቱ፡፡ የአባታቸው ንብረት ለመካፈል የማይመች ስለሆነ እቃው ለጨረታ ቀርቦ እያንዳንዱ የፈለገውን ከገዛ በኋላ፣ ገንዘቡን ለሁለት ለመካፈል ተስማሙ፡፡ በዚህ መልክ ንብረቱ ተሸጦ ተካፈሉ፡፡ ነገር ግን፣ አባትየው በአካባቢው አንድም ሰው ያላደረገው ትልቅ የወርቅ ሰዓት ነበራቸው፡፡ ሰዓቱ ለጨረታ በቀረበ ጊዜ ሁለቱ ወንድማማቾች መጫረት ሲጀምሩ፣ ሌላው ተጫራች ህዝብ ለቆላቸው ከጨረታው ወጣ፡፡ በዚህ ጊዜ ዘነበ ያሰበው፣ በልዩ ይለቅልኝና እኔ እወስዳለሁ የሚል ነበር፡፡ በልዩም በበኩሉ እንዲሁ ይመኝ ነበር፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 2. የውርስ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? ------------- -----------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(3) ጨረታው በዚህ ሂደት ቀጥሎ የሰዓቱ ዋጋ አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር ላይ ደረሰ፡፡ በዚህ ጊዜ ዘነበ፣ "ወንድሜ የሚሰራው ስራ ጥሩ አይደለም" ብሎ አሰበ፡፡ ከዚያም በአንድ ጊዜ ሁለት ሺ ብር አደረሰውና ወደ ወንድሙ ዘወር ብሎ እንኳ አልተመለከተም፡፡ በጨረታው አዳራሽ ፀጥታ ሰፈነ አጫራቹ ብቻ የተጠራውን ዋጋ እየመላለሰ ይናገር ነበር፡፡ በልዩ አሁንም ከጨረታው እንዳልወጣ ባየ ጊዜ፣ "በውነቱ ጥሩ ስራ አይሰራም፣ እንዴት እኔ የዋልኩለትን ውለታ ሁሉ ቸል ብሎ ጨረታውን ያንርብኛል፤ ወዲያውም እኮ

ታላቅ ወንድሙ ነበርኩ" ብሎ አሰበ። እዚያ ቦታ ብዙ ሰዎች ቆመው ይመለከቱ ስለነበር፣ በልዩም "ወንድሜ በነዚህ ሰዎች መካከል መሳቂያ ሊያደርገኝ አይችልም" በማለት፣ አሁንም ጨረታውን በመቶ ብር ከፍ አደረገ። ዘነበ ድንገት በሳቅ ፈንድቶ፣ "ሶስት ሺ ብር እና የኔንም ወንድምነት ከዚሁ ጋር" ካለ በኋላ፣ እየሮጠ ካዳራሹ ወጥቶ ሄደ።

| |
|---|
| **ጥያቄ 3. ዘነበ ከሳቀ በኋላ "ሶስት ሺ ብርና የኔንም ወንድምነት ከዚሁ ጋራ ሲል ምን ማለቱ ነው።-------------------------------------------------------------------------------------------** |
| **-------------------------------------------------------------------------------------------** |

(4) ዘነበ ፈረሱን እየጫነ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ አንድ ሰው ካዳራሹ ወጥቶ ወደርሱ ቀረበና "ሰዓቱ ያንተ ነው፤ በልዩ ተሸንፏል" አለው። ይህንን እንዳወቀ፣ ወዲያው የፀፀት ስሜት ተሰማው። በዚህ ጊዜ በልዩ ከእንግዲህ በኋላ ወንድምህ አንተን እየተከተለ የሚሄድበትን ጊዜ ደግመህ አታየውም!" በማለት፣ ጮሆ ተናገረ። "አንተም! ሁለተኛ እኔ ላንተ እሰራ የነበረውን ሁሉ ፈጽሞ ደግመህ አታየውም!" ብሎ ሲመልስለት፣ ነብር ሆኖ ነበር። ከዚህ ጊዜ በኋላ ሁለቱም ከአባታቸው ጋር አብረው ይኖሩበት የነበረውን ቤት ረግጠውት አያውቅም።

(5) በልዩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአንድ ድሃ ገበሬ ልጅ አገባ። ነገር ግን ወንድሙን ለሰርግ አልጋበዘውም። ባገባ በዓመቱ፣ ከቤቱ ራቅ ብላ ታስራ ሳር ትበላ የነበረች አንድ ላሙ ሙታ ተገኘች። የአማሟቷንም እንቆቅልሽ ማንም ሊፈታው አልቻለም። ተመሳሳይ መጥፎ እድሎች ተከታትለው ደረሱበት። ይባስ ብሎም፣ በክረምት ወቅት የድርቆሽ ዳሱ ከበርካታ ንብረቱ ጋር ተቃጠለ። እሳቱ ከየት እንደተነሳ ያወቀ ግን አልነበረም። "ይህ ሁሉ የተደረገው እኔን ለመጉዳት ባሰበ ሰው ነው" በማለት፣ ስቅስቅብሎ አለቀሰ። ሰማዩ በላዩ ተደፋበት። ድሃ እየሆነ ስለሄደም የመስራት ፍላጎቱ ተዳከመ።ቤቱ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲተክዝ መዋል አበዛ።

| |
|---|
| **ጥያቄ 4. በልቦለዱ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦች እንደተነሱ በአጭሩ ዘርዝሩ።** |
| **-------------------------------------------------------------------------------------------** |
| **-------------------------------------------------------------------------------------------** |

(6) ዘነበ በወንድሙ ላይ በደረሰው ሁሉ አዘነ፤ ዛሬ ወንድሜን ይቅርታ መጠየቅ አለብኝ ብሎ ወሰነ፡፡ ቀኑ ሲመሽ ወደ ወንድሙ ቤት አመራ፡፡ በሩ አጠገብ ሲደርስ ትንሽ ቆም ብሎ እንደማሰብ ሲል፣ ከቤት ውስጥ የርሱ ስም ሲጠራ ሰማ፡፡ የወንድሙ ሚስት ነበረች፣ ስሙን እያነሳች የምትናገረው፡፡ "ወንድምህ ዛሬ ቆረበ እኮ! እርግጠኛ ነኝ ስላንተ ያስብ ነበር" አለች፡፡ "እባክሽ ስለኔ አይደለም፤ ስለራሱ ነው የሚያስበው" አለ በልዩ፡፡ በዚህ ጊዜ ዘነበ ከአመድ ማጠራቀሚያው በርሚል ከሰል በመውሰድና ጭራሮ ለቃቅሞ ወደ ድርቆሹ ዳስ በመግባት እሳት አነደደ፡፡ በእሳቱ ብርሃንም ወንድሙ ፋኖስ የሚሰቅልበትን ሜንጦ ስላየ፣ ስዓቱን በሜንጦው ላይ አንልጥሎ ፍሙን በማጥፋት ወደ ቤቱ አመራ፡፡ ጭንቀቱ ስለተቃለለለትም፣ በዚያ ቅዝቃዜ ሲሮጥ የወጣትነት ኃይል ይሰማው ነበር፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 5. ዘነበ ይቅርታ ለመጠየቅ ሄዶ ይቅርታ ሳይጠይቅ የተመለሰው ለምንድን ነው?** |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------- |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------- |

(7) በሚቀጥለው ቀን የድርቆሹ ዳስ ተቃጥሎ ማደሩን ሰማ፡፡ ምንአልባት ማታ ያነደደው እሳት ፈጽሞ ሳይጠፋ ቀርቶ ሳያቃጥለው አልቀረም ይሆናል፡፡ ይህም ሁኔታ ዘነበን በጣም አሳዘነው፤ ሀፍረትም ለበሰ፡፡ ቀኑ በጨለማ ሲተካ፣ ዘነበ በጠፍ ጨረቃ ወደ ወንድሙ ቤት በመሄድ ከቃጠሎው መካከል አንድ ቦታ ቆፍሮ አንድ ነገር አወጣ፤ ከዚያ ሰዓት የቀረው አንድ የተጨባበጠ ወርቅ ነበር፡፡ አንዲት ትንሽ ልጅ ቃጠሎው መካከል ቀሞ ሲቆፍር ማየቷን ተናገረች፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ወጣቶችም፣ ዳሱ የተቃጠለ እለት ዘነበን ወደ ወንድሙ ቤት ሲሄድ እንዳዩት ተናግረዋል፡፡ በማግስቱ ሰኞም፣ የፀባይ ለውጥ ማሳየቱን ሁሉም ሰዎች ያውቁ ነበር፡፡ የአካባቢው ባለስልጣኖችም ይህ መረጃ ስለደረሳቸው ለማጣራት ወስነዋል፡፡ በልዩ ደግሞ እነዚህ ሁሉ ወሬዎች ደርሰውት ስለነበር፣ ድርጊቱን የፈፀመው ወንድሙ እንደሆነ አምኖ ተቀብሏል፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 6. የአካባቢው ባለስልጣናት ዘነበን በቃጠሎው የጠረጠሩት ከምን ተነስተው ነው?** |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------- |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------- |

(8) በማግስቱ ለሁለቱም መጥሪያ ደርሷቸው ምርመራው ቦታ ተገናኙ፡፡ ዘነበ ወንድሙን ተመለከተው፡፡ በልዩም አስተዋለው፡፡ በድርጊቱ ወንድሙን የሚጠረጥረው እንደሆነ ሲጠየቅ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመጮህ "አልጠረጥረውም" አለ፡፡ ከዚያን ቀን በኋላ፣ በልዩ አልኮል በብዛት መጠጣት ጀመረ፡፡ ሁኔታዎች ሁሉ ተበላሹ፡፡ ዘነበም ቢሆን፣ ምንም እንኳን መጠጥ ባይጠጣ፣ መልኩ ስለተለወጠና ስለተጎሳቆለ፣ እሱ መሆኑን ማወቅ አዳጋች ነበር፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 7. በልዩ በወንድሙን "አልጠረጥረውም" ያለው ለምንድን ነው?**<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>----------------------------------------------------------------------------------------------------- |

| |
|---|
| **ጥያቄ 8. ታሪኩ በምን መልኩ ይቋጫል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ማስረጃችሁ ምንድን ነው?** --------------------------------------------------------------------------------------------------<br>--------------------------------------------------------------------------------------------------------- |

(9) አንድ ቀን ማታ ዘነበ ወደተከራያት ትንሽ ክፍል የወንድሙ ባለቤት ገብታ ከርሷ ጋር እንዲሄድ ጠየቀችው፡፡ ምንም ሳይናገር ተከትሏት ሄደ፡፡ በሩ መግቢያ ላይ ሲደርስ፣ የሚያንገሸግሽ ሽታ ሸተተው፡፡ በልዩ ገርጥቶ፣ ከስቶ፣ ዓይኖቹ ጎድጉደውና ከሰውነት ጎዳና ወጥቶ ሲመለከተው የዘነበ ጉልበት ነፋስ እንደነካው ቀጤማ አረገደ፡፡ ከአልጋው ታች ተቀምጦም እርር ብሎ አለቀሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁለቱም ወንድማማቾች መነጋገር ጀመሩ፡፡ ይህንን ያህል ጊዜ ተለያይተው ሲኖሩ፣ አንዳቸውም እንኳ የተደሰቱበት ጊዜ እንዳልነበር ተገላለጡ፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 9. ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂው ማን ነው ትላላችሁ? ምክንያታችሁን ግለፁ፡፡**<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------ |

(10) በልዩ አቅሙ ደክሞና ታሞ ስለነበር፣ ዘነበ ከአልጋው አጠገብ ሳይለይ አስታመመው፡፡ አንድ ቀን ጧት በልዩ ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ "ዛሬ ፍፁም ድኛለሁ፤ ከእንግዲህ ወንድሜ ሁልጊዜ ሳንለያይ እንደ ቀድሟችን አብረን እንኖራለን" አለው፡፡ ሆኖም በዚያው ቀን አረፈ፡፡ ዘነበ የወንድሙን ባለቤትና ልጇን ወደ ቤቱ ይዞ በመሄድ፣ ተንከባክቦ አኖራቸው፡፡ እሱም በአካባቢው ሰው የተከበረ፣ ምራቁን የዋጠ ሰው ሆነ፡፡ ሽማግሌው

የአስር አለቃ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆነውም፣ ለአካባቢው ህዝብ አንድ ውለታ ጥሎ ለማለፍ ስለፈለገ ነበር፡፡ በህፃናቱ ፀባይ ላይ እንዲቀረፅ የሚፈልገው ነገር ቢኖር፣ መጀመሪውም መጨረሻውም ፍቅር ነበር፡፡ እናም፣ ሰው ማፍቀርን ለታዳጊዎች አስተማረ፡፡ ህፃናት፣ እየመጡ እንደጓደኞቸውና እንደአባታቸው ያጫውቱት፣ ችግራቸውንም ያወያዩት ነበር፡፡

(በዓለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፣ ትርጉም አምሳሉ አክሊሉ) ለፈተናው እንዲመች መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ፡፡

**1.3 ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ (የድህረ ንባብ ጥያቄዎች 4 ማርክ ይይዛሉ፡፡**

1. ለበልዩ ድሃ መሆን ምክንያቶች ናቸው የምትሏቸውን ዘርዝሩ፡፡--------------------------
   ---------------------------------------------------------
2. የፅሁፉን አብይ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለፅ በአጭሩ ፃፉ፡፡---------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------

**ክፍል ሶስት፡- ከታች የቀረበውን የህወት ታሪክ አንብቡና ግለታሪካችሁን በአጭሩ ጻፉ፡፡ (5 ማርክ ይይዛል) ፡፡**

## “እንጋፋው የአትሌቲክስ አባት”

አትሌት ዋሚ ቢራቱ የተወለዱት ጥር 11 ቀን 1907 ዓ.ም ነው፡፡ የአቶ ቢራቱ በራቂ እና የወይዘሮ ወርቂ አያና ልጅ የሆኑት ዋሚ፣ የትውልድ ስፍራቸው ከአዲስ አበባ ከተማ 21 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ሱሉልታ ወረዳ አካኮና መነ አብቹ በተባለው ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው፡፡ ዋሚ የስድስት ወንዶች እና የአምስት ሴት ልጆች አባት፣ የሃያ አንድ ልጆች አያት እና የአስራ አንድ ልጆች ቅድመ አያት ናቸው፡፡

አትሌት ዋሚ ወደ አትሌቲክስ ስፖርት የመጡት መስከረም 5 ቀን 1945 ዓ.ም ወደ ውትድርናው ዓለም ከገቡ በኋላ ነው፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ግዛት በነበረችው አስመራ ውስጥ በነባር እና በአዲስ ወታደሮች መካከል በተደረገው የሩጫ ውድድር አንደኛ ወጡ፡፡ በዚህ አይነት መንገድ የአትሌቲክሱን ህይወት “ሀ” ብለው ጀመሩ፤ በሀገር ውስጥ የማራቶን ውድድር ሲኖር የሚቀናቀኗቸው ጠፉ፡፡ “በባዶ እግሬ በመሮጥ እና አበበ ቢቂላን ወደ ውድድሩ ዓለም በመሳብ፣ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፋና ወጊ ነኝ” የሚሉት ዋሚ ቢራቱ

በ1953 ዓ.ም በጃፓን ቶኪዮ ላይ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድር ሻምበል አበበ ቢቂላን ተከትለው ሁለተኛ ወጥተዋል፡፡

ሀገራችንን በመወከል በምስራቅ አፍሪካ፣ በጃፓን በቼክ ሪፐብሊክ እና በቀድሞዋ ሰው ቤት ህብረት ተወዳድረው አመርቂ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ዋሚ በሀገር፣ በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ ውድድሮች ሃምሳ አንድ ወርቅ፣ አርባ አራት የብር እና ሰላሳ የነሀስ ሜዳሊያዎችን ለመሸለም በቅተዋል፡፡ በተለይም በመስከረም 1996 ዓ.ም ቱሪዝም ኮሚሽን ባዘጋጀው ውድድር የሃያ አንድ ኪሎ ሜትሩን እሩጫ በ 2፡05 ደቂቃ በመፈፀም አድናቆትን ያተረፉ አንጋፋ አትሌት ናቸው፡፡ የሻለቃ ዋሚ ቢራቱ ታሪክ እጅግ ረጅም፣ ሰፊና ጥልቅ ነው፤ ደማቁ ዋሚ በቀጣይ የአትሌቲክስ ታሪክ ሲወሱ የሚኖሩ አንጋፋ አትሌት ናቸው፡፡

ምንጭ፡- (ደማቆቹ፣ 2000ዓ.ም የአንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሕይወት ውልብታ)

## የግለታሪክ መፃፊያ ቦታ

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

**አባሪ ሶስት**

**በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ**

**የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

# ለሙከራ ቡድኑ ለማስተማሪያነት የቀረቡ የምንባብ ትምህርቶች

## ሀ. ትምህርት አንድ

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፦ ያበዳሪዋ ጫና

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፦ 1፡30

የትምህርቱ ዓላማ፦

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳችሁን በፅሁፍ ትመልሳላችሁ፡፡
- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፦ ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዩ ቅድመ ንባብ ጥያቄ መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. አንድ ሰው የሚበላውና የሚጠጣው ቢያጣ ምን ሊያደርግ እንደሚችል በዝርዝር ፃፉ፡፡ ---
-------------------------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ ሁለት፦ ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

### "ያበዳሪዋ ጫና"

"በጣም ኩሩ ነህ ስለዚህ ነው ችግር የጎለሰሰህ… ግን ምን ታደርግ "አውራ ዶሮ በየፍጉ ክምር ላይ ቆም ይጮሃል" … እኔን ተመልከተኝ፤ ለምሳሌ፦ አዎ፣ እግዜር ሞገስን ንጉሠ ነገሥቱ ክብርን አልነሱኝም፡፡ ሆኖም አልኮራም፤ እንዴት ልኮራ እችላለሁ? ማነኝና! ትል ለራሴ! ትንሽ ፍጥረት፣ ምናምን! ግን እንደምታየው ራሴን ዝቅ ዝቅ በማድርጌ እግዜርና ንጉሤ ከፍ ከፍ አደረጉኝ በፊታቸው … በሰማያዊ ኃይል የጐለበተ እንዲህ ነው ይኸውልህ… እግዜር ሞገሱን

ሰጥቶ በንጉሤ ፊትም ሞገስ እንዳገኝ አደረገኝ… “… እና አሁን ታዲያ የመጣኸው ትንሽ ዘንጋዳ ለመበደር ነው አልክ…?”

| |
|---|
| **ጥያቄ 1. እስካሁን በቀረበው የምንባብ ታሪክ ተናጋሪው ማን ነው? እንዴት ልታውቁ ቻላችሁ? -----------------------------------------------------------------------------------------------------** <br> **-----------------------------------------------------------------------------------------------------** |

“ነበራ እመየቴ ማስቸገሬ ባይሆን…”

“ለመግዛት ነው የምትፈልገው …?”

“ከየት እቴ እመይቴ ብሩ ከየት ተገኝቶ? በዚያው ባይነት ለመክፍል ነው እንጂ በትሣሥ…”

“ነገር ማሞድሞድ ገንዘብ አይሆንም፤ ይኸውልህ፣ ‘ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው፣ ቀንዱ ይከለክለዋል’ ነው”

“መቼምኮ የሚሉት ሳይገባኝ ቀርቶ አይደለም… ብቻ እንዲያው ሰኔና ሰኞ…”

“አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አያምር፤ ‘በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አያደምቅ ቢበሉበት አያደቅ…’!”

“ታዲያ ምን ተሻለኝ ይመስልዎታል አሁን…?”

“መክልክሌ አይደለምኮ! ‘ሰው ሆኖ የማያብስ እንጨት ሆኖ የማይጨስ’!፣ ‘ሰው ከስህተት ብረት ከዝገት…’

“ታዲያ ያሉትን ብለውኝ ብሄድ…”

ብረት ካልፈላ አይላላ’ ይኸውልህ…

| |
|---|
| **ጥያቄ 2 የአበዳሪዋ ንግግር ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ሀሳባችሁን አብራርታችሁ ፃፉ::-----------------------------------------------------------------------------------------------------** <br> **-----------------------------------------------------------------------------------------------------** |

| |
|---|
| **ጥያቄ 3 ብረት ካልፈላ አይላላ ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ምንባብ አውድስ አበዳሪዋ ምንን ለመግለፅ ተጠቀመችበት? ---------------------------------------------------------------------** <br> **-----------------------------------------------------------------------------------------------------** |

“ድሮምኮ ቢሆን … እንዲያው ባንጣጣም ይሆናል…”

"ያለፈው አለፈ፤ አሁን አንድ ልልህ የምፈልገው… ምን ነበር እቴ! አዎ ለሁሉ እግዚአብሔርን…ማለቴ ከሆነ ወዲያ 'ደም ማልቀስ ድንጋይ መንከስ' አያስፈልግም… 'ወረቱን እንደተቀማ ነጋዴ፣ ዋግ እንደመታው ስንዴ' መዋሰስ የወንድ ልጅ ተግባር አይደለም… ያሁኑ ወራት ስህተትህን ማረሚያ ነው። 'ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ መላጣ' መሻሉን መገንዘብያህ … እንዲያ ተንዠባረህብኝ የነበረው ሰውዬ ቢኖረኝ ነው የመጣኸው … 'ተካር ያየ ተማሪ ሽቀጥ ያየ አጣሪ…'

"የመሄጃ እጦት ነው እመየቴ…"

| |
|---|
| **ጥያቄ 4 ተበዳሪው እስከአሁን ታግሶ መቆየቱ ተገቢ ነበር ትላላችሁ? ምን ማድረግ ነበረበት? ------------------------------------------------------------------------------------------** |
| **------------------------------------------------------------------------------------------** |

"ትዕቢተኛነትህን ትንሽ አብርዶልሃል፤ መቼስ ጨርሶም ባይጠፋ። አዎ! ለወደፊቱ መንገድ ስንገናኝም ቢሆን ከፊትለፊቴ ሽረር ብለህ መንገዱን ብትለቅልኝ ነውር የለውም፤ አንዳንዴ እንደሚማልግ ነብር እንዳንዴ እየተፍረገረገ እንደሚለማመጥ ድመት መሆን ያስተዛዝባል… አዎ ፊት ማጭገግ ወይም መሰንገጭም በእኔ አይደለም… ከግንባርህ ትህትናን አታጥፋ…

| |
|---|
| **ጥያቄ 5 ተበዳሪው የሄደበት ዓላማ ይሳካለታል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ማስረጃችሁ ምንድን ነው? ------------------------------------------------------------------------------------------** |
| **------------------------------------------------------------------------------------------** |

"እመየቴ መቼም ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም…"

"እንዴት አዝን ይመስልሃል እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ…!"

"ታዲያ ታዝኑ…"

"እንዴታ! በርግጥ ታሳዝነኛለህ፤ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ 'ህል ያለው ፈርዛዛ ፣ገንዘብ ያለው ቀበዝባዛ'… የተቻለኝን ባደረግሁልህ… እንደምታውቀው ግን ዘንጋዳው ተወዷል፤ የሚሆንልህ ቢሆን ጥሬው ገንዘብ ይሻለኝ ነበር። ሳት ሆኗል ዘንጋዳ… እንደ ዘንድሮ ሆኖም አያውቅ… ምን ይመስልሃል ታዲያ…? ደግሞስ ደግሞስ ሰማህ ሆይ፣ መረዳዳትን የመሰለ ምን ዓለም አለ? መረዳዳቱ አይከፋም… ዛሬ ባበድርህ ነገ ደግሞ እኔ አበድረኝ ልልህ እመጣ ይሆናል…

**ጥያቄ 6 ሰው ተቸግሮ ብድር ሊጠይቅ ሲመጣ ይሄን ያህል ማንገላታት ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? -----------------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

“ይሆን ይሆን እመየቴ … መቼስ…”

“አይ ይሆናል እንኳ ብዬ አይደለም… “ያልጠረጠረ” ለማለት ያህል ነው… እና ታዲያ አሁን የምትፈልገው አስራ አምስት ቁና መሆኑ ነው…?”

“አዎ እመየቴ ፈቃድዎ ከሆነ…”

“ጥሩ ነው… አስራ አምስት ቁና… ዘጠኝ ቁና እሰጥሃለሁ ማለት ነው፤ በትሣሥ አስራ አምስት አድርገህ ትመልሳለሁ…”

“አይ እኔ እንኳን…”

“እንደምታየው ወለድ አልፈልግም ያው ዓይነት ባይነቱ ነው፣ በብዛት አምርተህ ከምታገባው። አዎ፣ ብዙ አይደለም። ደግሞ በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሰፈርልሃል፤ ‘ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምባ ይጥም’

**ጥያቄ 7. “ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምባ ይጥም” ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? -----------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

“ትንሽ አልበዛም እመየቴ…?”

“በዛ? አይ እንግዲያው ከበዛ ሌላ ሰው ብትጠይቅ ይሻላል። እኔ እስከዚህ የምጓጓለት ነገር አይደለም፤ ስላዘኔታዬ ነው የማበድርህ፡- አንተ መጣህብኝ እንጂ እኔ አልመጣሁብህም…”

“መቼም እመየቴ አዜኔታዎን አልኩ እንጂ…”

“አዘኔታዬ አልተለየህም… ደግሞም ነገር ቢዘበዝቡት ምን ያደርጋል…”

“እርግጥ ነው ብቻ የምመልሰው ትንሽ የበዛ መሰለኝ…”

**ጥያቄ 8 አበዳሪዋ በወለድ እያበደሩ “አዘኔታዬ አልተለየህም” ማለታቸው ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? -----------------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------**

“አይ፣ አይ፣ አይ፣ እንግዲህ በነገር አትጕሸምጠኝ። መንግስት ከፈቀደልኝ በላይ የምወስድብህ አራጣ በሊታ ማድርግህ ነው? አጉል ተናገርክ። እኔ ደሞ ጥንክር ሰው ስትመስለኝ ወስዋሳና ተልካሻ ወጣህ ልበል…?”

| |
|---|
| **ጥያቄ 9. አራጣ በሊታ ማድርግህ ነው? አጉል ተናገርክ፡፡ ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?** |
| **------------------------------------------------------------------------------------------------** |
| **------------------------------------------------------------------------------------------------** |

*"ዋ፣ እመየቴ መቼም ያላቅሜ..."*

*"ምነው ቢገባህ እኔስ በምን ልኑር ትላለህ? ስንት መሰለህ የሚተኮሰው ጉዳዬ... የየቁረንጮው ግብር ራሴን ሊያዞረው ነው፡፡ በዚህ ላይ የሮማን ሠርግ ደርሷል... የየመነኮሳቱ ድርጐ አለብኝ... ስንቱን ልበልህ... አዎ፣ ባይሆን ለወደፊቱ በየቦታው ከማዘጥዘጥ ጠንክር ብሎ መስራት ይኖርብሃል፡፡ 'ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም...'*

*"መቼስ ምን ይደረጋል ይሁና ከጨከኑ ..."*

*"ጭካኔ! የምን ጭካኔ? ጭካኔን ምን አመጣው...? አይ አድራጎቴ ጭካኔ ከመሰለህ ብትተወው ይሻላል..."*

*"ማለቴኮ እመየቴ..."*

*"ሰማሁኮ ያልከውን..."*

*"ይሁና እንግዲያው መቼስ ምን አደርጋለሁ...?"*

| |
|---|
| **ጥያቄ 10 ተበዳሪው "ይሁና እንግዲያው መቼስ ምን አደርጋለሁ...?" በማለት ሳይፈልግ የተስማማው ለምንድን ነው? -----------------------------------------------------------------** |
| **------------------------------------------------------------------------------------------------** |

*"አዎ! እንዲያ ይሻላል... ዘንድሮ አምናን አይደለም፤ የምታደርገው ነገር የለም... "በነገራችን ላይ እኔ ላንተ አንድ ነገር ስውልልህ ፣ አንተም ለኔ መዋል ሳይኖርብህ አይቀርም... የክርስቲያን ምልክቱ ነው፡፡"*

(አደፍርስ፣1965 ከገጽ8-12)

***መመሪያ ሶስት፡- ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

**1. በምንባቡ ውስጥ "ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ" ሲል ምንን ለመግለፅ ፈልጎ ነው? ------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------**

**2. የምንባቡ አጠቃላይ ጭብጥ ምንድን ነው? ------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------**

## ለ. ትምህርት ሁለት

የትምህርት ርዕስ (የግጥሙ ርዕስ) ፡- <u>የክፉት ተጋቦት</u>

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- <u>1:30</u>

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳችሁን በፅሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- በግጥም የቀረበን ሀሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጣችሁ ትጽፋላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፡- ግጥሙን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥለው ለቀረቡት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. **ከግጥምና ከስድ ጽሁፍ አንባቢውን ወይም አድማጩን ይበልጥ የሚስበው የትኛው ነው? ለምን ይመስላችኋል? ----------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
2. **በግጥምና በስድ ጽሁፍ መካከል ያሉ ልዩነቶች ምን ምን ናቸው? -----------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **--------------------------------------------------------------------------------------------------**
3. **"የክፉት ተጋብኦት" ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ በመጥቀስ አብራሩ------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**
   **---------------------------------------------------------------------------------------------------**

# የክፋት ተጋቦት

ከሰል የሚሸጥ ሰው ልብስ አጣቢን አለው፣
ለቤት ኪራይ ብለህ ገንዘብ የምትከፍለው፣
ቀሪ እንዲሆንልህ አብረህ ከኔ ጋራ፣
ኪራይ ሳትከፍል ተቀምጠህ ብትሰራ፣
ቤቱም ይበቃናል አንድነት እንኑር፣
ልብስ አጣቢም ሰምቶ ይህንኑ ምክር፣
አመሰግናለሁ በማሰብህ ለኔ፣
ግን የማይጠቅመኝ ነው ከአንተ ጋር መሆኔ፤
ታጥቦ ታጥቦ ጭቃ የተባለው ተረት፣
እንደሚደርስብኝ አስበህ ተመልከት፣
እኔ የማጥበው ልብስ ከአንተ ከሰል ጋራ፣
ይቆሽሽ የለም ወይ አብረን ስንሰራ፤
ከሰል ለነጭልብስ ነውና ጠላት፣
የማይሆን ሀሳብ ነው ሲል መለሰለት፡፡
ከሰል ለነጭ ልብስ እንደሆነው አጥፊ፣
ከክፉም የዋለ ክፋትን አትራፊ፣
ከመሆን አይድንም ምንም ቢጠነቀቅ፣
ከመጥፎ ጓደኛ ይገባል መራቅ፡፡

(ከበደ ሚካኤል፤ የቅኔ ውበት፤1999፤ ከገፅ 28-29 የተወሰደ)

**መመሪ ሁለት፡- ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡**

1. **ግጥሙን ስታነቡ የተረዳችሁትን የተረዳችሁትን ቁም ነገር በአጭሩ ፃፉ፡፡----------------**

   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

**መመሪያ ሶስት፡- ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ የተሰጣችሁን ግጥም አንብባችሁ መልዕክቱ ሳይዛባ ወደ ስድ ጽሁፍ ለውጣችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ውፍረቱ ክሳቱ ቅጥነቱ ግዝፈቱ፣

ጥቁረቱ ቅላቱ ንጣቱ ግርጣቱ

ማራኪ ገፅታው ማግኘቱ ማጣቱ

መስፈሪው አይሆንም ለሰው ሰውነቱ፡

**ወደ ስድ ጽሁፍ ሲለወጥ፡-**

የአንድን ሰው ማንነት ለመለካት ውጫዊ የሆነው ገጽታው፣ የሰውነት ቅርፁ፣ አቋሙና ሀብቱ ወሳኝ ሊሆን አይችልም፡፡

ግጥም፡- አንድ ነገር አለ ብንመለከት

እንስሳ ከሰው ልጅ የሚበልበት

በሰዎች መካከል ሰካራሞች ሞልተው

እንስሶች ግን መቼም አይሰክሩም ጠጥተው፡፡

ስድ ፅሁፍ፡-------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

## ሐ. ትምህርት ሶስት

የትምህርት (የምንባቡ ርዕስ) ፡- ውቅያኖስ በድንኳ ፕላኔት፣ፕሉቶ

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1፡30

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳችሁን በፅሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቅንጫቢውን በማንበብ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት መልሳችሁን በጽሁፍ ትገልጻላችሁ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- በግጥም የቀረበን ሀሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጣችሁ ትጽፋላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፡- ንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥለው ለቀረቡት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. **በዓለማችን ስንት ፕላኔቶች አሉ? የምታውቋቸውን ዘርዝሩ፡፡------------------------------ ---------------------------------------------------------------------------------------**
2. **የጨረቃ ግርዶሽ የሚፈጠረው እንዴት ነው? ------------------------------------------------ ---------------------------------------------------------------------------------------------------**
3. **የአሜሪካው ብሔራዊ የበረራ ሳይንስና የህዋ አስተዳደር (NASA) ሲነሳ ማንን ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ ታስታውሳላችሁ? ------------------------------------------------**

***መመሪያ ሁለት፡- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

### "ውቅያኖስ በድንኳ ፕላኔት፣ፕሉቶ"

(1) ምድር ከፀሐይ ከምትርቀው 40 ጊዜ እጥፍ ትርቃለች፤ ድንኳ ፕላኔት ፕሉቶ፡፡ ይህች ከፕላኔቶች ወዲያ በርቀት የምትገኘው ድንክ ፕላኔት፡-ለዘመናት እንቆቅልሽ ሆና ቆይታለች፡፡ ከእነ አምስት ጨረቆቿ ከሥርዓተ-ፀሐይ ሽክርክሪት ጠርዝ ላይ ተንሳፋ ምሥጢር ሆና ዘመን ፈጅታለች፡፡ ካለፉት ስድስት ወራት አንስቶ ግን ፕሉቶ በየጊዜው አስደናቂነቷ እየጎላ ነው፡፡

(2) የድንኳ ፕላኔት ፕሉቶ ከርሠ ምድር ለሕይወት አመቺ በሆነ የበረዶ ቅይጥ የውቅያኖስ ውኃ የተሞላ መሆኑን የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ አዲስ አድማስ (New horizone) የተሰኘችው ኅዋ ቃኝ መንኵራኵር ፕለቶ ጥግ ደርሳ ድንኪቱን ፕላኔት ትበረብር ይዛለች፡፡

በበረዶ ግግር በተሞላው ከርሰ ምድሯ ፕሉቶ ከምድር የማይተናነስ የበረዶ ቅይጥ የውቅያኖስ ውኃ ሸሽጋ ኖራለች። ቋጥኞች፣ የበረዶ ግግሮች፤ አሁን ደግሞ የበረዶ ቅይጥ ውኃዋ ተደርሶባታል። ድንኳ ፕላኔት ፕሉቶ።

(3) እንደ ሥነ-ፈለክ እና ጠፈር ተመራማሪዎች ከሆነ ፕሉቶ ከፀሐይ 5.9 ቢሊዮን ኪሎ ሜትር ትርቃለች። እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር በ1930 ዓመት መገኘቷ ይፋ ከተደረገ ወዲህ መጠኗ ብዙ ሲያጨቃጭቅ ቆይቷል። ፕሉቶ ፕላኔት ናት አለያስ ድንክ ፕላኔት ሲሉም ሳይንቲስቱ ሞግተዋል። እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር በ2006 ዓለም አቀፉ ሥነ-ፈለክ ኅብረት (IAU) ፕሉቶን ድንክ ፕላኔት ብሎ ሲሰይም ሦስት መስፈርቶችን በመዘርዘር ነበር።

(4) በደቡብ አፍሪቃ፤ ኖርዝ ዌስት ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪው ዶክተር ጌትነት «አንደኛው መስፈርት ፕላኔቷ በፀሐይ ዙሪያ መሽከርከር አለባት፣ ሁለተኛ የራሷ የሆነ ጠንከር ያለ ስበት ያስፈልጋታል፤ ሦስተኛ በዙሪያው በቅርብ የሚሽከረከሩ ነገሮች መኖር የለባባቸውም» ሲሉ ሦስቱን መስፈርቶችን አብራርተዋል። ሁለቱን መስፈርቶች የምታሟላው ፕሉቶ ሦስተኛውን መስፈርት ስለማታሟላ እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር በ2006 ሳይንቲስቱ ፕሉቶ፦ «ፕላኔት መሆኗ ቀርቶ ድንክ ፕላኔት መሆን አለባት ብለው ወሰኑ» ሲሉም አክለዋል።

| **ጥያቄ 1. ፕሉቶን ድንክ ፕላኔት ብሎ ለመሰየም ያስቻለበት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?** |
|---|
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |

(5) ዶክተር ጌትነት እርስ በእርስ የሚሽከረከሩ ጥንድ ከዋክብት (binary stars) የሽክርክሪት ባሕሪያትን በመቃኘት ጥልቅ ጥናት አከናውነዋል። ፕሉቶ አነስተኛ ከመሆኗ የተነሳ ከፕላኔት ጁፒተር 67 ጨረቆች መካከል ከአንደኛው ትልቁ ጨረቃ እንኳ በመጠን እንደምታንስ ተናግረዋል።



(6) አዲስ አድማስ የተሰኘችው ኅዋ ቃኝ መንኩራኩር ተጠግታ እንደለካችው ከሆነ የፕሉቶ ገሚስ-ክበብ አውታር (diameter) 2370 ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው፡፡ ምናልባትም ከኢትዮጵያ ሰሜናዊ ጫፍ እስከ ናይሮቢ ያለውን ርቀት የሚሸፍን ቢሆን ነው፡፡ ይኽ ርቀት ከምድር አንጻር ሲሰላ 18.5% እንደሚደርስ የዩናይትድስ ስቴትሱ ብሔራዊ የበረራ ሳይንስ እና የኅዋ አስተዳደር (NASA) አስታውቋል፡፡ እንደው በጥቅሉ ፕሉቶ የጨረቃን ሲሶ ብታክል ነው ማለቱ ይቀላል፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 2. በምንባቡ መሰረት የዶ/ር ጌትነት ጥናት ምንን ያመላከተ ነበር? ----------------------**<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------ |

(7) አዲስ አድማስ የተሰኘችው ኅዋ ቃኚ መንኩራኩር እዚህች ድንክ ፕላኔት ምኅዋር ውስጥ ገብታ ለመቃኘት ለዐሥር ዓመት ግድም ከንፋለች፡፡ «ኒውሆራይዘን መንኩራኩር የናሳ ሳተላይት ናት ወደ ኅዋዋም የመጠቀችው እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር በ2006 ነው» ያሉት ዶ/ር ያብባል ታደሰ መንኩራኩሯ ፕሉቶ ጋር «ለመድረስ ረዥም ጊዜ ነው የፈጀባት» ብለዋል፡፡ «ፕሉቶ ጋር ከመጠጋቷ በፊትም ጁፒተር የተሰኘችው ፕላኔት ጋር ተጠግታ በርካታ ዳሠሣዎችን በማከናወን እስከዛሬ የማናውቀውን አዲስ ምስል ልካለች» ሲሉ ገልጸዋል፡፡

(8) ዶ/ር ያብባል ታደሰ ያልታሰሰውን የኅዋ ክፍል ለማጥናት በሚገነባው በዓለም ትልቁ የሬዲዮ ቴሌስኮፕ ላይ ጥናት ለማከናወንም ደቡብ አፍሪቃ ይገኛሉ፡፡ በአውሮጳ የኅዋ ተቋም የጠፈር አፈጣጠር ምሥጢርን ለመፍታት አሠሣ በሚያደርገው የፕላንክ ሳተሊይት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን የሚተነትኑ ሣይንቲስትም ናቸው፡፡ ወደ ፕሉቶ ከዓመታት በፊት የተላከችው መንኩራኩር ፕላኔቶችን እና የኅዋ አካላትን ማጥኛ በርካታ መሣሪያዎች በውስጧ እንደተገጠሙላት ዶ/ር ያብባል ተናግረዋል፡፡

(9) መንኩራኩሯ በነዚህ መሣሪያዎቿ ባነሳችው ምስሎች እና መረጃዎች በመታገዝም ሳይንቲስቱ ስለፕሉቶ ምንነት ጥልቅ ግንዛቤ እያገኙ መኾናቸውን አስታውቀዋል፡፡ በተለይ ፕሉቶ ላይ የታየው የልብ ቅርጽ እና ቻሮን የተሰኘችው የፕሉቶ ጨረቃ ጉዞ አቅጣጫ ጥምረት ተመራማሪዎችን ድንኪቱ ፕላኔት በረዶ ቅይጥ ውኃ አላት የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ አስችሏል፡፡ «ቻሮን ከፕሉቶ ጨረቆች ትልቋ ናት» ያሉት ዶክተር ያብባል የዚህች ጨረቃ እና «ፕሉቶ ላይ የተገኘው የልብ ቅርጽ አቅጣጫ የተጣመረ አለያም የተንሰላሰለ

በመሆኑ ፕሉቶ ውስጥ በረዶ ቅይጥ ውኃ ለመኖሩ ማስረጃ» እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ዶክተር ያብባል የጨረቃዋ እና የፕሉቶ ቅርፅ አቅጣጫ መመሳሰሉ «ሞገድ አለያም ስበት ለመኖሩ ጠቋሚ ነው» ብለዋል፡፡



(10) ፕሉቶን የሚዞሯት አምስት ጨረቆች ናቸው፡፡ ኬርቤሮስ፣ ቻሮን፣ ሃይድራ፣ ኒክስ እና ስቲክስ፡፡ በእነዚህ አምስት ጨረቆች ታጅባ ከሥርዓተ-ፀሐይ ጠርዝ ላይ የምትገኘው ትንሺቱ ፕሉቶ ቅዝቃዜዋ ወደር አይገኝለትም፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ዶ/ር ጌትነት ሲያብራሩ «አንድ ፕላኔት አለያም ድንክ ፕላኔት ከፀሐይ እየራቀ በሄደ ቁጥር እየቀዘቀዘ ነው የሚሄደው» ብለዋል፡፡ «ከጁፒተር ጀምረን፣ ሣተርን፣ ኡራነስ፣ ኔፕቲውን፣ ፕሉቶ እያልን ስንሄድ ቅዝቃዜያቸው በዛው እየጨመረ ነው የሚሄደው፡፡ ያ ማለት ወደ በረዶ የመቀየርም ባሕሪ አለው ማለት ነው፡፡»

(11) በእርግጥም ከፀሐይ በርቀት የምትገኘው ፕሉቶ የተዋቀረችው በበረዶ ግግር ነው ሲሉ ሳይንቲስቱ ይናገራሉ፡፡ «የበረዶ እና የውኃ ቅልቅል አለ ነው የተባለው፡፡ አንዳንዶች የከርሠ-ምድር ውኃ ሲሉ ይጠሩታል፡፡ በብዛት አይታይም፡፡ ከላይ ያለው የፕሉቶ አካል በረዶ የሠራ አካል ነው» ሲሉ ትንታኔ የሰጡት ዶ/ር ጌትነት «ናይትሮጂን፣ ሚቴን እና ካርበን ሞኖክሳይድ ጋዞች ራሳቸው ፕሉቶ ላይ በበረዶ መልክ ነው ያሉት» ብለዋል፡፡ «የውኃው ክፍል ያለው ከነዚህ የበረዶ ግግሮች ስር ከ100 እስከ 200 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገኘው፡፡ ውኃው ክፍል ራሱ ወደታች 100 ኪሎ ሜትር ጥልቀት አለው፡፡»

**ጥያቄ 3. እስካሁን ስለድንኪቱ ፕልቶ ምን ተማራችሁ? በቀጣይ የምንባቡ አንቀፆች ምን ትጠብቃላችሁ? ------------------------------------------------------------------------------------------**

**-----------------------------------------------------------------------------------------------------------**

(12) ድንኪቱ ፕላኔት ፕሉቶን ለማጥናት የተላከችው የናሳ መንኲራኲር መጠነ-ሰፊ መረጃዎችን ወደ ምድር ልካለች፡፡ መንኲራኲሯ ያነሳቻቸውን የምስል ክምችቶች እና ግዙፍ መረጃዎች ወደ ምድር ለመላክ የ15 ወራት ጊዜያት ፈጅቶባታል፡፡ እናም ይኸን ተልዕኮዋን

አጠናቃ ከሥርዓተ-ፀሐይ ውጪ በማቅናት ላይ ትገኛለች፡፡ «ኒው ሆሪዞን ለሁለት ዓላማ ነው የተላከችው» በማለት ዶክተር ጌትነት ያብራራሉ፡፡ «አንደኛው ፕሉቶን ለማጥናት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከፕሉቶ ቀጥሎ 1.6 ቢሉዮን ኪል ሜትር የራቀ ሌላ ኪዩፐር ቤልት (Kuiper Belt object) የሚባል ቁስ አለ፡፡ መንኵራኵሯ ወደዚያ እያቀናች ነው» ብለዋል፡፡



(13) ፕሉቶ ላይ ጥናቷን የጨረሰችው ቃኚ መንኮራኩር የመጨረሻ ግቧን ስትፈጽም እንደሌሎቹ መንኮራኩሮች እንድትከስም አትደረግም፡፡ ይልቁንም ከዚህ ቀደም ጥናታቸውን አከናውነው ከሥርዓተ-ፀሐይ በመውጣት በጥልቁ ኅዋ ላይ እንደተለቀቁት የናሳ ሁለት ሳተላይቶች በራሷ ጊዜ እየተንሳፈፈች እንድትጓዝ ትደረጋለች፡፡ እዛ ከመሄዷ በፊት ግን አንድ የመጨረሻ ግብ ይቀራታል፡፡ «እንደ ጎርጎሪዮስ አቆጣጠር 2019 ላይ ከፕሉቶ ቅርበት ላይ የምትገኝን ሚጢጢ ፕላኔት (asteroids) ታጠናለች» ብለዋል፡፡ ዶክተር ያብባል አክለው ሲገልጡም መንኩራኩሯ «ትሪሉዮን ወደ ሆኑ ቁሶች ወዳለበት ኪዩፐር ቤልትም» እንደምታቀና ገልጠዋል፡፡

(14) አዲስ አድማስ (New horizone) መንኵራኵር ከሥርዓተ-ፀሐይ ውጪ ስትወጣ የፀሐይ ብርኃን በጣም ደካማ ስለሚሆን ያለ ኃይል በዘፈቀደ ነው የምትጓዘው፡፡ እስካሁን በፕሉቶ ምኅዋር ላይ ሆና የሰበሰበችው ግዙፍ መረጃ በሳይንቲስቱ እየተተነተነ ነው፡፡ ምናልባትም 6.5 ጌጋ ባይት መጠን ያላቸው መረጃዎቹ በፕሉቶ ሕይወት ያለው ነገር ስለመኖሩ ወይንም የነበረ ስለመሆኑ ፍንጭ ይሰጡ ይሆናል፡፡ አዲስ አድማስ ግን ለተጨማሪ መረጃ የዓመታት ጉዞዋን ቀጥላለች፡፡ ፍለጋው አያበቃም፡፡

**(ማንተጋፍቶት ስለሺ፣2016)**

**መመሪ ሶስት፡- ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡**

1. ፐልቶ ላይ ጥናቷን የጨረሰቸው አዲስ አድማስ ሆራይዘን የናሳ ቃኝ መንኮራኩር በ2019 እ.ኤ.አ. ስራዋ ምንድን ነው? ---------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

2. ፐልቶን የሚዞሯት ጨረቆች ስንት ናቸው? ዘርዝሩ? ---------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

   ---------------------------------------------------------------------------------------------------

3. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ በአጭሩ ግለፁ፡፡---------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

   -----------------------------------------------------------------------------------------------------

   ---------------------------------------------------------------------------------------------------

# መ. ትምህርት አራት

የትምህርት ርዕስ ፡- አስተዋፅኦ

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1፡30

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- የቀረበላቸችሁን አስተዋፅኦ/ቢጋር በጥሞና ታነባላችሁ፤ በመቀጠልም በቢጋሩ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች አገጣጥማችሁ የተሟላ ድርሰት ትፅፋላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፡- ንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥለው ለቀረቡት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

2. **አስተዋፅኦ/ቢጋር ምንድን ነው? ---------------------------------------------------------------**

   **-------------------------------------------------------------------------------------------**

3. **አስተዋጽኦ ምን ምን ጥቅሞች እንዳሉት ዘርዝሩ፡፡-------------------------------------------**

   **-------------------------------------------------------------------------------------------**

   **---------------------------------------------------------------------------**

## ርዕስ፡- መስከረም ሲጠባ

1. አካባቢው አስደሳች ይሆናል፡፡
   - 1.1. አበቦች ያብባሉ፡፡
   - 1.2. የደፈረሱት ጅረቶች ይጠራሉ፡፡
   - 1.3. በክረምት ተደብቀው የነበሩ አዕዋፍ ብቅብቅ ይላሉ፡፡
   - 1.4. ሰማይው ይጠራል፤ ደመና ይወገዳል፡፡
2. ሰዎች መልካም ምኞታቸውን ይገልፃሉ፡፡
   - 2.1. በዘፈን
   - 2.2. ስጦታ በመለዋወጥ
   - 2.3. እርስ በርስ በመመራረቅና በመመሰጋገን
   - 2.4. በአምልኮ ቦታዎች በመገኘትና ፈጣሪያቸውን በማመስገን
3. ተለያይተው የከረሙ ሰዎች ይገናኛሉ፡፡
   - 3.1. ውሃ ሙላት የለያያቸው ይገናኛሉ፡፡
   - 3.2. በትምህርት ቤት መዘጋት የተለያዩ ተማሪዎች ይገናኛሉ፡፡
4. ሰዎች በአዲሱ ዓመት እቅድ ተልመው ለመተግበር ይዘጋጃሉ፡፡

4.1. ሰራተኛው የተሻለ ለመስራት ያቅዳል፡፡

4.2. ገበሬው የተሻለ ለማምረት ይዘጋጃል፡፡

4.3. ነጋዴው የተሻለ ለማትረፍ ያልማል፡፡

4.4. ተማሪው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ቃል ይገባል፡፡

4.5. ወንደላጤው ትዳር ለመያዝ ይቆርጣል፡፡

4.6. ሱሰኛው ከሱሱ ለመላቀቅ ምላል

(ከቀድሞው የ9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅሀፍ የተወሰደ)

***መመሪያ ሁለት፡- በቢጋሩ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች ገጣጥማችሁ መስከረም ሲጠባ በሚል ርዕስ የተሟላ ድረሰት ፃፉ፡፡***

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------

## ሠ. ትምህርት አምስት

የትምህርት ርዕስ ፡- ምሳሌያዊ አነጋገር

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1:30

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ለምሳሌያዊ ንግግሮች ፍቺ ትሠጣላችሁ፡፡
- ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮችን ታሟላላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፡- የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ቀጥለው ለተሰጡት ምሳሌያዊ አነጋሮች ፍቺ ስጡ፡፡***

**ምሳሌ፡- *ሀ. ታጥቦ ጭቃ* ፡- ከስህተቱ የማይማር (የማይለወጥ) ማለት ነው፡፡**

**ለ. *ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል*፡- በችኮላ የተሰራ ስራ ዘላቂነት የለውም ማለት ነው፡፡**

1. በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
2. የሙት ቀናተኛ ሚስቴን አደራ ይላል፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
3. ውሸትና ስንቅ አያደር ይቀላል፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
4. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
5. እህልን አላምጦ ነገርን አዳምጦ፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
6. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
7. ታጥቦ ጭቃ፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------
8. እባብ ለባብ ይተያያል ካብ ለካብ፡፡
   ------------------------------------------------------------------------------------

9. ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ ነው፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------

10.የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------

*መመሪያ ሁለት፡-* የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ቀጥለው የቀረቡትን ያልተሟሉ ምሳሌያዊ አነጋሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ፡፡

ለ. የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ፡፡

1. ሞኝ ካመረረ ---------------------------፡፡
2. ጠርጥር -----------------------------------፡፡
3. ----------------------ጅማት ለመነኝ፡፡
4. ---------------------------መውጫ አያጣም፡፡
5. ቤተሰሪ -----------------------------፡፡
6. ------------------------------እያደር ይጠራል፡፡
7. ----------------------ለባሏ ዘውድ ናት፡፡
8. ሰርገኛ መጣ ----------------------------፡፡
9. ልጅና ጦጣ -------------------------------፡፡
10. የውሃና የናት ----------------------------፡፡

## ፈ. ትምህርት ስድስት

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፦ መኖር ሰው ገደለ

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፦ 1:30

የትምህርቱ ዓላማ፦

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳችሁን በፅሁፍ ትመልሳላችሁ፡፡
- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፦ ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዩ ቅድመ ንባብ ጥያቄ መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. **የምንባቡን ርዕስ በማየት ስለምን ሊያወራ እንደሚችል በዝርዝር ፃፉ፡፡ ---------------------**

   **---------------------------------------------------------------------------------------------------------**

   **--------------------------------------------------------------------------------------------**

***መመሪያ ሁለት፦ ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

### "መኖር ሰው ገደለ"

(1) ይድረስ ለእናቴ ለወ/ሮ ግምጃ ስላሴ፤ እማይዬ ለጤናሽ እንደምን ከርመሻል? ... እኔ እንዳለሁ አለሁት፡፡ ሰሞኑን በጥሩ ሁናቴ ላይ አይደለም ያለሁት፡፡ አዲስ ነገር ስለገጠመኝ ነው ይሄንን አሳዛኝ ደብዳቤ ዛሬ የፃፍኩልሽ፡፡ ካንቺ ከናቴ በላይ ማን በዚህ ክፉ ሰዓት ከጎኔ ሊቆም ይችላል? ... የጭንቀቴ ተካፋይ ትሆኚና ከዚህ ጉድ ውስጥ ታወጪኝ ዘንድ እምነቴ ነው እማምዬ፡፡ የሆንኩትን ስትሰሚም እንዳትበሳጪ፣ እንዳታዝኚም አስቀድሜ እለምንሻለሁ፡፡ ይሄውልሽ እንዲህ ሆነ እማምዬ... ባለፈው ሳምንት አንድ የሉካንዳ ቤታችን ደምበኛ የጎረሰው ስጋ አንቆት ከሞተ በኋላ፣ የፍቼ ሰው ሁላ በክፉ ዐይኑ ያየኛል፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 1. በክገፉ አይኑ ያየኛል ሲል ምን ማለቱ ነው? አብራርታችሁ ጻፉ፡፡ ------------** <br> **------------------------------------------------------------------------------------------------------** <br> **-----------------------------------------------------------------------------------** |

(2) ሰውየው ከሞተበት እለት ጀምሮ ወደ ሉካንዳ ቤታችን የሚገባው ሰው ቁጥር ቀንሷል፡፡ ወሬውን ያልሰሙ አንዳንድ ሰዎች ብልት ብልቱን እየጠያየቁ፣ ከስንት አንዳንዶቻቸው ብቻ አስጠቅልለው ይሄዳሉ፡፡ የገዛውን *ሥጋ* እራሱ መሽከም የተጠየፈውን ደሞ እንደተለመደው እኔኑ አሸክሞኝ ከኋላ ኋላው ያስሮጠኛል፡፡ ጥቂቶቹ ትንሽ ሳንቲም ቢጥሉልኝም፤ አብዛኞቹ ግን በነፃ ነው የሚያሸክሙኝ፡፡ "… ልጄ በርታና ትምህርትህን ተማር …" ያልሸኝን ሁሌም ስለማልረሳ፣ የጋሽ ቶልቻን ቁጣ አዘል ትእዛዝና የሥራ ጫናውን እንግልት እየቻልኩ ፤ በማዝገም ላይ ነኝ፡፡

(3) እማምዬ ሰሞኑን የሚሰማኝን ጭንቀት የሚያብስብኝ፤ ይሄ *ሥጋ* አሸክሞ ከኋላ ኋላው የሚያስሮጠኝ ሁሉ ድንገት ቆም ብሎ፤ "መኖር ማለት አንተ ነህ? ሰውየውን ለምን ገደልከው? …" ብሎ የሚያፋጥጠኝ እየመሰለኝ፤ ሰውነቴ በሀሳብ እልቅ ይላል፡፡ አንዳንዱም የገዛውን *ሥጋ* እቤት ደርሶ ለመብላት ካለው ጉጉት የተነሳ ተካልቦ ሲያካልበኝ፣ ሮጦ ሲያስሮጠኝ፤ ምናልባት የዚያ የሟቹ ሰውየ ዘመድ ሁኖ ተቤቱ ስደርስ ቢበቀለኝስ ብየ ማሰቤና መጨነቁም አልቀረም፡፡

(4) የእኔ እማዬ ይሄ ዓይነቱ ክፉ አሳብ ከራሴ ላይ የሚራገፈው፤ *ሥጋ*ውን ያሸከመኝ ሰውየ ከቤቱ እንደደረስን፣ የኔን መፈጠር ረስቶ ያንን የገዛውን *ሥጋ* ከጠረጴዛ ላይ አጋድሞ፤ " ቶሎ በይ! … ቢላ አምጪ! …" እያለ በሚስቱ ላይ የትእዛዝ ናዳ ሲያወርድና፤ አስሬ ምራቁን እየዋጠ እጆቹን ሲያፋትግ ሳይ ነው፡፡ ይሄኔ ቀስ ብየ ዘንቢሌን አንጠልጥየ እሾልክና ወደ ሉካንዳ ቤቱ እፈረጥጣለሁ፡፡ ግና ምን ያደርጋል! ምን ያህል ራሴን ሰውሬ ስርቻ ለስርቻ እየተሸለኮሎኩ ብጓዝም፤ ወሬኛው ሁላ ሲያየኝ "ያውና ያ ሰውዩውን የገደለው ልጅ! …" እያለ መንገድ አላስኬድ ይለኛል፡፡ ይሄኔ ያው እንደተለመደው የሆድ ብሶቴን በእምባየ እበሳ እየተወጣሁ፤ ግራና ቀኝ ሳልገላመጥ ወደ ሉካንዳ ቤቱ እሽመጥጣለሁ፡፡

**ጥያቄ 2. የሆድ ብሶቴን በእንባዬ እበሳ እየተወጣሁ የሚለው አባባል ምን ማለት ነው? አብራርታችሁ ጻፉ፡፡ --------------------------------------------------------------------**
**-----------------------------------------------------------------------------------------------**
**-----------**

(5) እማምዬ አንቺ አይደለሽ “ ሰው መርዳት ጥሩ ነው፣ የደከመን ማገዝ ያስፈልጋል፣ ከመርዳት ምርቃት ይገኛል” ብለሽ የምትመክሪኝ? እማምዩ ሰው መርዳቴ ግን ለኔ እርግማን ነው የሆነብኝ፡፡ ጉድሽን አላወቅሽም ለካ! ሰውየው እንደሞተ እስር ቤትም ልገባልሽ ነበር እኮ! ይህ እጀ ቆራጣ ደንበኛው ጋሼ ቶልቻ ጋ መጥቶ ጥሬ ስጋ አስቆረጠና ተቀመጠ፡፡ “ሂድና እየቆረጥክ አጉርሰው” አለኝ ጋሼ ቶልቻ፡፡ ረዳሁት፡፡ ሰውዬው ሥጋውን አላኘከው ኖሮ ከጉሮሮው ተወተፈ፤ ዐይኔ እያየው ተንፈራፍሮ ሞተ፡፡ እማምዬ እኔ ልገድለው አላጎረስኩትም፡፡ ሰው ግን ዐይንህን ለአፈር አለኝ፡፡ ፖሊስ ወደ ቤትህ ሂድ አለኝ እንጂ እዚያው አስረውኝ ባቆዩኝ ኖሮ እላለሁ፡፡ የሰው ዐይን ማየት ፈራሁ፡፡

(6) ሰውዬው ታንቆ እንደሞተ የተፈጠረውን ግርግርና የደረሰብኝን እንግልት ብታይ እማምዬ ሐዘኑን አትችይውም ነበር፡፡ እንኳንም በአጠገቤ አልኖርሽ፡፡ ሰዎች ጭራሽ የኔ ያልሆነ ታሪክ ፈጥረውልኝ መድረሻ እስኪጠፋኝ አሸማቀቁኝ፣ ዛቱብኝ፡፡ ሰው ከቦኝ እንደዚያ ልዩ አውሬ አርጎኝ ሲራገም ብታይ እማምዬ፣ ስለሞተው ሰውዬ ሳይሆን ስለኔ ብለሽ ልብሽ በሀዘን ይሰበር ነበር፡፡ እንዲያው ምን ብለውት ይሆን እንዲህ ልጄ የተማረረው ብለሽ እንዳታሰላስይ የማስታውሰውን ጥቂቱን ላካፍልሽ፡፡ አንቺን ለማሳሰብ ብዬ ሳይሆን እንዲያው የደረሰብኝን የልብ ስብራት የማካፍለው ሰው ስላጣሁ ነው፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 3. የእስካሁኑን የታሪክ ክፍል እንዴት አገኛችሁት? ወደፊትስ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል? ---------------------------------------------------------------------------------**<br>**-------------------------------------------------------------------------------------------------------**<br>**-------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(7) ይሄውልሽ አደጋው የደረሰ እለት አንድ ግብዳ የሚያህል መዳፍ ማጅራቴን ጨምድዶ እንደያዘኝ ልብ አላልኩም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሰማይ ምድሩ ዞሮብኛል፡፡ የሟቹን ሰውዬ አስከሬን አምቡላንስ ወደ ፍቼ ጤና ጣቢያ ሲወስደው፣ እኔን ጨምድዶ የያዘኝ መዳፍ ደሞ እያዳፋ ከቀበሌ አደረሰኝ፡፡ ቀበሌም ተቀብሎ ለፖሊስ ጣቢያ አሳለፈኝ፡፡ እኔ ከፖሊስ ጣቢያው ደጃፍ ቆሜ፤ ፍርሀት ሰቅዞ እያርገፈገፈኝ ነው፡፡ አላፊ አግዳሚው በዓይንና በአፉ አሟሸኝ፡፡ መላ ምቱን የማያሰላብኝ፣ የማይተቸኝ፣ የማይረግመኝና የማይሰድበኝ የሰው ዓይነት አልነበረም፡፡ ምን ያልተባልኩት ነገር አለ?

| |
|---|
| ጥያቄ 4. አላፊ አግዳሚው በዓይንና በአፉ አሚሽኝ ሲል ምን ማለቱ ነው ? ------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------ |

(8) "አንድ ፍሬ ልጅ እኮ ነው! … ምን ዓይነቱ ጨካኝ ቢሆን ነው አቦ?!..." ይለኛል አንዱ "ጨካኝ ብቻ ትላለህ እንዴ?... አሪዮስ የሰይጣን ቁራጭ እንጂ! " ይላል ሌላው "ይሄ አውሬ ነው እንጂ፣ ከሰው ዘር የተፈጠረም አይደል … አሲዳም!" ይቀበላል ሌላው ተራጋሚ "እቆራጣ እጁ ላይ በተንዘለዘለው እጅጌው ነው አሉ አንቆ የገደለው …" ይላል ደሞ ሌላው። "የለም የለም!... በካራ ወግቶ ነው፣ ይሄ ሸንፍላ ገልባጭ ጥጋበኛ!" ይመልሳል ሌላኛው "ይሆናል! ይሆናል!... ወግቶ ነው፣ አንገት ላንገት ተናንቆስ ትልቁን ሰውዬ ሊገለው አይችልም ! " "ጥጋበኛ ብጤ ነው ያስታውቃል!... ዓይኞቹን ደም አስለብሶ ሲያጉረጠርጥ አታየውም... " እንዲህ እንዲህ እያሉ ነው የተቀባበሉኝ። እኔ ግን ተግራና ተቀኝ የሚሰነዘርብኝን ትችትና እርግማን በሰማሁ ቁጥር ይበልጥ ጨነቀኝ። ከመደንገጤም የተነሳ ያ አንቺ የምታደንቂው ጠይሙ የገጼ ቀለም ተለውጦ አመድ የተነፋበት ቁርበት መምሰሉ ይሰማኝ ነበር። ከሰውነቴም ላይ ሙዳ ሙዳ ሥጋ የተነሳለት ነበር የሚመስለኝ።

(ምንጭ፡- የነገ ናፍቆት፣ ገፅ 80-83)

***መመሪያ ሶስት፡- ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ።***

**1. ተግራና ተቀኝ <u>የሚሰነዘርብኝን</u> ትችትና እርግማን በሰማሁ ቁጥር ይበልጥ ጨነቀኝ። በሚለው ሀሳብ ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው? ---------------------------**

----------------------------------------------------------------------------------------------------

**2. በምንባቡ ውስጥ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው የዘይቤ ዓይነት የትኛው ነው? ምሳሌ በመስጠት ግለፁ?------------------------------------------------------------------------------------------**

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

**3. የምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ምንድን ነው? ----------------------------------------------------**

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------

## ሰ. ትምህርት ሰባት

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፡- ዋንጫውና ጠጁ

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1:30

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ መልሳችሁን በፅሁፍ ትመልሳላችሁ፡፡
- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፡- ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዮቹ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. ***ዋንጫ ከምን ከምን ይሰራል? ለምን አገልግሎትስ ይውላል? በዝርዝር ጻፉ፡፡*** ----------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
2. ***ሰዎች አዲስ ዓመትን እንዴት እንደሚያከብሩ በጽሁፍ አብራሩ፡፡*** ----------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ ሁለት፡- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

### "ዋንጫውና ጠጁ"

(1) አንድ ባለቅኔ አንድ ድግስ ላይ ተጠርተው በመሄድ ገበታ ላይ ይሰየማሉ፡፡ ጠጅ አሳላፊው ይመጣና በተሰነጠቀ የሸክላ ዋንጫ ጠጅ ይቀዳላቸዋል፡፡ እያዘኑ ተቀብለው ጠጁን ቀመስ ያደርጉታል፡፡ "ከመ ወይን ጣዕሙ!" የሚባልለት ዓይነት ነው፡፡ ጠጁንና የቀረበበትን ዋንጫ አስተያይተው "ዋንጫው በጠጁ ከብሯል፣ ጠጁ ግን በዋንጫው ተዋርዷል፣ ዋንጫው ጠጁን ይዞ ይስቃል፣ ጠጁ ግን ዋንጫው ውስጥ ገብቶ ያለቅሳል፡፡" የሚል ቅኔ ተቀኙ ይባላል፡፡ ያ ሰባራ ዋንጫ ያንን ለመሰለ ምርጥ ጠጅ መጠጫ መሆኑ የማያገኘው ክብርና ዕድል ነው፤ እንደ ባሕሉ ቢሆን የተሰነጠቀ ዋንጫ የቅራሪ መጠጫ ከመሆን ያለፈ ክብር አልነበረውምና፤ ለጠጁ ግን በሰንጣቃ ዋንጫ መቅረቡ ውርደት ነው፡፡ እንዲህ ያለው ጠጅ ሲሆን የወርቅ፣ ሲቀር ደግሞ የቀንድ ዋንጫ ይገባው ነበር፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 1. "ከመ ወይን ጣዕሙ!" ማለት ምን ማት ነው? -----------------------------------** |
| **-----------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(2) አንዳንድ የኢትዮጵያ ጉዳዮች ከኢትዮጵያ ክብር ጋር በማይመጥኑ ሰዎች እጅ ወድቀው ሳይ የእኒህ ሰውዬ ቅኔ ትዝ ይለኛል፡፡ ለነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያን የምታህል የታሪክ ሀገር፣ የቅርስ ሀገር፣ የነጻነት ሀገር፣ የጥበብ ሀገር፣ የጀግኖች ሀገር፣ የልዩ ልዩ ባሕሎችና ወጎች ሀገር በእጃቸው መግባቷ በሥዕለት የማያገኙት ክብራቸው ነው፤ ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናትና፡፡ ለኢትዮጵያ ግን በእነዚህ በማይመጥኗት ሰዎች እጅ መውደቋ ውርደቷ ነው፤ እነርሱ ሲስቁ፣ ኢትዮጵያ ታለቅሳለች፡፡

(3) "የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ጳጉሜ 5/6 እኩለ ሌሊት አይገባም፡፡" የሚለውን መስማት የማይፈልጉ ሰዎች ጊዜውና ሁኔታው ፈቅዶላቸው ጣፋጯ ጠጅ ኢትዮጵያ እንደ ሰባራው ዋንጫ በእጃቸው ስለገባችላቸው ብቻ ሲያወርዷት አየናቸው፡፡ የእጅ ሰዓታቸው ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት እያለ፣ በሥልጣናቸው ከጠዋቱ 12 ሰዓት አደረጉት፡፡ ወይ አይረዱ ወይ አያስረዱ፤ ሰው እንዴት ከሁለቱም ይወጣል! ወይ እኩለ ሌሊት "አዲስ ዓመት ገብቷል" ሲሉ መከራከሪያውን አምጥቶ ማስረዳት ያለበለዚያ ደግሞ የሚቀርበውን መከራከሪያ መቀበል አለባቸው፡፡ የኢትዮጵያ ዕለት በእኩለ ሌሊት ይገባል ከተባለ፣ በእኩለ ሌሊት የሚገባው መስከረም 1 ቀን ብቻ ነውን? ለምን መስከረም ሁለትስ በእኩለ ሌሊት አይገባም?

| |
|---|
| **ጥያቄ 2. የእስካሁኑን የታሪክ ክፍል እንዴት አገኛችሁት? ወደፊትስ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል? -----------------------------------------------------------------------------** |
| **-----------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(4) ሞቅታ ዕውቀትና እውነትን እየሻረ እስከመቼ መጓዝ ይቻላል? ሀገር ከፍ የምትለው በጭፈራና በሆታ አይደለም፤ በእውነትና በዕውቀት እንጂ፡፡ ችግሩ ግን አሁን ኢትዮጵያ በእጃቸው የገባችላቸው አንዳንድ ሰዎች እውነትም ዕውቀትም የማይፈልጉ መሆናቸው ነው፡፡ ዕውቀት ወደ እውነት፣ እውነትም ወደ ቆራጥነት ይመራልና፡፡ አውሮፕላኑን አብርር ተብሎ ሲሰጥህኮ በተፈቀደልህ ከፍታ፣ በተፈቀደልህ ፍጥነት፣ በተፈቀደልህ ሕግ

*መሠረት፣ ወደተፈቀደልህ ቦታ፣ አብርር ማለት እንጂ መሪው እጅህ ስለገባ ብቻ ወደፈለግከው ቦታ በፈለግከው መንገድ ይዘህ መሄድ አትችልም።*

(5) ሌሊት እንጨፍር፣ ሌሊት ርችት እንተኩስ፣ ሌሊት እንጠጣ ማለት ይቻላል። የእነርሱ ጭፈራ፣ የእነርሱ አሥረሽ ምችውና ርችት እንዲያምር ስለተፈለገ ግን የኢትዮጵያ ታሪክና ቅርስ መናድ የለበትም። የኢትዮጵያ ሚሊኒየም የተከበረበትን አስረኛ ዓመት አከበርን እያልን በሚሊኒየሙ ጊዜ ስናወድሰው የነበረውን ቅርስ ማበላሸት አለብን? ያኔ "ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ሀገር ናት" ስንል አልነበረም እንዴ? ዛሬ በአስር ዓመቱ ረስተነው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በእኩለ ሌሊት ለምን ዘመኑን አባትነው? መሠረቱን እያፈረሱስ ከፍታ እንዴት ይገኛል? መቀየርም ካስፈለገ ለተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ፣ በምክንያት መቀየር የሚችለው የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስቴር በሥልጣኑ ይህን የኢትዮጵያ ታሪክ ለምን አባሪ ተባባሪ ሆኖ ሊቀይር ፈለገ? ዕውቀት ሥልጣንን ይሰጣል፤ ሥልጣን ግን ዕውቀትን አይሰጥም። ጊዜ ሥልጣን ይሰጣል እንጂ ዕውቀት አይሰጥም። ለዚህም ነው "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል" የተባለው።

**ምንጭ፡- ዳንኤል ክብረት (ዓ.ም ያልተገለፀ፣ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)**

**መመሪያ ሶስት፡- ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ።**

**1. በምንባቡ ውስጥ "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል" ተብሎ የገባውን ምሳሌያዊ አነጋገር ፍቺ ምሳሌ በመስጠት በፅሁፍ አብራሩ።---------------------------------------------------**

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

**2. ታሪኩን በአንድ አንቀፅ አሳጥራችሁ ጻፉ።-------------------------------------------------------**

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

## ሸ. ትምህርት ስምንት

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፡- ንጉሱና ሞት

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1:30

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳችሁን በፅሁፍ ትመልሳላችሁ፡፡
- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ትሰጣላችሁ፡፡

***መመሪያ አንድ፡- ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዩ ቅድመ ንባብ ጥያቄ መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. **ሞት ምንድን ነው? ሰዎች ለምን ሞትን ይፈራሉ? ------------------------------------------ ---------------------------------------------------------------------**

***መመሪያ ሁለት፡- ከቀደመ ልምዳችሁና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

### "ንጉሡ እና ሞት"

(1) "አንቺ ዓለም አንቺ ዓለም፣ የጀመረሽ እንጂ የጨረሰሽ የለም!" ብሩህ አእምሮ ካለህ የስግብግብነትን ዋጋ ቢስነት ትረዳለህ፡፡ ብሩህ አእምሮ ካለህ ዛሬን ለነገ ስትል አትሰዋም፡፡ ይህን ቅፅበት ለሌላ ቅፅበት ብለህ አትሰዋም፤ ይህን ቅፅበት ሙሉ ለሙሉ ትኖረዋለህ እንጂ፡፡ ለአንድ ሺህ ዓመታት ብትኖርም እንኳ ፍላጎቶችህ መቼም ቢሆን አይሟሉም፡፡

(2) ሕንድ ውስጥ አንድ የሚያምር ታሪክ አለ፡፡ ታላቁ ንጉሥ፣ ያያቲ መሞቻቸው ቀን ደርሶ ሞት ያያቲ ዘንድ በመምጣት የያያቲን በር አንኳኳ፡፡ ያያቲ በሩን ሲከፍት ሞት በሩ ላይ ቆሟል፡፡ "ምን?" አለ ያያቲ፣ "ገና መቶ አመት እኮ ነው የኖርኩት! አንተ ግን እነሆ በሬ ላይ ቆመሃል፤ ያውም ያለምንም ማስጠንቀቂያ! ቢያንስ ቢያንስ የተወሰነ ጊዜ ልትሰጠኝ ይገባል፡፡ አሁንም እውነተኛ ፍላጎቶቼን አላሳካሁም፡፡ ከዛሬ ነገ አደርገዋለሁ ስል ይሄው ከች አልክ! በእውነቱ ይሄ ጭካኔ ነው! እባክህን እዘንልኝና የተወሰነ ጊዜ ጨምርልኝ" "የፈለገ ነገር ቢሆን ባዶ እጄን መሄድ እንደማልችል ግን ልታውቅ ይገባሃል! የሆነ ሰው ይገኘ መሄድ አለብኝ! እሺ ይሁን መቼም አንድ መቶ አመት እጨምርልሃለሁ፡፡ ግን ከልጆችህ መሃል አንዱ ከእኔ ጋር መሄድ አለበት፡፡" አለ ሞት፡፡ "ይሄ ችግር የለውም፤ ቀላል ነው!" አለ ያያቲ፡፡

ጥያቄ 1. የንጉሱን ውሳኔ እንዴት አገኛችሁት? እናንተ በንጉሱ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር? ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ጥያቄ 2. ልጆቹ በአባታቸው የሀሳብ የሚስማሙ ይመስላችኋል? ምክንያታችሁ ምንድን ነው? ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

(3) *ያያቲ ከመቶ ሚስቶቹ መቶ ልጆች አሉት፡፡ ግን እንዳሰበው ቀላል አልሆነም፤ መቶዎቹንም ልጆቹን ጠርቶ "ከመሃከላችሁ ማነው በእኔ ፋንታ ከሞት ጋር የሚሄድ?" አላቸው፡፡ "…የሽማግሌ አባታችሁን ሕይወት ልትታደጉ ይገባል!" አለ ያያቲ፣ "ብዙ ጊዜ ‹አባዬ ላንተ እንሞታለን› ስትሉኝ አልነበረም? ይሄው ጊዜው ደረሰ! ቃላችሁን የመፈፀሚያው ጊዜ አሁን ነው፡፡" ግን ያው እንደሚታወቀው እንደዚህ አይነት ነገሮች ሁሌም ይባሉ የለ! ልጆቹ እርስ በእርስ መተያየት ጀመሩ፡፡ አንዱ ሰባ፣ አንዱ ሰባ አምስት፣ ሌላኛው ስልሳ ዓመታቸው ነው፤ ልጆቹም ራሳቸው አርጅተዋል፡፡*

(4) *ከልጆቹ መካከል ወጣቱ ሃያ አመቱ ነው፡፡ ወጣቱ ልጅ ብድግ አለና፣ "እኔ ከሞት ጋር ለመሄድ ዝግጁ ነኝ!" አለ፤ ማንም ሊያምን አልቻለም፡፡ ዘጠና ዘጠኙም ወንድሞቹ ሊያምኑ አልቻሉም፤ "ይሄ ልጅ ሞኝ ነው ማለት ነው!" አሉ፡፡ አልኖረም እኮ! መቼ ኖረና ነው? ገና ሃያ ዓመቱ ነው፡፡ ገና መኖር መጀመሪያው ጊዜ አይደለ እንዴ! ሞት ራሱ አዝኖ ጭንቅላቱን ነቀነቀ፡፡ ልጁን ከወንድሞቹ መሃል ይዞት ወደ ጎን ወጣና በጆሮው፣ "ምን አይነት ጅል ነህ ግን? ረጅም ዓመት የኖሩት ወንድሞችህ እንኳ ለመሄድ ሳይፈልጉ አንተ ምን ቤት ነህ? ሰባ አምስት ዓመት የኖረው አልሄድም ብሎ አንተ ምን ልሁን ብለህ ነው የምትሄደው! መች ኖርክና ነው! ሕይወትን መች አጣጣምካት? መቶ ዓመት የኖረው አባትህ መሞት አይፈልግም፡፡ እና አንተ ምን ልሁን ብለህ ነው ገና በለጋነትን ለመሞት የወሰንከው?" በማለት ጠየቀው፡፡*

| |
|---|
| **ጥያቄ 3. ወጣቱ በሞት ምክር ሀሳቡን የሚቀይር ይመስላችኋል? ለምን? ------------------------** <br> **------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(5) ወጣቱ ልጅም የሞትን ንግግር ካዳመጠ በኋላ እጅግ በጣም ውብ እና ትልቅ ዋጋ ያለው ቁም ነገር ተናገረ፡፡ ወጣቱ እንዲህ አለ፣ "አባቴን ሳይ፣ አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባው ነገር ሁሉ ኖሮት፣ መቶ ዓመት ኖሮም እንዳልጠገበ፣ እንዳልረካ ስረዳ የሕይወትን ዋጋ ቢስነት ተረዳሁ፡፡ ምን ዋጋ አለው? እኔም መቶ ዓመት ብኖር የሚለወጥ ነገር የለም፤ ሁኔታው ያው ነው የሚሆነው፡፡ ይሄ ነገር አባቴ ላይ ብቻ ቢሆን ኖሮ 'የእሱ የተለየ ነው' ብዬ ልተወው እችል ነበር፡፡ ግን ደግሞ ሰባ፣ ሰባ አምስት፣ ስልሳ፣ ስልሳ አምስት የኖሩት ወንድሞቼም ብዙ ዓመት ኖረዋል፤ ደስታ የሚባለውንም ሁሉን አጣጥመዋል፡፡ እና ምን ቀራቸው? ያለውን ደስታ ሁሉ አጣጥመው አርጅተዋል፤ ግን አሁንም አልረኩም፡፡ ስለዚህ በአንድ ነገር እርግጠኛ መሆን ይቻላል፤ በዚህ መንገድ መርካት አይቻልም! ስለዚህም አብሬህ ለመሄድ ዝግጁ ነኝ፡፡ ተስፋ በመቁረጥ ሳይሆን በጥልቅ መረዳት አብሬህ እሄዳለሁ፡፡ በታላቅ ደስታ ተውጬ ነው አብሬህ የምሄደው፡፡ አባቴ ባለፈበት በዚህ ስቃይ ውስጥ የመቶ ዓመት ያለመርካት ሕመም ውስጥ ሳልዘፈቅ ይሄን እድል በማግኘቴ በታላቅ ደሰታ ነው አብሬህ የምሄደው፡፡ አባቴ ገና ነገሩ ስላልገባው ካንተ ጋር ለመሄድ ብቁ አይደለም" በማለት ተናገረ፡፡

| |
|---|
| **ጥያቄ 4. በልጁ ሀሳብ ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? ምክንያታችሁን በአጭሩ ግለፁ፡፡-** <br> **------------------------------------------------------------------------------------------------------------** <br> **----------------------------------------------------------------------------------------------------------** |

(6) እንደገና መቶ ዓመት ሸው ብሎ አለፈ፤ ሞትም በቀጠሮው መሰረት ዳግም የያያቲን በር አንኳኳ፡፡ ያያቲ መቶ ዓመት እንደዘበት ማለፉን የተረዳው ሞት በሩን ሲያንኳኳ ነው፡፡ "ከመቼው ደግሞ መጣህ? ኧረ እባክህ አሁንም ገና ነኝ፤ ዝግጁ አይደለሁም!" አለ ያያቲ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ በየመቶ ዓመቱ በእሱ ፋንታ አንድ ልጅ ከሞት ጋር እየሄደ ያያቲ አንድ ሺህ ዓመት ኖረ፡፡ ከአንድ ሺህ ዓመት በኋላ ሞት ያያቲ ዘንድ መጣና፣ "እህ! እንዴት ነው? አሁንስ ምን ታስባለህ?" "አይይ! አሁንስ እመጣለሁ!" አለ ያያቲ፣ "ምንም ዋጋ የሌለው ነገር ነው! እዚህ ዓለም ላይ ምንም ነገር መቼም እንደማይሞላ ገብቶኛል፡፡ ፍላጎት መቼም አያልቅም፤ አንዱን ፍላጎት ስታረካ ሌላ አስር ተፈጥሮ ያድራል፡፡ አሁን በፍቃዴ አብሬህ እሄዳለሁ፡፡ ያ በሀያ ዓመቱ ካንተ ጋር የሄደው ልጄ ምን አይነት ብልህ ልጅ ነበር! እኔ ግን

የለየልኝ ደደብ ነበርኩ! እኔ በአንድ ሺህ ዓመት የገባኝን እሱ በሀያ ዓመቱ ገባው፡፡ ይሄ ነው ብሩህ አእምሮ ማለት! ብርሃናማ ልብ ማለት!" በማለት መለሰለት፡፡

(7) ብሩህ አእምሮ ካለህ የስግብግብነትን ዋጋ ቢስነት ትረዳለህ፡፡ ብሩህ አእምሮ ካለህ ትኖራለህ እንጂ ለመኖር አትዘጋጅም፡፡ ስግብግብነት ለመኖር መዘጋጀት ነው፤ ለመኖር የምትዘጋጀው መቼ ልትኖር ነው? ብሩህ አእምሮ ካለህ ዛሬን ለነገ ስትል አትሰዋም፡፡ ይህን ቅፅበት ለሌላ ቅፅበት ብለህ አትሰዋም፤ ይህን ቅፅበት ሙሉ ለሙሉ ታጣጥመዋለህ፣ ትኖረዋለህ፡፡ የዚህችን ቅፅበት ወለላ ጨምቀህ ትጠጣለህ፣ ትኖራለህ፣ ታጣጥማለህ፡፡

**ምንጭ፡- ግሩም አበጀ (ከድረ ገፅ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)**

***መመሪያ ሶስት፡- ቀጥለው ለቀረቡት ድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ፡፡***

1. ***የሀያ አመቱ ወጣት ልጅ በአባቱ ፋንታ ለመሞት እንዲወስን ያደረገውን ነገር ማስረጃ በማቅረብ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡***---------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
2. ***ንጉሱ ያያቲ በስድስተኛው አንቀፅ የገለፀውን ሀሳብ በራሳችሁ አገላለፅ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡***------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
3. ***ንጉሱ ያያቲ በስድስተኛው አንቀፅ የገለፀውን ሀሳብ በራሳችሁ አገላለፅ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡*** ------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
4. ***በምንባቡ ሀሳብ መሰረት አንድ ሰው ብሩህ አእምሮ ሲኖረው ምን ምን አይነት ተግባራትን እንደሚያከናውን በራሳችሁ አገላለፅ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡***---------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ አራት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ለሙከራ ቡድኑ የተዘጋጀው የምንባብ ትምህርት የመምህሩ መምሪያ

## ሀ. ትምህርት አንድ

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፡- ያበዳሪዋ ጫና

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1:30

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳቸውን በፅሁፍ ይመልሳሉ፡፡
- ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

- ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- “የአበዳሪዋ ጫና” በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡
- ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-**

ማንበብ፣ መገመት፣ ዳራዊ እውቀትን መጠቀም፣ ማንፀባረቅ፣ በጥልቀት ማሰብ፣ ማጠቃለልና መፃፍ

**መርጃ መሳሪያ፡-**

ዳኛቸው ወርቁ (አደፍርስ)

**ግምገማ፦**

የቀረበውን ቅንጫቢ ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ማንበባቸውን፣ በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ መስጠታቸውን፣ መልሱን እንደገና አስተካክለው መፃፋቸውን ማረጋገጥ፡፡

# ለ. ትምህርት ሁለት

የትምህርት ርዕስ (የግጥሙ ርዕስ) ፦ <u>የክፉት ተጋቦት</u>

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፦ <u>1:30</u>

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- በግጥም የቀረበን ሀሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጠው ይጽፋሉ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፦**

- ቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- የታደላቸውን ግጥም ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡
- ግጥሙን አንብበው ያገኙትን ቁም ነገር በጽሁፍ ይገልጻሉ፡፡
- የግጥሙን ሃሳብ በአጭሩ በዝርው ይፅፋሉ፡፡ የፃፉትን ሀሳብ ከቡድን አጋራቸው ጋር በየተራ በማንበብ ከተወያዩበት በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፦**

ማንበብ፣ ማጠቃለል፣ ማብራራትና መተንም፣ ዳራዊ እውቀትን መጠቀም፣ ማንፀባረቅና መፃፍ

**መርጃ መሳሪያ፦**

ከበደ ሚካኤል (የቅኔ ውበት)

**ግምገማ፦**

የታደላቸውን ግጥም ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ማንበባቸውን፣ ከምንባቡ ያገኙትን ቁም ነገር በጽሁፍ መግለፃቸውን፣ የግጥሙን ሃሳብ በአጭሩ በዝርው መፃፋቸውን ማረጋገጥ፡፡

# ሐ. ትምህርት ሶስት

የትምህርት (የምንባቡ ርዕስ) ፦ ውቅያኖስ በድንኳ ፕላኔት፣ፐሉቶ

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፦ 1፡30

የትምህርቱ ዓላማ፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ቅንጫቢውን በማንበብ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት መልሳቸውን በጽሁፍ ይገልጻሉ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- በግጥም የቀረበን ሀሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጠው ይጽፋሉ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፦**

- ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- “ውቅያኖስ በድንኳ ፕላኔት፣ፐሉቶ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡
- ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፦**

ማንበብ፣ ማጠቃለል፣ ማብራራትና መተንም፣ በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

**መርጃ መሳሪያ፦**

**(ማንተጋፍቶት ስለሺ፣2016)**

**ግምገማ፦**

ቅንጫቢውን በማንበብ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት መልሳቸውን በጽሁፍ መግለፃቸውን፣ ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ መስጠታቸውን እንዲሁም በግጥም የቀረበን ሀሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጠው መፃፋቸውን ማረጋገጥ፡፡

## መ. ትምህርት አራት

የትምህርት ርዕስ ፡- አስተዋፅኦ

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1:30

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የቀረበላቸውን አስተዋፅኦ/ቢጋር በጥሞና ያነባሉ፤ በመቀጠልም በቢጋሩ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች አገጣጥመው የተሟላ ድረሰት ይፅፋሉ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

- ለቀረበላቸው ቅድመ ንባብ ጥያቄ ተገቢውን መልስ በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- የቀረበላቸውን አስተዋፅኦ/ቢጋር በጥሞና ያነባሉ፡፡ በመቀጠልም በቢጋሩ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች ገጣጥመው የተሟላ ድርሰት ይፅፋሉ፡፡ የፃፉትን ድርሰት ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየርና በመገማገም አስተያየታቸውን በጽሁፍ ይሰጣጣሉ፡፡ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-**

ማንበብ፣ ምሰላ፣ ማብራራትና መተጎም፣ በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

**መርጃ መሳሪያ፡-**

የቀድሞው የ9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅሀፍ

**ግምገማ፡-**

የቀረበላቸውን አስተዋፅኦ/ቢጋር በጥሞና ማንበባቸውን፣ በቢጋሩ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች ገጣጥመው የተሟላ ድርሰት መፃፋቸውን፣ ከጓደኞቻቸው ባገኙት አስተያየት መሰረት አስተካክለው መፃፋቸውን ማረጋገጥ፡፡

## ሠ. ትምህርት አምስት

የትምህርት ርዕስ ፡- ምሳሌያዊ አነጋገር

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- 1:30

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ለምሳሌያዊ ንግግሮች ፍቺ ይሠጣሉ፡፡
- ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮችን ያሟላሉ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

- ለቀረቡላቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች በፅሁፍ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ የሰጡት ፍቺ ትክክል መሆኑን ከጓደኞቻቸው ጋር በመቀያየር አስተያየታቸውን በጽሁፍ ይሰጣጣሉ፡፡

* የቀረቡላቸውን ጅምር ምሌዊ ንግግሮች ያሟላሉ፡፡ በመቀጠል ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየርና በመገማገም አስተያየታቸውን በጽሁፍ ይሰጣጣሉ፡፡ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-**

ማንበብ፣ ማብራራትና መተንም፣ በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

**መርጃ መሳሪያ፡-**

የምሳሌያዊ ንግግር መፅሀፍ

**ግምገማ፡-**

ለምሳሌያዊ ንግግሮች ፍቺ መስጠታቸውን እና ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፡፡

# ረ. ትምህርት ስድስት

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፡- <u>መኖር ሰው ገደለ</u>

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- <u>1፡30</u>

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

* ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
* ቅንጫቢውን በማንበብ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት መልሳቸውን በጽሁፍ ይገልጻሉ፡፡
* ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡-**

* ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኂላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
* “መኖር ሰው ገደለ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡
* ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
* ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኂላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፡-**

ማንበብ፣ ማብራራትና መተንም፣ በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

***መርጃ መሳሪያ፡-***

*የነገ ናፍቆት (ገፅ 80-83)*

***ግምገማ፡-***

*ቅንጫቢውን በማንበብ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት መልሳቸውን በጽሁፍ መግለፃቸውን ማረጋገጥ፤ ታሪኩን አሳጥረው እንዲጽፉ ማድረግ፡፡*

## ***ሰ. ትምህርት ሰባት***

*የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፡- <u>ዋንጫውና ጠጁ</u>*

*ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፡- <u>1፡30</u>*

*የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-*

- *ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹ መልሳቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡*
- *ከቀደመ ልምዳቸውና ከምታነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡*
- *ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡*

***ዝርዝር ተግባራት፡-***

- *ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡*
- *"ዋንጫውና ጠጁ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡*
- *ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡*
- *ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡*

***የማስተማሪያ ዘዴ፡-***

*ማንበብ፣ መገመት፣ ዳራዊ እውቀትን መጠቀም፣ ማንፀባረቅ፣ በጥልቀት ማሰብ፣ ማጠቃለልና መፃፍ*

***መርጃ መሳሪያ፡-***

***ዳንኤል ክብረት (ዓ.ም ያልተገለፀ፣ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)***

***ግምገማ፡-***

*የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ማንበባቸውን እንዲሁም በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፡፡*

# ሽ. ትምህርት ስምንት

የትምህርት ርዕስ (የምንባቡ ርዕስ) ፦ ንጉሱና ሞት

ለትምህርቱ የተመደበው ጊዜ፦ 1፡30

የትምህርቱ ዓላማ፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄው መልሳቸውን በፅሁፍ ይመልሳሉ፡፡
- ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡

ዝርዝር ተግባራት፦

- ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ አጠገባቸው ካለ ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በፅሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- "ንጉሱና ሞት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ምንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡
- ከቀደመ ልምዳቸውና ከሚያነቡት ታሪክ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡፡
- ጥንድ በመሆን የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ባገኙት ማሻሻያ መሰረት መልሱን እንደገና አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴ፦**

ማንበብ፣ መገመት፣ ዳራዊ እውቀትን መጠቀም፣ ማንፀባረቅ፣ በጥልቀት ማሰብ፣ ማጠቃለልና መፃፍ

**መርጃ መሳሪያ፦**

ግሩም አበጀ (ከድረ ገፅ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

ግምገማ፦

የቀረበውን ቅንጫቢ ንባብ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ማንበባቸውን እንዲሁም በምንባቡ ውስጥ ለቀረቡት የሒደት ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሁፍ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## አባሪ አምስት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ሀ. በሙከራ ቡድኑ ለተካተቱ የ11ኛ “A” ክፍል ተማሪዎች ከትምህርት በፊት የቀረበ ቃለ መጠይቅ፡፡

መለያ ቁጥር ----------------------------------ቀን፡- -------------------------------------

ቦታ፡- -------------------------------------

ወድ ተማሪዎች፡- የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ ለሚደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡ ከቃለ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ ከታቀደው ዓላማ ውጭ ለሌላ ተግባር አይውልም፡፡ ስለዚህ ቀጥሎ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች እውነተኛና ትክክለኛ መልስ እንድትሰጠኝ/ጭኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

1. አማርኛ ቋንቋን ስትማሩ በቅንጅት እንድታነቡና እንድትጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች ነበሩ?---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ተጠቅማችሁ በቅንጅት እንድታነቡና እንድትፅፉ ምን አይነት ዘዴዎችን ጠቀማሉ? ----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
3. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማጣቀሻነት ከተዘጋጁት መፃህፍት መካከል ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድትለማመዱ የሚያደርጉ መጻህፍትን አግኝታችሁ ታውቃላችሁ?------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
4. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንድትማሩ ቢደረግ ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስላችኋል?------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**ለ. በሙከራ ቡድኑ ለተካተቱ የ11ኛ "A" ክፍል ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ የቀረበ ቃለ መጠይቅ፡፡**

**መለያ ቁጥር ---------------------------------ቀን፡- ---------------------------------------**

**ቦታ፡- ---------------------------------------**

ወድ ተማሪዎች፡- የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎቹን ለማጎልበት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ ለተደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡ በመሆኑም ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ የመጣውን ለውጥ ለማወቅ ይህ የድህረ ቃለ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም ቀጥሎ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች ትክክለኛና ተገቢ መልስ እንድትሰጡኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

1. ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማራችሁበትን መንገድ እንዴት ትገልፁታላችሁ? ---------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------
2. የዚህ ትምህርት አቀራረብ ከዚህ በፊት ከተማራችሁበት መንገድ ጋር ሲነፃፀር ምን ልዩነት አለው? የትኛው ተመራጭ ነው?---------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------
3. በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ መንገድ ሁሉም ተማሪዎች ቢማሩ ጠቀሜታ አለው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ ? ለምን?-----------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------
4. የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ቢሆን መሻሻል የሚገባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?--------------------------------------------------------------------------
   -------------------------------------------------------------------------------------

# አባሪ ስድስት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## ሀ. ከቅድመ ትምህርት ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

1. **አማርኛ ቋንቋን ስትማሩ በቅንጅት እንድታነቡና እንድትጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች ነበሩ? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 1 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 "እስካሁን በተማርኩበት መንገድ ውስጥ እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያደርጉ መልመጃዎች አላጋጠሙኝም፡፡ ቅድመ ንባብና ድህረ ንባብ ጥቄዎችም ቢኖሩ በቃላችን እንድንመልስ የሚያደርጉ ናቸው"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 በበኩሏ "እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያደርጉ መልመጃዎች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ አልፎ አልፎ አጫጭር ቃላትን እንድንጽፍ የሚያደርጉ መልመጃዎች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ቅድም እንደገለጽኩልህ አጫጭር ቃላትን ብቻ እንድንጽፍ የሚያዙ በመሆናቸው በቅንጅት ቀርበዋል ማለት አይቻልም"፡፡ በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 "ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድናከናውን የሚያደርጉ መልመጃዎች አላጋጠሙኝም" በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 " እኔ በበኩሌ አጋጥሞኝ አያውቅም ፤አንዳንድ ጊዜ በጽሁፍ መልሱ የሚሉ ጥያቄዎች ያጋጥማሉ ነገር ግን አጫጭር መልስ ብቻ የሚያሰጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሰው ስም፣ ዓመተ ምህረት፣ ቁጥሮችን ወዘተ. የሚመለከቱ መልሶችን እንድንጽፍ የሚጠይቁ ናቸው" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 " የመማሪያ መጻህፍቱ ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንሰራ የሚደርጉ መልመጃዎች የሏቸውም፡፡ ክሂሎቹ ለየብቻ የቀረቡ ናቸው" በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 በበኩሉ " ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የያዙ መልመጃዎች የሉም፡፡ በማለት መልሷል፡፡

2. **የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ቋንቋውን ተጠቅማችሁ በቅንጅት እንድታነቡና እንድትፅፉ ምን አይነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 2 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 “መምህራችን የሚያስተምሩን ለማስተማሪያነት የተዘጋጀውን መጽሀፍ ነው፡፡ መጽሐፉ ደግሞ ክሂሎቹን በቅንጅት እንድንተገብር በሚያደርግ መልኩ የተዘጋጀ ባለመሆኑ በመጽሐፉ መመሪያ መሰረት እንጅ የተለዬ ዘዴ አይጠቀሙም”፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 በበኩሏ “መምህራችን ቋንቋውን ተጠቅመን በቅንጅት እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያስችሉ ዘዴዎችን አይጠቀሙም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ መምህሩ የሚያስተምሩት የመማሪያ መጽሐፉን መንገድ ተከትለው መሆኑ ይመስለኛል”፡፡ በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 “እኔ በበኩሌ መምህራችን ቋንቋውን ተጠቅመን በቅንጅት እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ አላየሁም፡፡ እንድንጽፍ ወይም እንድናነብ የሚያደርጉ መልመጃዎችን ለየብቻ እንድንሰራ ነው የሚያዙን”፡፡ በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 “መምህራችን ቋንቋውን ተጠቅመን በቅንጅት እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያስችሉ ዘዴዎችን አይጠቀሙም በመማሪያ መጽሐፉ ያለውን ብቻ ነው የሚስተምሩት ይህ ደግሞ ለየብቻ የሚቀርብ ነው” በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 “መምህራችን የሚያስተምሩን መማሪያ መጽሐፉን ብቻ ነው፡፡ መጽሐፉ ደግሞ ቋንቋውን ተጠቅመን በቅንጅት እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያስችሉ መልመጃዎችን የያዘ አይደለም፡፡ በመሆኑም መምህራችን ሌሎች ዘዴዎችን በመፈለግ እንድናነብና እንድንጽፍ በሚያደርግ መልኩ አያስተምሩንም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ምን አልባት ከመጽሐፉ ከወጣን የክፍለጊዜ እጥረት ያጋጥመናል ከሚል ይመስለኛል”፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 በበኩሉ “መምህራችን ቋንቋውን ተጠቅመን በቅንጅት እንድናነብና እንድንጽፍ የሚያስችሉ ዘዴዎችን አይጠቀሙም” በማለት መልሷል፡፡

3. **ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማጣቀሻነት ከተዘጋጁት መፃህፍት መካከል ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድትለማመዱ የሚያደርጉ አግኝታችሁ ታውቃላችሁ? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 3 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 "ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማጣቀሻነት ከተዘጋጁት መፃህፍት መካከል ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንለማመድ የሚያደርጉ አግኝቼ አላውቅም፡፡ ሁሉም ማጣቀሻ መጻህፍት ክሂሎችን ለየብቻ እንድንለማመድ የሚያግዙ ናቸው"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 በበኩሏ "ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማጣቀሻነት የተዘጋጁት መፃህፍት ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንለማመድ የሚያደርጉ አይደሉም፡፡ አብዛኛዎቹ ድርሰትንና ጽህፈትን የሚመለከቱ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ንባብን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንለማመድ የሚያደርጉ መጻህፍት አጋጥሞኝ አያውቅም"፡፡ በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 "ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማጣቀሻነት የተዘጋጁ በርካታ መጻህፍት በትምህርትቤታችን ቤተመጻህፍት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መጻህፍትም ንባብን ለማስተማር የተዘጋጁ፤ ጽህትንና የአጻጻፍ ዘዴዎችን የያዙ፣ የልቦለድ እንዲሁም ሌሎች ክሂሎችን ለየብቻ ለማስተማር የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንለማመድ የሚያደርጉ መልመጃዎችን የያዙ አይደሉም"፡፡ በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 " ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንለማመድ የሚያደርጉ ማጣቀሻ መጻህፍት አጋጥመውኝ አያውቁም፤ ሁሉም መጻህፍት ክሂሎቹን ለየብቻ እንድንለማመድ በሚያደርግ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 " ማንበብና መጻፍን በቅንጅት እንድንለማመድ የሚያደርጉ ማጣቀሻ መጻህፍት አጋጥመውኝ አያውቁም"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 በበኩሉ " በርካታ የማጣቀሻ መጻህፍት በትምህርትቤታችን የሚገኙ ቢሆንም ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ንባብን ለማስተማር፣ ጽህፈትን ለማስተማር፣ ሰዋስውን ለማስተማር ወዘተ. የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በተረፈ ማንበብና መጻፍን በቅንጅት ለማስተማር የሚያገለግሉ ማጣቀሻ መጻህፍት የሉም"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የያዙ መልመጃዎች የሉም፡፡ በማለት መልሷል፡፡

4. **የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንድትማሩ ቢደረግ ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስላችኋል? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 4 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 "እስካሁን ባለው የትምህርት ጊዜ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርኩበት አጋጣሚ የለም፡፡ በመሆኑም ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ ያመዝናል ብዬ በልበ ሙሉነት መናገር አልችልም፡፡ ይሁን እንጂ ስገምት የማንበብና መጻፍ ክሂላችንን በአንድ ጊዜ እንድናጎለብትና እርስ በርስ አስተሳስረን ለመጠቀም የሚያግዝ ይመስለኛል፡፡ ይህ ማለት ጥቅሙ የሚያመዝን ይመስለኛል"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንድንማር ቢደረግ ጥቅሙ የሚያመዝን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ማንበብና መጻፍ ሁለቱም እርስ በርስ የተያያዙ የክሂል ዘርፎች በመሆናቸው

ያነበብነውን እየጻፍን፤ የጻፍነውን ደግሞ እያነበብን ብንማር የማንበብና የመጻፍ ብቃታችንን ለማሳደግ የሚረዳ ይመስለኛል"፡፡ በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 " ምንም እንኳን ከዚህ በፊት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት የመማር እድሉ ባያጋጥመኝም እንድንማር ቢደረግ ጥቅሙ የሚያመዝን ይመስለኛል"፡፡ በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንድንማር ቢደረግ ጥቅሙ የሚያመዝን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱንም ክሂሎች በተመሳሳይ ጊዜ ለማጎልበት ያግዛል፤ በተጨማሪም የምናነበውን ነገር እየተረዳነው እንድንሄድ ያግዘናል ብዬ አስባለሁ" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንድንማር ቢደረግ ጥቅሙ የሚያመዝን ይመስለኛል"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት እንድንማር ቢደረግ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም ክሂሎቹን አስተሳስሮ ለመጠቀም እና ክሂሎቹን ለማጎልበት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው" በማለት መልሰዋል፡፡

## ለ. ከድህረ ትምህርት ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

1. **ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማራችሁበትን መንገድ እንዴት ትገልፁታላችሁ? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 1 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 "ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርንበት መንገድ በጣም ጥሩ ነበር፡፡ ትምህርቱ የቀረበው የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት በመያዝ ነው፡፡

በትምህርቱ ሂደትም እያነበብንና እየጻፍን፤ የተሰጡ መልመጃዎችን በግልና በቡድን እየሰራን፤ በቡድን በመወያየት በግል የሰራነውን መልሰን እንደገና እያስተካከልን ነበር፡፡ በመሆኑም የነበረው የትምህርት ጊዜ ክሂሎቹ እንዴት እንደሚቀናጁ እንዲሁም ምን ያህል ትስስር እናዳላቸው ያየንበት ነበር"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 በበኩሏ "ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርንበት መንገድ በጣም ደስ የሚል ነበር፡፡ ለየት ያለ አቀራረብና አዲስ ዘዴ በመሆኑ ወደነው ተምረናል፤ ከዚህ በተጨማሪም ያለንን አቅም አውጥተን እንድንሰራ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጎልናል" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 "ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርንበት መንገድ ደስ የሚል ነው፤ መደበኛውንም ትምህርት በዚህ መንገድ ብንማር በጣም ጥሩ ነበር"፡፡ በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 " የተማርንበት መንገድ አዲስና ለየት ያለ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ደስ ብሎን ተምረናል" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 " "ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርንበት መንገድ በጣም ደስ የሚል ነበር፡፡ እኔ እንደዚህ አልጠበኩም ነበር፤ ሳልሰለችና ትምህርቱ ሳይደብረኝ እንድማር አድርጎኛል"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 ደግሞ "ለሁለት ወር የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርንበት መንገድ ከተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ የተለዩና የሚስብ ነበር" በማለት መልሷል፡፡

2. **የዚህ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከዚህ በፊት ከተማራችሁበት መንገድ ጋር ሲነፃፀር ምን ልዩነት አለው? የትኛው ተመራጭ ነው? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 2 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 " የዚህ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከዚህ በፊት ከተማርንበት መንገድ ጋር ሲነፃፀር ሰፊ ልዩነት አለው፡፡ ዋናው ልዩነት የማስተማሪያ መንገዱ ነው፡፡ ይህም ማለት በዚህ ዘዴ የተማርነው የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት ሲሆን በመደበኛው መርሃ ግብር የምንማረው ግን ክሂሎቹን ለየብቻ በመነጠል ነው" በመሆኑም የዚህ ዘዴ ተመራጭ ነው፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 በበኩሏ "የዚህ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከዚህ በፊት ከተማርንበት መንገድ በእጅጉ ይለያል" ተመራጩም ይህ ዘዴ ነው"፡፡ በማለት መልሳለች፡፡

ሌሎቹ ተማሪዎችም በተመሳሳይ የዚህ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከዚህ በፊት ከተማሩበት መንገድ ጋር ሲነፃፀር ሰፊ ልዩነት ያለው መሆኑንና የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማስተማር ዘዴው ተመራጭ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

3. **በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ መንገድ ሁሉም ተማሪዎች ቢማሩ ጠቀሜታ አለው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ ? ለምን? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 3 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 "በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ መንገድ ሁሉም ተማሪዎች ቢማሩ ጠቀሜታ አለው ብዬ አስባለሁ፤ ምክንያቱም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርንበት መንገድ በጣም ጥሩ ነበር፡፡ በመሆኑም ሁሉም ተማሪዎች በዚህ ዘዴ ቢማሩ የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸውን ለማጎልበት ያግዛቸዋል፤ በተጨማሪም የራስ የመተማመንና የማሰብ ችሎታቸውን ያጎለብታል" በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 " ጠቀሜታ አለው ብዬ አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም ይህ ዘዴ ተማሪዎቹ ችሎታቸውን አውጥተው እንዲጠቀሙ ያግዛቸዋል፡፡ በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 "በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ መንገድ ሁሉም ተማሪዎች ቢማሩ ጠቀሜታ አለው ብዬ አስባለሁ፤ ምክንያቱም የተሻለ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን እኛ በተግባር አይተነዋል፡፡ በመሆኑም ወደፊት በዚህ ዘዴ ቢማሩ ተማሪዎቹ በጣም ተጠቃሚ ይሆናሉ" በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 "በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ መንገድ ሁሉም ተማሪዎች ቢማሩ ጠቀሜታ እንዳለው በእርግጠኝነት መናገር ችላለሁ፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎቹን የማንበብና የመጻፍ ክሂል ለማጎልበት ተመራጭ ዘዴ ነው" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 "አዎ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ምክንያቱም በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ሲማሩ ክሂላቸውን ከማጎልበታቸውም በተጨማሪ ወደፊት ጥሩ ደራሲ እና ገምጋሚ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል ብዬ አስባለሁ"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 በበኩሉ "በዚህ አይነት የትምህርት አቀራረብ መንገድ ሁሉም ተማሪዎች ቢማሩ ጠቀሜታ እንዳለው አያጠያይቅም፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎቹን የማንበብና የመጻፍ ክሂል ብሎም በራስ መተማመን ይጨምራል ብዬ አስባለሁ" በማለት መልሷል፡፡

4. **የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ቢሆን መሻሻል የሚገባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 4 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

ተማሪ 1 "የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ቢሆን መልካም ነው፡፡ መሻሻል የሚገባው ነገር ብዬ የማስበው ትምህርቱ በሚተገበርበት ጊዜ ሌሎች ክሂሎችን ማዳመጥና መናገርን እንዲሁም የሰዋስው ክፍሎችንም አካቶ ቢቀርብ መልካም ነው ብዬ አስባለሁ"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 2 "የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ከሆነ በሰፊውና በርካታ ይዘቶችን በማካተት ሌሎች ክሂሎችን በሚያሻሽል መልኩ ቢዘጋጅ መልካም ነው" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 3 "የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ከሆነ መሻሻል አለበት በዬ የማስበው ሰፊ ዝግጅት ተደርጎበት ተጨማሪ ክፍለጊዜ ተመድቦለት ስራ ላይ ቢውል መልካም ነው"፡፡ በማለት የመለሰች ሲሆን ተማሪ 4 " ትንሽ ሠዓት ተጨምሮለት ቢዘጋጅ መልካም ነው" በማለት መልሳለች፡፡

ተማሪ 5 "የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ከሆነ በቂ ጊዜ እንዲመደብለት ቢደረግ መልካም ነው"፡፡ በማለት የመለሰ ሲሆን ተማሪ 6 በበኩሉ" የዚህ አይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ቢሆን መልካም ነው፡፡ መሻሻል አለበት ብዬ አላስብም፤ ሌሎች ክሂሎችንም ጨምሮ ቢቀርብ መልካም ነው በማለት መልሷል፡፡

አባሪ ሰባት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ሀ. የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና የአራሚዎች ውጤት

| የሙከራ ቡድን የአራሚዎች ውጤት | | | | | የቁጥጥር ቡድን የአራሚዎች ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ኮድ | አራሚ «ሀ» | አራሚ «ለ» | አራሚ «ሐ» | አማካይ ውጤት | መለያ ኮድ | አራሚ «ሀ» | አራሚ «ለ» | አራሚ «ሐ» | አማካይ ውጤት |
| **1** | 24 | 27 | 27 | 26 | **1** | 26 | 24 | 25 | 25 |
| **2** | 25 | 29 | 27 | 27 | **2** | 17 | 17 | 20 | 18 |
| **3** | 24 | 26 | 25 | 25 | **3** | 22 | 21 | 20 | 21 |
| **4** | 17 | 19 | 18 | 18 | **4** | 14 | 11 | 14 | 13 |
| **5** | 17 | 17 | 20 | 18 | **5** | 26 | 26 | 23 | 25 |
| **6** | 22 | 21 | 23 | 22 | **6** | 8 | 8 | 8 | 8 |
| **7** | 14 | 16 | 15 | 15 | **7** | 21 | 25 | 26 | 24 |
| **8** | 19 | 19 | 19 | 19 | **8** | 16 | 17 | 15 | 16 |
| **9** | 11 | 13 | 12 | 12 | **9** | 25 | 25 | 28 | 26 |
| **10** | 15 | 16 | 17 | 16 | **10** | 13 | 16 | 13 | 14 |
| **11** | 22 | 26 | 24 | 24 | **11** | 25 | 21 | 20 | 22 |
| **12** | 29 | 27 | 28 | 28 | **12** | 11 | 12 | 10 | 11 |
| **13** | 31 | 34 | 34 | 33 | **13** | 29 | 27 | 28 | 28 |
| **14** | 15 | 15 | 12 | 14 | **14** | 22 | 27 | 23 | 24 |
| **15** | 23 | 21 | 19 | 21 | **15** | 32 | 30 | 28 | 30 |
| **16** | 8 | 10 | 9 | 9 | **16** | 21 | 20 | 19 | 20 |
| **17** | 25 | 22 | 22 | 23 | **17** | 22 | 22 | 22 | 22 |
| **18** | 12 | 16 | 14 | 14 | **18** | 34 | 35 | 33 | 34 |
| **19** | 9 | 7 | 8 | 8 | **19** | 10 | 10 | 13 | 11 |
| **20** | 27 | 23 | 22 | 24 | **20** | 22 | 22 | 25 | 23 |
| **21** | 14 | 11 | 14 | 13 | **21** | 8 | 9 | 7 | 8 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **22** | 6 | 9 | 9 | 8 | **22** | 15 | 15 | 12 | 14 |
| **23** | 23 | 21 | 25 | 23 | **23** | 18 | 20 | 19 | 19 |
| **24** | 35 | 34 | 30 | 33 | **24** | 30 | 30 | 27 | 29 |
| **25** | 16 | 15 | 20 | 17 | **25** | 11 | 12 | 13 | 12 |
| **26** | 26 | 26 | 26 | 26 | **26** | 20 | 19 | 21 | 20 |
| **27** | 23 | 24 | 22 | 23 | **27** | 32 | 28 | 30 | 30 |
| **28** | 18 | 16 | 14 | 16 | **28** | 16 | 14 | 15 | 15 |
| **29** | 12 | 16 | 17 | 15 | **29** | 20 | 19 | 21 | 20 |
| **30** | 28 | 31 | 25 | 28 | **30** | 20 | 25 | 23 | 23 |
| **31** | 24 | 24 | 27 | 25 | **31** | 12 | 12 | 12 | 12 |
| **32** | 10 | 11 | 9 | 10 | **32** | 8 | 7 | 9 | 8 |
| **33** | 11 | 12 | 13 | 12 | **33** | 10 | 10 | 10 | 10 |
| **34** | 10 | 14 | 9 | 11 | **34** | 20 | 18 | 19 | 19 |

## ለ. የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ የድህረ ትምህርት ፈተና የአራሚዎች ውጤት

| የሙከራ ቡድን የአራሚዎች ውጤት | | | | | የቁጥጥር ቡድን የአራሚዎች ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መለያ ኮድ | አራሚ «ሀ» | አራሚ «ለ» | አራሚ «ሐ» | አማካይ ውጤት | መለያ ኮድ | አራሚ «ሀ» | አራሚ «ለ» | አራሚ «ሐ» | አማካይ ውጤት |
| **1** | 34 | 32.5 | 35.5 | 34 | **1** | 25.5 | 27 | 25.5 | 26 |
| **2** | 35 | 37 | 36 | 36 | **2** | 16.5 | 17 | 16.5 | 17 |
| **3** | 32.5 | 32.5 | 34 | 33 | **3** | 19.5 | 20.5 | 20 | 20 |
| **4** | 24 | 26 | 25 | 25 | **4** | 23.5 | 22 | 24.5 | 23 |
| **5** | 24 | 24 | 24 | 24 | **5** | 26.5 | 26 | 25.5 | 26 |
| **6** | 23.5 | 25.5 | 26 | 25 | **6** | 8 | 8 | 8 | 8 |
| **7** | 24 | 24 | 21 | 23 | **7** | 26 | 25.5 | 23.5 | 25 |
| **8** | 22 | 22 | 22 | 25 | **8** | 15.5 | 15.5 | 17 | 16 |
| **9** | 20.5 | 19 | 17.5 | 19 | **9** | 25 | 25 | 27 | 26 |
| **10** | 22 | 23 | 24 | 23 | **10** | 12 | 14 | 13 | 13 |
| **11** | 30 | 31.5 | 31.5 | 31 | **11** | 23 | 22.5 | 20.5 | 22 |
| **12** | 40 | 37.5 | 39.5 | 39 | **12** | 11 | 12 | 10 | 11 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **13** | 45 | 47 | 46 | 46 | **13** | 31.5 | 29 | 29.5 | 30 |
| **14** | 21 | 22 | 23 | 22 | **14** | 22 | 21 | 23 | 22 |
| **15** | 25 | 24 | 26 | 25 | **15** | 27 | 24.5 | 23.5 | 25 |
| **16** | 17.5 | 19 | 17.5 | 18 | **16** | 21 | 20 | 19 | 20 |
| **17** | 26 | 25.5 | 26.5 | 26 | **17** | 23 | 24.5 | 21.5 | 23 |
| **18** | 21.5 | 23 | 21.5 | 22 | **18** | 34.5 | 34.5 | 36 | 35 |
| **19** | 18 | 16.5 | 16.5 | 17 | **19** | 9.5 | 9 | 8.5 | 9 |
| **20** | 29.5 | 29 | 31.5 | 30 | **20** | 25.5 | 23.5 | 23 | 24 |
| **21** | 21.5 | 23 | 21.5 | 22 | **21** | 8 | 9 | 7 | 8 |
| **22** | 18 | 20 | 16 | 18 | **22** | 15.5 | 15 | 14.5 | 15 |
| **23** | 26 | 26 | 26 | 26 | **23** | 18 | 17 | 19 | 18 |
| **24** | 43 | 42 | 41 | 42 | **24** | 30.5 | 30 | 29.5 | 30 |
| **25** | 24 | 24 | 24 | 24 | **25** | 13.5 | 12.5 | 13 | 13 |
| **26** | 35 | 34 | 36 | 35 | **26** | 20 | 22 | 21 | 21 |
| **27** | 27 | 29.5 | 27.5 | 28 | **27** | 33 | 35.5 | 33.5 | 34 |
| **28** | 23 | 26 | 23 | 24 | **28** | 16 | 14 | 15 | 15 |
| **29** | 24 | 20 | 22 | 22 | **29** | 20 | 19 | 21 | 20 |
| **30** | 35.5 | 37.5 | 38 | 37 | **30** | 22.5 | 24.5 | 23 | 23 |
| **31** | 34 | 33 | 35 | 34 | **31** | 12 | 12 | 12 | 12 |
| **32** | 19 | 18 | 17 | 18 | **32** | 5.5 | 6.5 | 6 | 6 |
| **33** | 21 | 22 | 23 | 22 | **33** | 8 | 8 | 8 | 8 |
| **34** | 20 | 18.5 | 18.5 | 19 | **34** | 19.5 | 20.5 | 20 | 20 |

## ሐ. የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ ቅድመ ትምህረት የፈተና ውጤት

| የሙከራ ቡድን | | የቁጥጥር ቡድን | |
|---|---|---|---|
| መለያ ኮድ | አጠቃላይ ውጤት 50% | መለያ ኮድ | አጠቃላይ ውጤት 50% |
| 1 | 26 | 1 | 25 |
| 2 | 27 | 2 | 18 |
| 3 | 25 | 3 | 21 |
| 4 | 18 | 4 | 13 |
| 5 | 18 | 5 | 25 |
| 6 | 22 | 6 | 8 |
| 7 | 15 | 7 | 24 |
| 8 | 19 | 8 | 16 |
| 9 | 12 | 9 | 26 |
| 10 | 16 | 10 | 14 |
| 11 | 24 | 11 | 22 |
| 12 | 28 | 12 | 11 |
| 13 | 33 | 13 | 28 |
| 14 | 14 | 14 | 24 |
| 15 | 21 | 15 | 30 |
| 16 | 9 | 16 | 20 |
| 17 | 23 | 17 | 22 |
| 18 | 14 | 18 | 34 |
| 19 | 8 | 19 | 11 |
| 20 | 24 | 20 | 23 |
| 21 | 13 | 21 | 8 |
| 22 | 8 | 22 | 14 |
| 23 | 23 | 23 | 19 |
| 24 | 33 | 24 | 29 |
| 25 | 17 | 25 | 12 |
| 26 | 26 | 26 | 20 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **27** | 23 | **27** | 30 |
| **28** | 16 | **28** | 15 |
| **29** | 15 | **29** | 20 |
| **30** | 28 | **30** | 23 |
| **31** | 25 | **31** | 12 |
| **32** | 10 | **32** | 8 |
| **33** | 12 | **33** | 10 |
| **34** | 11 | **34** | 19 |
| ብዛት=34 | አማካይ=19.2941 | ብዛት=34 | አማካይ=19.2353 |

## መ. የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት

| **የሙከራ ቡድን** | | **የቁጥጥር ቡድን** | |
|---|---|---|---|
| *መለያ ኮድ* | አጠቃላይ ውጤት 50% | *መለያ ኮድ* | አጠቃላይ ውጤት 50% |
| **1** | 34 | **1** | 26 |
| **2** | 36 | **2** | 17 |
| **3** | 33 | **3** | 20 |
| **4** | 25 | **4** | 23 |
| **5** | 24 | **5** | 26 |
| **6** | 25 | **6** | 8 |
| **7** | 23 | **7** | 25 |
| **8** | 25 | **8** | 16 |
| **9** | 19 | **9** | 26 |
| **10** | 23 | **10** | 13 |
| **11** | 31 | **11** | 22 |
| **12** | 39 | **12** | 11 |
| **13** | 46 | **13** | 30 |
| **14** | 22 | **14** | 22 |
| **15** | 25 | **15** | 25 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **16** | 18 | **16** | 20 |
| **17** | 26 | **17** | 23 |
| **18** | 22 | **18** | 35 |
| **19** | 17 | **19** | 9 |
| **20** | 30 | **20** | 24 |
| **21** | 22 | **21** | 8 |
| **22** | 18 | **22** | 15 |
| **23** | 26 | **23** | 18 |
| **24** | 42 | **24** | 30 |
| **25** | 24 | **25** | 13 |
| **26** | 35 | **26** | 21 |
| **27** | 28 | **27** | 34 |
| **28** | 24 | **28** | 15 |
| **29** | 22 | **29** | 20 |
| **30** | 37 | **30** | 23 |
| **31** | 34 | **31** | 12 |
| **32** | 18 | **32** | 6 |
| **33** | 22 | **33** | 8 |
| **34** | 19 | **34** | 20 |
| ብዛት= 34 | አማካይ=26.8824 | ብዛት 34 | አማካይ=19.5294 |

**ሠ. የቅድመ ፈተና አጠቃላይ ውጤት ቡድናዊ ገላጭ ስታትስቲክስ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት**

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | ቡድኖቹ | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይት Std. D | መደበኛ ስህተት አማካይ | የቲ-ዋጋ (T) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ሰንጠረዥ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ | 34 | 19.2941 | 7.01310 | 1.20274 | 0.034 | 66 | 0.973 | የለም |
| | የቁጥጥር | 34 | 19.2353 | 7.08416 | 1.21492 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (significant level) $^*P>0.05$

**ረ. የድህረ ፈተና አጠቃላይ ውጤት ቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ በባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት**

| ቅድመ ትምህርት ፈተና | ቡድኖቹ | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይት Std. D | መደበኛ ስህተት አማካይ | የቲ-ዋጋ (T) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ሰንጠረዥ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ | 34 | 26.8824 | 7.40092 | 1.26925 | 4.048 | 66 | 0.000 | አለው |
| | የቁጥጥር | 34 | 19.5294 | 7.57682 | 1.29941 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (significant level) $^*P < 0.05$

# አባሪ ስምንት

## ከጥናቱ የተገኙ ፎቶዎች ናሙና

### ሀ. ተማሪዎቹ ፈተና ሲወስዱ የሚያሳይ ፎቶ



## ለ. ተማዎቹ ትምህርቱን ሲማሩ የሚያሳይ ፎቶ



ሐ. ተማሪዎቹ ቃለ-መጠይቅ ሲደረግላቸው የሚያሳይ ፎቶ



# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜንና ፊርማዬን ያስቀመጥኩት በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር የድህረ-ምረቃ ተማሪ ስሆን ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በስራው ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ በዋቢ መፅሀፍት ላይ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ______________________________

ፊርማ ______________________________

የማስረከቢያ ቀን _____________________